እንድትጠቀምበት ካላደረግን፥ በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ክብር ብቻ እንዲገለጽበት ከመለኮታዊ ፍቅሩ የተነሣ የሰጠውን አገልግሎት፣ ለኃላፊና ለጠፊ ሥልጣን ካዋልነው፥ እርግማንን ስለሚያስከትል እጅግ በጣም ኡድገን ልንጠነቀቅ ይገባል።[145]

በኋለኛው ዘመን ለበጎች የማይራሩ፣ ጨካኞች እንደሚመጡ የተነበየውን የሐዋርያውን ማስጠንቀቂያ በመገንዘብ ነበር፣ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ አትለፍ፥ ከዚህ አትቀንስ፥ የሚል ሕገ ቀኖና የሠራ ችው።[146] ይህን ሕገ ቀኖና ደግሞ የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን የማጥናትና የመጠበቅ፣ እንዲሁም የማስጠበቅ፣ ግዴታ ስላለባት ይሄው በሚቀጥለው ዐቢይ ከፍል የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የሠራችው ቀኖና፥ የቀኖና መንሥኤና ዓላማ፥ እንዲሁም አሁን የሚሰጠው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንመለከታለን። ይህም ጥናት አሁን ያለንበትን ደረጃ በማገናዘብ ሚዛናዊ ዕይታ እንዲኖረን ሊያ ደርግ ይችላል።

[145] የሐዋ 8፡ 20

[146] ቀኖና ምንድን ነው? የሚለውን ይመልከቱ።

ክፍል ሁለት፤

የቀኖና መንሥኤና ዓላማ

የቀኖና መንሥኤና ዓላማ፣ የቀኖና ትርጉምና አስፈላጊነት፥ በእየዘመኑ ግንዛቤ ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ላይ ያለው ጥቅም፣ የቀኖና ምንጮችና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር ያለው ዝምድና፣ እንዲሁም ቀኖናው የሰጣቸው ጥቅሞች በሚሉ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለአንባብያን ቀርቧል። ይህንን ዐቢይና ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ አንባብያን በጥሞና እንዲያነቡትና በሥራም ላይ እንዲያውሉት ይጠየቃሉ።

የክርስትና እምነት መጽሐፋዊ በመሆኑ፣ የሚደረጉት ክንውኖች ሁሉ ግጭት እንዳይፈጥሩ ጥንቃቄ ተደርጓል። ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ጀምሮ የእግዚአብሔር ረጅም መለኮታዊ ዓላማ እንደ ነበር በነቢያቱ አፍ፣[147] በሕግጋቱ፣[148] በካህናቱ፣ በመሥዋዕቱና እንዲሁም በሌሎች ቅዱሳን መጻሕፍት ሲመሰከር ቆይቷል። ክርስቶስ ሰው ሁኖ በዚህ ምድር ሲመላለስ ትምህርቱን የጀመረው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ መፈጸሙን እያሳወቀ[149] ነበር፤ ትእዛዙን እንዲያስፈጽሙ የተመረጡት፣ ደቀ መዛሙርትና ተከታዮቻቸው የተቀበሉት አደራ፣ እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ በሥራ ላይ መዋል

[147] ዕብ 1፡ 1

[148] ሉቃ 24፡ 44

[149] የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ። ማቴ 4፡ 17 ፤ ማር 1፡ 14

[156] The Apostolic Canons: Transelated by Henry R. Prcival 1899.

አለመዋሉን ለማወቅ መለኪያ ያስፈልግ ነበር።[150] በዚህ መነሻነት የቀኖናን ትርጉምና አስፈላጊነት እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ጥቅም በዚህ ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን።

1. <u>የቀኖና ትርጉም፤</u>

ቀኖና ማለት <u>ካኖን</u> ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ቀጥታ መሥመር የሥነ ጥበብ መለኪያ፣[151] ግልጽ የሆነ ዝርዝር ወይም ቀኖር፣ አንድን ነገር መቀነስ ወይም መጨመር የማያስችል መለኪያ ማለት ነው። በክርስትና ቋንቋ የሚነበቡ መጻሕፍት፣[152] የሚጸለየው ጸሎት፣ የሚካሄዱ ሥርዓቶች ሁሉ የሚለኩበት የሚወሰኑበት መለኪያ ማለት ነው።

ከዚህ በመነሣት የመጻሕፍት ቀኖና፣[153] የሥርዓተ አምልኮ ቀኖና፣[154] የሥርዓተ ጸሎትና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና፣ በመባል ይታወቃል፤ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ከፍሌ የግእዝ መዝገበ ቃላት ቀኖናን፣ <u>ቀነነ</u> ÷ አገገ፣ (ሕግ ሠራ)፣ ሠራ÷ ደነባ (ደንብ)÷ ሕግ÷ ሥርዓት÷ ደንብ አቆመ፤ በማለት ይገልጠዋል።[155] የቀኖና ጥሬ ትርጉሙ ሕግ÷ ደንብ÷ ሥርዓት÷ ቅጣት ማለት ነው። መቀኑን፣

---

[151] *John Anthony McGuckin, the Westmister Hand book to Patristic Theology, pp51-53*
ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት፣ ገጽ 800
[152] *John Anthony McGuckin, The Wwestmister Hande book to Patristic Theology*
[153] *Bruce F.F, the Canon of The Scripture, p. 22*

[154] *Ibid, p. 23*
[155] *ኪዳነ ወልድ ክፍሌ, መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት፣ ገጽ 800*

[156] (ሰጠ÷ አደለ÷ ደለደለ÷ ቆረሰ÷ ተነተነ) የሚለው የኢትዮጵያ የገዳማት የምግብ አደላ ሥርዓት የወጣው ከዚህ ግሥ ነው።

ስለ ቀኖና ስናጠና ከዚህ ግሥ ተነሥተን የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊ÷ ማኅበራዊ÷ አስተዳደራዊ÷ በተለይም ከህነታዊ ኃላፊነትን ሁሉ ምን እንደ ሆነ መረዳት እንችላለን። ከላይ እንደ ተገለጠው ቀኖና ማለት ቤተ ክርስቲያን አምልኮቷን÷ ጸሎቷን÷ ቅዱሳት መጻሕፍቶቿን÷ ከህነታዊ አገልግሎቷን የለካችበትና የምትለካበት÷ የምትጥልበትና የምታሳልፍበት መመዘኛ ሕጓ ነው።[157]

በሌላ አባባል ከዓለም ተለይታ ራሷን የቻለች ተቋም እንድትሆንና በዓለም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን፣ አንድ ዓይነት አመራርና አምልኮ እንዲኖራት ያደረገው ይሄው ቀኖና ነው፤[158] ቀኖና ለቤተ ክርስቲያን መመሪያ ብቻ ሳይሆን የአንድነቷ መሠረት ነው።[159] ምክንያቱም ከተሠራው ወይም ከተቀነነው መሥመር እንዳንወጣ ገድቦና ወስኖ የሚይዘን ሚዛናችን እንዳያጋድል ቀጥ ብለን[160] እን ድንሄድ የሚያደርገን÷ የተቀበልነውን ትውፊት በተቀበልነው መሠረት በሥራ ላይ ማዋል አለማዋላችንን የምናይበት የሥራ መስታይታችን ነው። ስለዚህ ቀኖና፣ ቤተ ክርስቲያንን እንድንጠ ብቅ የሚያድረገን፣ መሠረታዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው።[161]

---

[156] *ዝኒ ከማሁ*
[157] *Lewis J. Patsavos, Spiritual, Dimensions of the Holy Canons, 7*
[158] *Ibid 8*
[159] *Ibid 9*
[160] *Ibid 10-11*

[161] *Ibid*

አንድ ካህን ወይም ምእመን ቀኖና ጥሏል ከተበለ፤ ሕግን ተላል ፏል ማለት ነው። ስለዚህ ነው ስለ ቀኖና መጻሕፍት ማጥናት ያስፈለገን።

2. <u>የቀኖና አስፈላጊነት፤</u>

ቤተ ክርስቲያን፣ የምታነባቸው መጻሕፍት፣ የምታምነው እምነት፣ የምታካሂደውም ሥርዓተ አምልኮ፣ ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ፍቅር የተነሣ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ያለምንም ስሕተት የተቀበለቻቸው ስጦታዎች መሆናቸው ይረጋገጥ ዘንድ፣ ቀኖና አስፈለገ።[162] ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበትን ዘመን፣ የዓለምን ሁኔታና አቅጣጫ መመልከቱ የቀኖናን አስፈላጊነት የጐላ ያደርገ ዋል። ቤተ ክርስቲያን ገና ስትመሠረት በዘመኑ ከነበረው ሁኔታ የተነሣ፣ ሥራዋን እንዳትሠራ የሚያደርጉ ቢያንስ ሦስት ፈተናዎች ነበሩ።[163]

<u>አንደኛው</u>፣ አይሁድ እግዚአብሔር ያከናወነውን የማዳን ሥራ ከብሉይ ኪዳን ሕግ ጋር በማጋጨት፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ጠላት ሆነው መነሣታቸው ነው።[164]

<u>ሁለተኛው</u>፣ ከአይሁድ፣ ከሮማውያንና ከግሪካውያን ፍልስፍና የተ ውጣጣው፣ *በዕውቀት አንድናለን የሚለው "የግኖስቲክ"*[165] *አሰተ ምህሮ። ነው።*

[162] Ibid , 19
Harold O.J. Brown,Heresy and Oethodocy in The Histry of the Church, pp. 3-4
[164] *Ibid,p. 7*
[165] *Ibid, p. 29*

<u>ሦስተኛው</u>፤ የባለ ብዙ አምላኩ የሮማ መንግሥት ጫቆናና የአምልኮ ሥርዓት ነው።[166] እነዚህ ሦስት ነጥቦች በሌላኛው ርእስ መጠነኛ ማበራሪያ ይሰጥባቸዋል።

3. የቀኖና ምንጮች፤

ቀኖና ያስፈለገውን ያህል የቀኖና ምንጮችንም ማየት ተገቢ ይሆናል። ከላይ በተሰጠው ገለጻ ለመረዳት እንደሚቻለው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ከአደጋ ለመጠበቅ፣ አስጠባቂ ቀኖና ያስፈልጋል፣ ቀኖና እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ የቀኖና ምንጮችንም ማወቅና መመርመር እንደዚሁ ወሳኝና አስፈላጊም ነበር። የቀኖናዎቹ ምንጮች እንደ እየሁኔታው እየተጠኑ ፣ በተለያየ ጊዜያትና አጋጣሚዎች የተወሰኑ ሲሆን፤ ከዚህ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሀ/ ዓለም አቀፋዊ ቀኖናዎች፣[167]

ለ/ ክልላዊ ቀኖናዎች፣[168]

ሐ/ በቤተ ክርስቲያን አባቶች የተቀነኑ ግላዊ ቀኖናዎች፣ በመባል ይታወቃሉ።[169]

[166] Ibid, 17
[167] *የመጀመሪያው የኒቅያ ጉባኤ፥ ሁለተኛው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ፥ ሦስተኛው የኤፌሶን ጉባኤ ቀኖነዎች በፍትሐ ነገሥታችን መቅድም ላይ የእያንዳንዱ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ቀኖና ምልክት አለው። ለምሳሌ የሐዋርያት ቀኖና "ዓይን " የዲዲስቅልያው "ደስቅ" በማለት ሰሙሉ ምንጫቹን ያብራረል።*
[168] *ዝኒ ከማሁ በሙሉ*
[169] *ዝኒ ከማሁ*

በተለይም ከልሳዊና ግለሰባዊ ቀኖናዎች የተባሉት በዓለም አቀፋዊው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተመርምረው ጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ እንደ ቀኖና እንዲያገለግሉ ተወስደዋል።[170]

3.1. ዓለም አቀፋዊ ቀኖናዎች፤

እነህ ቀኖናዎች ከዘመነ ሐዋርያት አንሥቶ፣ የቤተ ክርስቲያን መመሪያዎች ተብለው የተወሰኑ ናቸው:: በሐዋርያት ስም የሚጠሩ የእነዚህ ቀኖናዎች ቁጥራቸው፣ ሰማንያ አንድና ሰማንያ ሁለት ናቸው። በአንዳንድ ምንጮች ደግሞ ሰማንያ ሁለትና ሰማንያ ሦስት ቀኖናዎች ሁነው ይገኛሉ። [171] እነዚህ ቀኖናዎች በተከታታይ ጉባኤያት ተቀባይነት አግኝተዋል። እነዚህ ሰማንያ ሁለትና ሰማንያ አንድ ቀኖናዎች በብዛት ያተኮሩት በክህነት አሰጣጥና አቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ነው። ለምሳሌ ሁለት መሠረታዊ አንቀጾችን ብንጠቅስ ጳጳስ በሁለት ወይም በሦስት ጳጳሳት ይሾም ይላል ።[172] እንደገና ዲያቆንና ቄስ በአንድ ጳጳስ ይሾም ይላል፤ ክህነት ሦስት ብቻ መሆኑን ለማስረጃነት የሚቀርበው ይህ ቀኖና ነው።[173] በቀኖናዎቹ ከሞላ ጎደል የተደነገጉት ድንጋጌዎች ስለ ክህነትና የክህነት አገልገሎት ነው::

[170] The Seven Ecumenical Councils of the Undivided Church, Their Canons and Dogmatic Decees,
[171] ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ አራት ቍጥር 57 ኒቅያ ገጽ 31 The Firste Ecumenical Council of Nice Canon IV
[172] ዝኒ ከማሁ፣ ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት
[173] ዝኒ ከማሁ Ibid

በአሁኑ ጊዜ በየትኛውም የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ፤ በዚህ ጽሑፍ በምንጭነት የተገለገልነው ግን *'The St. Pachomius Orthodox Library, St. Angelina of Serbia and Albania 19'9* የሚለው ምንጭ ነው ::[174]

የእኛ ቀኖና ምንጭ በሆነው ፍትሐ ነገሥታችን የጳጳሳትን ሹመትና ደረጃ በተመለከተ ከሰማንያ ሁለት በላይ ቀኖናዎች ተዘርዝረዋል።[175] ይህም The Church of the Ancient Councils by Arch Bishopn Peter L; Huillier[176]. እንዲሁም The Seven Ecumenical Councils vo 14 Edit ed by Henry R. Percivale የሚገኙት ተመሳሳይነት አላቸው።[177]

በሁለተኛ "ከልብ የተገኘ" በተባው ከፍል ውስጥም እንዲሁ ብዙ ተመሳሳይ የቀኖና ዓይነቶች ይገኛሉ። አንደዚሁም በልዩ ልዩ ስብስቦች ውስጥ ያሉ ዓለም አቀፋዊ ቀኖናዎች ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ቀኖናዎች በኮድ በመቀመጣቸው ምክንያት የግልጽነት ችግር አለባቸው። በዚህ ዙሪያ ላይ ጥናት ያጠኑት፥ ዶክተር ዲበ ኩሉ ዘውዴ ለችግሩ መፍትሄ ለማቅረብ ጥረት ቢያደርጉም በግልጽ የተቀመጠ መፍትሄ አይመስልም::

[174] *The Apostolic Canons of the Holy and Altogether August Apostles [Latin Version adds: set forth by Clement, Pontiff of the Roman Church Canon I and II*
[175] *በፍትሐ ነገሥት የተገለጠው የቀኖና ብዛት በአንቀጽ አራት ቍጥር 38 ቍጥር 79 የተዘረዘሩት ቀኖናዎች ሲሆኑ፤ ከመጽሐፍ የተገኙና ከልብ የመነጩ በሚል ከሁለት ከፍሏቸዋል። ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ገጽ 28 - 37*
[176] *Arch bishop Peter L'Huollier, the Chuch of the Ancient Councils the Disciplinary Work of the First Four Ecumenical Councis pp 3-10*
[177] *ፍትሐ ነገሥት መቅድም*

ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ፣ "እስከዚህ የታሪኩ ሂደት በሥነ ጽሑፍ ሕግ የሚንቀሳቀስ ሲመስል፣ ነገር ግን ቀጥሎ ማለት ስለ ሁለት መጻሕፍት፣ ሕግ ከተረከ በኋላ እንደ ገና ደግሞ ስለ ሦስት መጻሕፍት 1. ረስጠለ መጽሐፍ ፣ 2. ረስጠብ መጽሐፍ ፣ 3. ረስጠጅ መጽሐፍ ይነግረናል ። ስለዚህ ሦስተኛው መጽሐፍ ረስጠጅ ከወዴት መጣ? የሚል ጥያቄ ይነሣል። ምክንያቱም በመለካውያንና ንስጥሮሳውያን ዘንድ የሚገኘው ከሁለት ተከፍሎ ሁለት መጻሕፍት ረስጣና ረስጠብ ሁኖ መገኘቱ ሲደገፍ፣ ሦስተኛው መጽሐፍ ረስጠጅ ከወዴት መነጨ ነው? ትኩረቱ"[178] በማለት አቅርበዋል::

በዚህ ሐሳብ መሠረት፣ የፍትሐ ነገሥት ችግር ትከከለኛ ቀኖና ያለመያዝ አይደለም፤ የቀኖናዎች ምንጮች በተለየ ኮድ በመጻፋቸው ምክንያት፥ የቱ ከየቱ ምንጭ መሆናቸው በትክክል አለመጠናታቸው ነው።[179] ያም ቢሆን ጊዜ ተወስዶ ከተጠና ማሰባሰቡ ቀላል ሊሆን ይችላል። በዚህ መልክ እነዚህ ዓለም አቀፍ ቀኖናዎች የተባሉት፣ ከዚህ በላይ በመጠኑ በተገለጸው መሠረት የተቀነኑ የሐዋርያት ቀኖናዎች በኋላዎቹ ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ የጸደቁ እንዲሁም በጠቅላላው የተቀነኑ፣ ማለትም በኒቅያ፥[180] በኤፌሶን፥ በቀሥጥንጥንያ ጉባኤያት የተቀነኑ ቀኖናዎች

[178] ዲበ ኩሉ ዘውዴ፣ ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 104

[179] ዝኒ ከማሁ

[180] The nicea cauoncil 325 ad

ናቸው።[181] እነዚህም አሁን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ፣ ተግባራዊ የምታደርጋቸው ቀኖናዎች ናቸው።

3.2. ክልላዊ ቀኖናዎች፤

ክልላዊ ቀኖናዎች የተባሉት፣ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ማለትም በእስክንድርያ፥ በካርቴጅ፥ በአዴሳ፥ በኤፌሶን፥ በኢየሩሳሌም፥ በሮም የሚገኙ ሲኖዶሶች በየግላቸው የክልል ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያስተዳድሩበት ያወጧቸው ቀኖናዎች ናቸው። ለምሳሌ በየክልሉ የተካሄዱ ጉባኤያትና የተቀነኑ ቀኖናዎችን መመልከት ይቻላል::

የዓለም አቀፉን ቀኖና ስብስብ የያዘው ጉባኤ በእንግሊዘኛ የሚከ ተለውን አስፍሯል። T*he Canons of the Councils of Anc yra,Neo/Esarea,Antioch and Laodi cea Canons Were accepted and Received by the Ecumenical Synods*[182] የእነዚህ ሲኖዶሶች ጉባኤያት የወሰኗቸው ቀኖናዎች ከሞላ ጎደል በእኛ የፍትሐ ነገሥት ስብስብም ይገኛሉ:: ቀኖናዎቹ በብዛት የሚያተኩሩት በጳጳሳት የሥልጣን ደረጃ፣ የዲያቆናትን የሥራ ድርሻ፣ የካህናትን አገልሎትና የካህናትን የጋብቻ ሥርዓት፣ ለቅ ዱስ ቊርባን አገልገሎት የሚውሉ የመሥዋዕት እቃዎችንና የመ

[181] *The Council of Constantinople The First Council of Constantinople p. 381 A.D and the Council of Ephesus 431 A.D*

[182] *The Seven Ecumnical Councils pp 63-160*

ሥሪያ ቦታዎችን፣ ከህነትን የሚያስይዙ ስሕተቶችን የሚያጠቃ ልሉ[183] ናቸው::

2.3. ግለ ሰባዊ ቀኖናዎች፣

ግላዊ ቀኖናዎች የተባሉት፣ ግማሾቹ ከላይ በሁለተኛ ደረጃ ከጠቀ ስናቸው ከክልል ቀኖናዎች ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣[184] በተ ለይ ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር የያዘው የአትናቴዎስ ቀኖና ፣ [185] የእምነትን መግለጫ የያዘው የሄሬኔዎስ ቀኖና፣[186] ስለ ከህነት የሚተርከው የአግናጥዮስና የቀለሚንጦስ ቀኖናዎች፣[187] እንዲሁም ስለ ጥምቀትና ከከህደት ስለ ተመለሱ ምእመናን የሚያዘው የሲብሪያን ቀኖናዎችን፣[188] ለምሳሌ ያህል መጥቀስ ይቻላል። የሌሎችም በብዛት ስለ ጾም ስለ ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የተጻፉ፤ ነገር ግን በዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነትን አግኝተው በሥራ ላይ የዋሉ ቀኖናዎች ናቸው።

[183] ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አምስትና አራት ተዘርዝረው ይገኛሉ።

[184] በፍትሐ ነገሥት መቅድም ላይ የተዘረዘሩ የግል ቀኖናዎች የሮሜ ሊቀ ጳጳስ የአቡሊዲስ፣ የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ የአባ ጴጥሮስ፣ የቂሣሪያ ሊቀ ጳጳስ ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ቀኖናዎች ይገኛሉ። ይላል የፍትሐ ነገሥት መቅድም።

[185] Athansius Select Works and Letters from Letter 39 on Ester ,551; ዲበ ኩሉ ዘውዴ ዶክተር፣ 81 ቅዱሳት መጻሕፍትና ምንጮች ቀኖናት በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ገጽ 50-51.

[186] Hans von Campenhnusen, the Fathers of the Church, 21 Gonzalez Jutol, The Sstory of Christianity volume I 64.

[187] Epistle of Ignatiusto the Philadelphian Chap. IV, 81.

[188] The Epistle of Cyprian to the Lapsed, Epistle XXVI and Concerning the Baptism of Heretics, Epistle LXXII

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ቀኖናዎችና የቀኖና ምንጮች በአብዛኛው አትኩሮት የሰጡበት ስለ ከህነት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት፣ ስለ ጳጳሳት የሥራ ከፍፍልና ደረጃ፣ ስለ ካህናትና ዲያቆናት የሥ ልጣን አሰጣጥ፣ አጠቃቀምና ስላለባቸው ኃላፊነት የሚያብራሩ ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ ከህነቱን በደፈናው እንጠቀምበታለን እንጂ ማን ምን እንደሚሠራና ምን ኃላፊነት እን ዳለበት በትክክል ተረድተን በቀኖናው እየተመራን ሳይሆን የዘበፈ ቀደ ዓይነት ሥራ የምንሠራ ነን።

ቤተ ክርስቲያኒቱ የተቀበለችውን ቀኖናዊ የሥልጣነ ከህነት ውክል ናና አጠቃቀም፥ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት መሆኑን፥ መመ ርመርና ማጥናት ይጠቅማል። ከዚህ አንጻር በዚህ መጽሐፍ አት ኩሮት በመስጠት የቀረበው ማብራሪያ፣ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጠበቅ የቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነት መሆኑን ከማሳየቱም በላይ፤ ስለ ጵጵስና ሥልጣን አስ ፈላጊነትና ኃላፊነትም በቂ እውቀት እንዲኖረን የሚያደርግ ነው።

ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ያስፈልጋታል ሲባል፣ ምን ማለት እንደሆነ ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ ያለ ውን ትውፊታዊ ቀኖናና ሥርዓት እንመረምራለን። ከዚህም እነ ዚያ የጥንት አባቶች ባሠመሩልን (በሠሩልን) ቀኖና ሂደን ከሆነ እንድንቀጥል፤ ያንን አልተከተልን ከሆነ ራሳችንን እንድንመረም ርና እንድንታረም ያስችለናል ማለት ነው። ከላይ እንደ ተገለ ጸው፣ የቀኖናውን አስፈላጊነትና ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ጥቅም ከብደት ለመመልከት ከዚህ በታች የተጠቆሙትን ነጥቦች በጥንቃቄ በመመልከት የቀኖናውን ዓላማ መረዳት ያስፈልጋል።

3. <u>የቀኖና ዓላማ፤</u>

ቀኖና ማለት ሕግ፣ መመሪያ፣[189] አንድን ነገር እንዳንጨምር፥ እንዳንቀንስ የሚያደርግ መንፈሳዊ የመስተዳድር ሕግ መሆኑን ቀደም ሲል ከላይ ገልጸናል።[190] በዚህም መሠረት ቀኖና እንዲሠራ ወይም እንዲጸፍ የሆነበት ዓላማ ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የዘመኑ ውስብስብ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታ፣
ለ/ የእምነቱ ብዛትና የአስተምህሮ ልዩነቶች፣
ሐ/ ከርስትና የተመሠረተበት ትምህርትና የሕዝቡ ግንዛቤ።

ሀ/ <u>የዘመኑ ውስብስብ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታ፤</u>

እንደ ዛሬው ሁሉ ያን ጊዜም ቤተ ክርስቲያን ክርስትናን እንዳታስተምር ወይም የክርስትናን እውነት በትክክል ማስተላለፍ እንዳትችል ዝብርቅርቅ ያለ ዘመን ነበር። የዘመኑ ውጥረት አንደኛውና ዋናው የሮማ አስተዳደር የፈቀደው የልዩ ልዩ የእምነት ነጻነት ነበር።[191] በተለይም የሩቅ ምሥራቅ መንፈሳዊነትና የአይሁድ ተቃውሞ፥ እንዲሁም የሮማ የጣዖት አምልኮ፥ ሦስቱም በየበኩላቸው ያደርጉት የነበረው ጫና፣ ቤተ ክርስቲያን እውነት የሆነውን ነገር እንዳታስተላልፍ እንቅፋት ሁኗት ነበር።[192]

---

[189] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 እና 10ን ይመልከቱ።
[190] ዝኒ ከማሁ
[191] Gonzalez Jutol, The Story of Christianity volume I 51-53.
[192] Ibid

ለዚህ ማስረጃ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ያሰፈረውን ቀጥሎ መመልከት ይጠቅማል።

"ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ አንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን አንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ አንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ አንለምናለን። አርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም አርሱንም የኃጢአት ን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን። አርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታ ዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥ ሮአል"። [193]

ይህ ቃል አሁን ላይ ሁነን ለምንመለከተው ችግር ያለው አይመስልም፣ በዚያ ዘመን ግን ይህ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ቤተ ክርስቲያንን ያወከ ትምህርት ነበር። ስለ ሆነም ሐዋርያ በዚህ ምንባብ ውስጥ የክርስቶስን አምላክነት ለካዱ፣ ነገር ግን ደግሞ ክርስቶስን ከአምላክነት ዝቅ አድርገው ለተቀበሉና የእነሱን ጥበብና ዕውቀት የመዳኛ መንገድ አድርገው ለያዙ፣ ነገር ግን ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን ለተባሉ አማኞች ነበር የጻፈው።[194] ከዚህ የከፋው ደግሞ የአይሁድ በሕግ እንድናለን አከራሪነት

---

[193] ቆላ 1፡ 9-13
[194] Harold O.J.Brown,Hheresies. P. 56

ተጨምሮበት ስለ ነበር፥ ቤተ ክርስቲያን እውነት የሆነውን ነገር ለመያዝና ለማስተማር ግራ ተጋብታ ነበር።[195]

ከዚህ ውጥረት ወጥቶ ትክክለኛ አቅጣጫ በመያዝ በሁሉም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ትኖር ዘንድ፣ የስህተት ትምህርቱን ሁሉ የሚቋቋም ቀኖናዊ እምነት ወይም ከዚህ አትለፍ ከዚህ አትጨምር የሚል ሕግ ቀኖናን መሠረት አድርጎ መወሰንና መቀነን ያስፈ ልግ ነበር።[196] ይህንን እንዲወስኑ ያደረጋቸውን ሁኔታ ለመገንዘብ ምሳሌ እንዲሆነን በመጀመሪያው የክርስትና ዘመን የነበረውን የእምነት ፍልስፍና ማየት ያስፈልጋል። በዚያ ዘመን ከነበሩት አማኞች መካከል ይከተሉት የነበረው የእምነት አመለካከት በአንዱ ታላቅ አምላክ ሥር የተለያዩ ንዑሳን አምላኮች አሉ። የሚል ነበር።

ከነዚህም ሁለቱ አምላኮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከነዚህም አንደኛው፤ ክፉ ሌላኛው ደግሞ መልካም/ደግ ነው፤[197] በተለይም የአዲስ ኪዳኑ አምላክ መልካም ሲሆን፤ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ ጨካኝና ክፉ አምላክ ነው፣ በማለት ለራሳቸው የሚስማሙ መጻሕፍትን መርጠው እውነተኛ የክርስትና ማስተማሪያና የቀኖና መጻሕፍት እነዚህ ናቸው፣ በማለት የደጉ አምላክ ማስተማሪያ አድርገው ማቅረባቸው ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አደጋ ነበር።[198] ከዚህ አደገኛ ትምህርትና የእምነት ማስተማሪያ ተብሎ የተዘጋጁ፣ የተሳሳቱ መጻሕፍትን ለማረምና ከስህተትም ለመዳን <u>አንድ</u>

[195] *Brucel.Shelley, Church History In plain language, pp. 62-63*
[196] *Irenaes Against Heresies Book, III, I.2*
[197] *Harold O.J.Brown, Heresies.47*
[198] *Ibid, 49-54*

የእምነት መግለጫ፣ <u>ሁለት</u> የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር መቀነን/መዘርዘር/ አስፈላጊ ነበር። በዚህም ዙሪያ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ አባቶችን ቀጥለን እንመልከት።

1/ <u>ሄሬኔሬዎስ፤</u> የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት ከሐዋርያት ቀጥሎ ለመጀመርያ ጊዜ ግልጽ የሆነ የእምነት የአቋም መግለጫ አወጣ።[199] የሄሬኔዎስ የመጻሕፍት ዝርዝር አሁን እንደ ያዝነው የመጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝር ተራ ቍጥር ጠብቆ አይደለም፤ በዚያ ፈንታ የጸሐፊውን ስም ከነከብሩ በመጥራት ሐዋርያቱ በጎበረትና በግል መጀመሪያ በቃል በኋላም በመጽሐፍ ደረጃ እንዳስተላለፉ ይተርካል ።[200]

ቅዱስ ማርቆስ በጴጥሮስ የተሰበከውን ወንጌል አንደ አስተርጓሚ በመሆን የጻፈውን ወንጌል፥ ቅዱስ ሉቃስም በስሙ የተጠራውን ወንጌል በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቷል። ዮሐንስም በሚኖርበት በኤፌሶን ሁኖ ወንጌሉን ጽፏል፤ ጳወሎስም ላስተማራቸው ምእመናን በጽሑፍ አስተላልፏል። እነዚህን ሕግጋተ መጻሕፍትንና ነቢያትን፣ ያወጁልንን በሙሉ፤ ሁሉን የፈጠረ፣ የሚታየውንና የማይታየውን፥ ሰማይና ምድሩን የፈጠረ አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን በማስረገጥ፣ የእምነቱን መግልጫ ሲያወጣ፥ ለዚህ እምነት ምስክር የሚሆኑ፣ የቀኖና መጻሕፍትን ስም ዝርዝር፣ ከላይ በገለጥነው መልክ ጨምሮ አወጣ።[201] ሄሬኔዎስ ለእግዚ አብሔር ህልውናና ለመዳናችን ምስክር አድርጎ ያቀረበው በሐ

[199] *Ibid, 55*
[200] *Irenaes Against Heresies Book, III, I. 1*
[201] *Ibid. I.2*

ዋርያቱ የተጻፉትን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትንና በከርስቶስ የተ መሰከረላቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው።

2/ <u>ቀሌምንጦስ፤</u> የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት ደግሞ ቤተ ክርስ ቲያንን ከእንደዚህ ዓይነት የውሸንብርና የውጥረት ዘመን ጠብቆ ነጻ ማውጣት የሚቻለው የጵጵስና ሥልጣን ሲከበር ወይም ሲኖ ዶሳዊ ሥልጣን ሲኖር ብቻ ነው በማለት፥ በሁሉም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን፥ አንድ እምነት የምታምን፥ አንድ ዓይነት ቅዱሳት መጻሕፍትን የምታነብ፣ በአንድ ዓይነት የጸሎት መጻሕፍት የምት ጸልይ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምታንጸባርቅ ናት፣ በማለት ይህች ቤተ ክርስቲያንም ተጠብቃ እንድትኖር አስተማረ።[202] የጵ ጵስና ሥልጣንና ኃላፊነትን የሚገልጥ ቀኖናዊ ሕግም አወጣ።

ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህንን በመከተል ከሐዋርያት ተያይዞ ከመጣው ትውፊት እንዳይዛቡ፣ ቀኖናዊ ትምህርትን እየተቀበሉና እያስተላለፉ ቤተ ክርስቲያንን ከአደጋ አተረፉ።[203] ስለዚህ የቀኖና ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን ከአደጋ ለማዳንና አስተዳደራዊና ማኅበራዊ ሥርዓትን በማስያዝ ለመጠበቅ ነው።[204]

ለ/ <u>የእምነቱ ብዛትና የአስተምህሮ ልዩነት፤</u>

ከላይ እንደ ተገለጠው ክርስትና የመጽሐፍ እምነት ስለ ሆነ ቤተ

[202] *The first Epistle of Clement,Chapc XLII,XLIII,XLIV,XLV*
[203] *Justin Martyr, The First and Second Apologies, pp. 18-20, Iraneus Against Heresies books II & III. 2*
[204] *See foot note 11*

ክርስቲያን ትምህርቷ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተስማምቷል ወይ ወይም የእግዚአብሔር አስትንፋስ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነበረባት። ስለ ሆነም ከላይ የተዘረዘሩት የስህተት ትምህርቶች ሰርገው እንዳይ ገቡ ለመጠበቅ፣ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የእግዚአብሔር አስ ትንፋስ ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ እንዳይሆን፣ ከአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ጀምሮ ለቀጣዮቹ ሁለት መቶ ዓመታት የቤተ ክር ስቲያን አባቶች የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል።[205]

<u>አንደኛው</u> ዘዴ፣ መንፈሳዊ ሐረገ ትውልድ ነው።[206] ይህም ማለት አያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባት፣ ከየትኛው ሐዋርያ ነው የተማ ረው? የየትኛው ሐዋርያ ደቀ መዝሙር ነው? በማለት፤ ያልተገ ለጠ የምሥጢር ሃይማኖት አለ፥ ከሚለው የስህተት ትምህርት ለመዳን፣ እግዚአብሔር ያልገለጠው የተሰወረ ነገር የለም። እግዚ አብሔር ለሐዋርያቱ ሰጥቷል፤ ሐዋርያቱም ለኛ አስተላልፈዋል።[207] ይህም እኛ የተቀበልነው ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት የተረ ጋገጠ ስለ ሆነ ሌላ የምሥጢር እምነት የለም በማለት ተከላከለ ዋል።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ይህንን እውነተኛ ትምህርት ሕጋዊ ከህነት የተቀበሉ እውነተኛ ጳጳሳት ብቻ እንዲያስተምሩ፣ የተፈቀደላቸውም ጳጳሳት በጠቅላላዋ በዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ዕውቅና ያገኙ መሆን

[205] *Iraneus Against Heresies book III&.II.2*
[206] *Ibid, Chap III. 3*
[207] *Ibid*

እንዳለበት የሚያስረዳ የቀኖና ስሪት ያስፈልግ ነበር። [208] ይህ ቀኖና ከስህተቱ ትምህርት ቤተ ክርስቲያንን ነጻ እንድትሆንና ስህ ተቱን እንድታወግዝ ረድቷታል።

ሐ/ ክርስትና የተመሠረተበት ትምህርትና የሕዝቡ ግን ዘቤ፤

ክርስትና በእግዚአብሔር ቸርነት ለሰው የተሰጠ ወይም የተመሠ ረተ ስለ ሆነ እግዚአብሔር የሰጠውን እውነት ብቻ ማጥናት፣ እሱ ንም መጠበቅና በትምህርቱም መኖር ነው እንጂ።[209] በሰው ጥበብ ሊሻሻል፣ ሊጨመርበት ወይም ሊቀነስበት አይችልም።[210] [211] የመ ጀመሪያዎቹ ሦስት መቶዎቹ ዓመታት ችግር ክርስትናን ከሰው ሠራሹ ፍልስፍና ጋር በመደባለቅ እውነቱን ግራ ማጋባት ነበር። [212] ይህ የተሳሳተ ትምህርት ሥር እንዳይሰድና ቤተ ክርስቲያንን እንዳያሳስት ቀኖና አስፈላጊ ነበር።

ስለዚህ የቀኖና መንሥኤና ዓለማ ሲጠቃለል እግዚአ ብሔር የሰ ጠው የማዳን ሥራ በትክክል ሳይዛባ ለሰው እንዲደርስ፣ ሰውም በማይድንበት መንገድ እንዳይሄድና የእግዚአብሔር ሐሳብ በትክ ክል እንዲከናወን ለማድረግ፣ የተደረገ ሥርዓትና መመሪያ ነው። በመሆኑም ቀኖና፣ ቤተ ክርስቲያንን ከጥፋት አድኖ አሁን እስካ ለንበት ጊዜ እንድትደርስ ያደረገ፣ ቤተ ክርስቲያንን ከቀውስና

[208] *Ibid*
[209] *Ibid,V.1*
[210] *Ibid IV.2*
[211] *Ibid,V.1*
[212] *Ibid V.3*

ከመበታተን የታደገ፣ መመሪያ ሕግ ነው። [213] ቤተ ክርስቲያን እንደመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት በቀኖናና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ብትመራ ኖሮ፣ አሁን የሚታየው የተከፋፈለ ቤተ ክርስቲያን አይኖርም ነበር። ይህ የቀኖና ሥርዓትና ዓላማ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲሁም ቀኖናው ምን ያህል ሚና እንደተጫወተ በሥራ ላይ እንዲውል፥ ሕግ አስከባሪነትንና ኃላፊነትን ማን እንደ ወሰደ ወደሚያስተምረውና የጥናታችን ዋና ማዕከል ወደ ሆነው ምሥጢረ ከህነትን በጥልቀት ለመረዳት ወደ ተጻፈበት ወደ ክፍል ሦስት እንገባለን።

[213] See foot note 11.

ክፍል ሦስት፤

የምሥጢረ ክህነት ችግሮችና ቀኖናው የሰጠው መፍትሔ

በክርስቶስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን አሁን ካለችበት ደረጃ አንዲህ ባለ መልኩ የደረሰችው፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን ካስተማራቸው በኋላ፤ እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝቦች ሄዳችሁ የነገርኳችሁን አስተምሩ፤ ባላቸው መሠረት ትእ ዛዙን ተቀብለው፣ ዓለምን ዙረው፣ አስተምረው፣ የታዘዙትንም ፈጽመው፣ በማለፋቸው ነው።

የሐዋርያት ተተኪዎች የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጳጳሳት፣ ካህናትና ዲያቆናት ይህንኑ የጌታችንን ቃል ተቀብለው፣ ምእመናንን በማገልገል ላይ ስለሚገኙ፣ ይኸው የቤተ ክርስቲያን ሥራ ቀጣይነት ከእኛ ደርሷል። አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ይህ ሕግ በትክክል በሥራ ላይ አለመዋሉን፣ በተግባር እየተመለከትነው ነው። በዚህ ክፍል ምሥጢረ ክህነት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መጠበቁን መሠረት ያደረገ ማብራሪያ ይቀርባል።

1. የቤተ ክርስቲያን አንድነትና ምሥጢረ ክህነት፤

ምሥጢረ ክህነት ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት በልዩ ጥሪ የሚገኝ

ሥልጣን ነው።[214] ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ አቋምና ታማኝነት፣ ጤናማ እድገትና ጤናማ አስተዳደር ይኖራት ዘንድ፥ ምሥጢረ ክህነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው።[215] ቤተ ክርስቲያንንም በባለቤትነት የሚመራት ይኸው ከእግዚአብ ሔር የተሰጣት ታላቅ ስጦታ ሥልጣነ ክህነት ነው። በመሆኑም የሥልጣን ተዋረዱንና አንድ ካህን የክህነትን ሥራ ለመሥራት እንዴት ተመርጦ እንደሚመደብ ምን መለኪያም እንደሚያስፈ ልገው እንመለከታልን።[216]

በሥልጣን ተዋረዱ ከታች ወደ ላይ ሲቆጠር፣ ዲያቆን፥ ቄስ፥ ኤጲ ስቆጶስ ወይም ጳጳስ በመባል ይታወቃል።[217] የጵጵስና የሥልጣን ምንጭ ቅዱስ ሲኖዶስ ሲሆን፣ የቅስናና የዲቁና የሥልጣን ምንጭ ግን ጵጵስና ነው። በዚሁ መሠረት አስቀድመን የምንመለከተው የምሥጢረ ክህነት ሥልጣን ምንጭ የሆነውን የጵጵስናን የሥል ጣን አመጣጥና አሿሿም ሥርዓት ነው።

የጵጵስና ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በቀኖና ቤተ ክርስቲ ያን ጥናትና በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ታሪክ መሠረት፣ ኤጲስ ቆጶስነት ወይም ሥልጣነ ጵጵስና ለቤተ ክርስቲያን የሥራ

[214] ማቴ 10 ፥ 1-15

[215] ማቴ 10፡ 1-15

[216] Joseph Cardinal Ratzinger,Called to Communion Undertanding the Church Today, p. 50; ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ፤

[217] ዝኒ ከማሁ

አመራርና አፈጻጸም የመጨረሻውና ትልቁ ነው።[218] የድጅስና ሥልጣን ለቤተ ክርስቲያን አንድነት፣ ጥንካሬ፥ ወጥነትና አቋም ወሳኝ ነት አለው።[219] በዚህም መሠረት ከአሿሿሙ ጀምሮ የሥልጣኑን አጠቃቀም፣ የሥራውን ሂደት፣ በሥልጣን የሚቆይበትን ጊዜ፣ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት የሰጠውን ጠቀሜታ፣ በተለያዩ ርእሶች መነሻነት የቀረበውን ዝርዝር ማብራሪ ቀጥሎ መመልከት እንችላለን።

1.1. <u>ሥርዓተ ሢመት፤</u>

ጵጵስናን ከቅስናና ከዲቁና ሥልጣን የሚለየው፣ ሹመቱ በአንድ ጳጳስ ብቻ አይካሄድም።[220] በሌላ አነጋገር የኤጲስ ቆጶስነት የሥልጣን ምንጭ ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ ነው።[221] እንዲሁም አንድ ጳጳስ ሲሾም የምእመናን፥ የካህናት ተወካዮች እንዲገኙ፣ ከመሆናቸውም በላይ ቢያንስ ከሦስት በላይ ሊቃነ ጳጳሳት መገኘት ይኖርባቸዋል። ስለ ኤጲስቆጶስ አሿሿም በፍትሐ ነገሥት የተቀመጠው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ይላል፤

"ኤጲስቆጶስ በዕለተ እሑድ ይሾም፤ በሚሾምበት ቀን ሰዎች ሁሉ ይገኙ። ሕዝብና ካህናት መስክረውለት ይሾም። እጃቸውን በእርሱ ላይ ሊያኖሩ የመጡ ኤጲስቆጶሳትም እጃቸውን ይታጠቡ፤ ከዚያ በኋላም ይሹሙት። ሕዝቡም በፍርሃትና በጸጥታ ቁመው እጃቸውን ያንሡ፤ ኤጲስቆጶሳቱም፥ እኛ በዚህ በተመረጠ በእግዚአብሔር ባሪያ ላይ እጃችንን እናስቀምጣለን፤ እያሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ሰም እጃቸውን ያስቀምጡ። ነውር በሌለባትና አንዲት በሆነች በማይገለጥ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በጸናች ሥርዓት ይጸና ዘንድ፣ የቀና ፍርድን ለመፍረድ ምሰጋናን ለመግለጥ ልጅነትን ለማሰጠት ለታመነች ትምህርት፣ ይሻውም ነገረ መስቀልን ለማስተማር ከሥሉስ ቅዱስ ዘንድ በጉባኤ ለቤተ ክርስቲያን የተሾመ ነው፤ ከዚህም በኋላ ከነርሱ ቀዳሚ የሆነው ኤጲስቆጶስ እጁን ይጫንበት። የሹመቱንም ጸሎት ያድርስ ሕዝቡም አሜን፥ ይበሉ።"[222]

ይህም የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ፍትሐ ነገሥት በምንለው መጽሐፍ ላይ የተዘገበ የቤተ ክርስቲያን መመሪያና ሥርዓት ነው። ከላይ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተዘረዘሩት የኤጲስ ቆጶስነት አሿሿምን ሥርዓት በአትኩሮት ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ነጥቦች እናገኛለን።

<u>አንደኛ</u>፣ተሿሚው በሚያገለግለው ሕዝብ የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት ብቃቱን ምስክርነት ማግኘት አለበት።[223]
<u>ሁለተኛ</u>፣ በሚያገለግለው ሕዝብ ፊት ሹመቱ መካሄድ አለበት። የተሾመው የእግዚአብሔር ባሪያ ሁኖ በሥላሴ ፈቃድ በባሕርዩ

---

[218] *Cardinal Ratzinger, Called to Communion Undertanding the Church Today, p. 75.*
[219] *Richard R. Gaillardietz, By What Authority, A Primer on Scripture,the ?Magisterium and the Sense of the Faithful, p. 57*
[220] Ibid pp. 60-72
[221] Ibid

[222] ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ ፥ አንቀጽ አምስት ቍጥር 101

[223] ዝኒ ከማሁ ቍጥር 52

ስውር ለሆነው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንዲሆን ነው።

ሦስተኛ፣ ሹመቱ የነገረ መስቀሉን የማዳን ኃይል በሁሉም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ማስተማር ነው።[224] በመጨረሻ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ አባት ሁኖ ነው የተሾመው። [225] ከዚህ በላይ ያየነው አንቀጽ አንድ ኤጲስቆጶስ በሚሾምበት ጊዜ የሚከናወነውን ሥርዓት የሚመለከት ነው። ስለ ጧሚዎቹ የሚናገረው ትእዛዝ በዚሁ አንቀጽ እንዲህ ይላል፤

"ኤጲስቆጶስ ከሌላ ሀገር ሳይመጣ ኤጲስ ቆጶስ ለይሾም፣ እርሱ ብቻ ለይደለም ሌሎች ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ከእርሱ ጋር ይኑሩ። በሦስት ኤጲስቆጶሳት ይሾም። እንደዚህ ይሾም፣ በራሱ ላይ ወንጌልን ተሸክመው የበለጠው ኤጲስቆጶስ እንደዚህ ይጸልይ። ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ እጁን ይጫንበት ይሳመውም። መንፈስ ቅዱስን ይመላበት ዘንድ በፊቱ እፍ ይበልበት። ከዚህ በኋላ የቀሩት ካህናት እጅ ይንሡት። ሕዝቡ ግን እጁን ይሳሙት። ከኤጲስ ቆጶሳቱና ከቀሳውስቱ በቀር አፉን ለይሳሙት። ከዚህ በኋላ ቅዳሴውን ይፈጽሙ። [226]

ይህ አንቀጽም የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባውና አሿሿሙም ልዩ መሆኑን የሚያስረዳ አንቀጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቀጥሎ ባለው አንቀጽ ምናልባት የችግር ዘመን ቢሆን ሁለት ኤጲስቆጶሳት የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት መሾም

[224] ዝኒ ከማሁ ቀኖር 51
[225] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 5.
[226] ፍትሐ ነገሥት ለአንቀጽ አምስት ቀኖር 104 ገጽ 43

የሚችሉ ሲሆንና ቤተ ክርስቲያንን የሚወክሉ ሲሆን፣ አንድ ኤጲስ ቆጶስ ግን ብቻውን አንዲትን ቤተ ክርስቲያን ገንጥሎ የጵጵስና ሥራ መሥራትና ከህነት መስጠት፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መፈተት አይ ችልም።[227] የሱ ጵጵስና ከሌላው ጋር በመሆን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለመጠበቅ እንጂ ከአንድነቱ (ከጉባዔው) ከተለየ ወዲያው በተለየበት ሰዓት የጵጵስና ሥልጣኑን አጥቷል።[228] ምክንያቱም ከሁለት በላይ የጵጵስናውን ሹመት እንደ ሾሙ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንንም ሊወክሉ የሚችሉት ከሁለት በላይ ሲሆኑ ብቻ ነው።[229] ቃለ መሐላውን ሲፈጽም የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አስጠብቃለሁ በእምነቷና በሥርዓቷ እሄዳለሁ ብሎ ስለ ሆነ፣ ከዚያ ሲወጣ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ካደ ተቆጥሮ ከህነቱ እንዳይሠራ ይሆናል።[230]

ከዚህ አንጻር የአባ ጳውሎስ የፕትርክና ሥልጣን ሕጋዊነት ሲታይ በየትኛውም ሚዛን ቢለካ ሕገ ወጥ ነው። በተጨማሪ እሳቸው ሲኖዶሱን ከደው፣ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ማቋቋማቸውና የሲኖዶስ አባል አይደለሁም፤ ማለታቸው ሌላው የሕገ ወጥነት መገለጫ ነው።

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ይህንን አንቀጽ በትክክል ያልተረዳች ቤተ ክርስቲያን፣ ኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስ

[227] ዝኒ ከማሁ 105
[228] ዝኒ ከማሁ
[229] *The Aopostolic canon* Canon, XXXI, XXXII
[230] Ibid John H.Erickson,the Challenge of Our Past, p. 75; Alexander Bogolepov,Toward an American Orthodocs Church; The Establishment of an Autocephaolous Orthodox Church, p. 24

ቲያን ነኝ ብላ ልትናገር አትችልም፤ እግዚአብሔር ከመለኮታዊ ፍቅሩ የተነሣ የሰጣትንም የጸጋ ስጦታ ለመረዳት ትቸገራለች፤ የአሁኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ችግር ይህን በትክክል አለመረዳትና በዚህም ሥርዓት ውስጥ አለመኖር ነው።[231] በዚህ መሠረት የተወሰነ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ ጵጵስና በቤተ ክርስቲያን ምን ቦታ እንዳለው የሚከተሉትን ከሥራው ጋር የተያያዙትን ገላጭ ስሞችን ወይም ተጨማሪ መጠሪያ ስሞችንና የሥልጣን ደረጃዎችን እንመለከታለን።

1.2. ጵጵስና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት መሠረት ነው፤

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ የአንድነት ምልክቷ ክርስቶስን የወከለው መሪው ነው። [232] ለምሳሌ በሐዋርያት ዘመን ብንመለከት፣ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሐዋርያ ሥር ወይም በአንድ ክህነታዊ አመራር ውስጥ ካልሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን አይቆጠርም ነበር። በዚያ ዘመን ሐዋርያ ይባል የነበረው አሁን ጳጳስ በሚለው ተተክቷል። ስለሆነም ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ እንኳ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባት ወይም ሐዋርያ ችግሩን ይዞ ወደ እናት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ

[231] የገለልተኛውንና የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ ከርከር መመልከት በቂ ነው። ለዚህ ማስረጃ የአባ ጳውሎስ የምርጫ ሂደት የተጻፈበት ዜና መዋዕላቸውን የዘረዘረው መጽሐፍ በቂ ማስረጃ ነው። ከዚህ በተጨማሪ "የማይገለጥ የተከደነ የለም" በሚል ርእስ ከሕጋዊው ሲኖዶስ ለሕገ ወጡ የወያኔ ሲኖዶስ የተሰጠ መልስ የሚለውን መጽሐፍ ከገጽ 55-75 መመለት ይጠቅማል።

[232] ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር 54፡ ፍትሐ ነገሥት ገጽ 31.

ችግሩን ያቃልል እንደ ነበር የሐዋርያት ሥራ ጉባኤ ማረጋገጫ ነው።[233]

የተጠቀሰው ውሳኔ፣ በሮምና በሌሎች አሕዛብ አገሮች የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፣ የነበረባትን ችግር ለእናት ቤተ ክርስቲያን ወይም ለኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን በማቅረብ ችግሩ እንደ ተፈታ ያስረዳል። ከዚያም ጳውሎስና ሲላስን የአንድነት ምልክት የሆነውን ቀኝ እጃቸውን በመስጠት ለሐዋርያነት አገልግሎት እንደ ላኳቸው በገላትያ [234] ተጠቅሷል። ከዚህም በመነሣት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ጌታ ሥልጣን በሰጣቸው [235] በሐዋርያት ፈቃድና፥ የነሱ ተከታይ በነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም የጵጵስና ሥልጣን ሥር ትመራ እንደ ነበር፣ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና መጻሕፍትና የነገረ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል።[236]

ይህንን መሠረት በማድረግ፣ ክርስቶስን የወከለውና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዲመራ፣ የተመደበው ጳጳስ ሳይፈቅድና ወይም ያለሱ ይሁንታ ቤተ ክርስቲያን ማቋቋም እና አገልገሎት መስጠት የተወገዘና ክህደት መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ሲገልጽ፤

[233] የሐዋ 15: 19.
[234] ገላ 2: 8-10
[235] ማቴ 10: 1-15.
[236] St.Cyprian of Carthage the Unity of the Cathoilc Church, the Faith of the Early Fathers, p. 219

"ያለ ኤጲስቆጶሱ ትእዛዝ ቤተ ክርስቲያንን አይሥሩ፤ አንድ ሰው ሰንኳ ደፍሮ ከዚህ ውጭ ቢሠራ በውስጧ አሰከ ዘላለም ቍርባን አይቅረብ፤ ቄሱም ይህንን ተላልፎ ቍርባንን ቢቈርብ ይሻር"።[237]

ይህ ማለት አንዲቷን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለማስተዳደርና ለመምራት ለቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና መብት ካለው ጳጳስ ፈቃድ ውጭ ቤተ ክርስቲያንን መሥራትና አገልግሎት መስጠት ከህደትና መናፍቅነት ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መከፈል ነው።*[238]

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንድ ካህን፣ ከህነትን የሚያገኘው ከጳጳስ እንደ መሆኑ መጠን ከህነቱን የሰጠው ጳጳስ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ወክሎ በዚያ ከህነት አንዲሠራ በቤተ ክርስቲያን ካልመደበው በቀር፣ ያለጳጳስ ፈቃድ በራሱ መብት በከህነቱ የሚያገለግል ከሆነ፥ ምሥጢረ ከህነትን፣ በመስረቅ ለራሱ ሥጋዊ ጥቅም ስላዋለ፣ በቤተ ክርስቲያን ትልቅ ወንጀል ነው።[239] ለዚህ ነው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፥ ያለ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያን የለችም፥ ያለቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የለም ያለችው።[240]

ይህም የሚያመለክተው፣ ጳጳስም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን የዕውቀትና የሥነ ምግባር ብቃትና ችሎታው ተመስክሮለት ድጽስና ካልተሰጠው፣ የአንድነቱ አባል እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን ካልፈቀ

---

[237] ፍትሐ ነገሥት፣ ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አንድ ቍጥር 2፡ ገጽ 21.
[238] ዝኒ ከማሁ* በአንቀጽ ሦት የተጠቀሱት በሙሉ ቤተ ክርስቲያን ሰትቋቋም የሚደረጉ ትእዛዛትን ያጠቃለለ ነው፤ የንዋያተ ቅድሳቱ ምንነትም በሙሉ ተዘርዝረዋል።
[239] ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ሰድሰት ቍጥር 213፡ፍትሐ ነገሥት ገጽ 71

[240] ትምህርተ ዲዲስቅሊያ ዘአበው፤ 16

ደችለት /ጳጳሳቱ ካልፈቀዱለት/ ጳጳስ ሊሆን አይችልም።[241] የሁለቱ አንድነት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ይገልጣል። በዚህም ምክንያት በእያንዳንዱ ከተማ አንድ ጳጳስ አለ፤ እያንዳንዱ ጳጳስ ከሌላው ጳጳስ ጋር በመሆን ቤተ ክርስቲያንን ይገልጣሉ። በዚህ መሠረት፣ አንደኛው ጳጳስ የተመደበበትን ቤተ ክርስቲያን ወይም ከተማ ካልወከለ ጳጳስ ሊሆን ይችልም።[242] በሌላ ቃል ብናስቀምጠው ድጽስናው በሲኖዶስ ምልዐተ ጉባኤ ታውቆ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመራ ቦታ ካልተሰጠው የድጽስናው ሥልጣን አይሠራም ማለት ነው።

ለምሳሌ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አራት መንበሮች የነበሯት ሲሆን፤ እያንዳንዳቸው ያሉበት ዋና ከተማ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ፤ ይህም ማለት የሮሙን ዓለም የሚያስተዳድረው የሮሙ ሊቀጳጳስ (ፓትርያርክ) የሮም ከተማ ሊቀ ጳጳስ ነው። የእስያን ሀገሮች የሚያስተዳድረው የኤፌሶኑ ሊቀ ጳጳስ የኤፌሶን ከተማ ሊቀ ጳጳስ ነው። አፍሪካን የሚያስተዳድረው የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ፣ የእስክንድርያ ከተማ ሊቀ ጳጳስ ነው።[243] በዚህ አንጻር የኢየሩሳሌሙም፣ የቊስጥንጥንያውም የየራሳቸው ከተማ ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ።

በዚህ መሠረት የራሳቸውን ሀገረ ስብከት የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ ይዘው በየሀገረ ስብከታቸው ሥር ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስቆጶሳት ሰብሳቢ ሁነው አንዲቷን የእግዚአብሔርን ቤተ

---

[241] The Apostolic Canon, Canon I ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር 57.
[242] ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር 40 ገጽ 28. Richard R. Gaillardetz, By What Authority, p. 68
[243] ዝኒ ከማሁ ቍጥር 42 Ibid, p. 69

ክርስቲያን ይገልጣሉ።[244] ይህ አንድነት የሚገኘውና ሊገኝ የሚችለው በጵጵና ሥልጣን ብቻ ነው። ለእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና ጳጳስ ሊሾም የሚችለው፥ ይኸው በዋና ዋና ከተሞች የተሾሙት ሊቃነ ጳጳሳት የሚሰበሰቡት ቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ነው።[245] ለዚህ ነው ጳጳስ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት መሠረት ነው፤ የተባለው።[246]

ከላይ የገለጥናቸው የሊቃነ ጳጳሳት መናብርት አንዱ በሌላኛው የታወቀና ራሱን የቻለ ቤተ ክርስቲያን ከላይ ማንም ሳይኖርበት ራሱን በራሱ የሚያስተዳደር ምሉዕ ማለት ነው።[247] ሁኖም ግን አሁን በኢትዮጵያ የሚታየው የፖለቲከኞች ገለልተኛ ነን ባይነት ትክክል እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም ምሉዕ ሲኖዶስ እያላት እንኳ ገለልተኛ የሚለውን ስም አልወሰደችም፣ አልተጠቀመችም ነበርና። ቤተ ክርስቲያን ከሕጋዊ የከህነት ውክልና እና ከትውፊታዊ ሲኖዶሳዊ ሥልጣን ተለይታ ቤተ ክርስቲያን ልትሆን አትችልም።[248] ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን የሚያስኛት ይኸው ሥልጣን ነውና።

ይህን ሐሳብ ከቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ብንጀምር የትንሣኤው የዓይን ምስክር ያልነበሩ ሰዎች በልዩ ጥሪ ካልሆነ በቀር የሐዋርያት አሠረ

[244] ዝኒ ከማሁ ቊጥር 43፡ Ibid , pp. 69-70
[245] The Apostolic Canon Canon I
[246] St. Irenaeus of Oyons, On the Apostolic Preaching, Popular Patristics Series, pp. 1-5
[247] The Autsolos Church
[248] St. Justin Martyer, The First and Second Apologies, pp. 17-20

ሥልጣን የተያያዘ በሐዋርያዊ መንበር ሥር ሁኖ እውቅና ያላገኘ ጳጳስም ቤተ ክርስቲያንን ሊወክል አይችልም።[249] ለምሳሌ አንዲት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፣ ከህነታዊ ሥልጣኗ ከሐዋርያት መንበር በአንዱ ትውፊታዊ ግንኙት ከሌለው የክርስቶስን አካል ከምትወክለው ቤተ ክርስቲያን አንድነት ጎብረት አታደረግም፤ ከህነታዊ ሥልጣኗም እውቅና የለውም።

1.3. [redacted]

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች አዘውትረው የሚያገኟቸውና ሊያገኟቸው የሚገቡ <u>አራት</u> ትላልቅ ምሥጢራት ነበሩ። እነዚህም ከህነት፣ ጥምቀት፣ ንስሐና ቅዱስ ቊርባን ናቸው።[250] በተለይ ከህ ነት ከላይ በተዘረዘረው መሠረት፣ በቀኖና ተደንግጎ የሚካሄድ ሲሆን፤ ጥምቀት፣ ንስሐና ቊርባን ደግሞ በሲኖዶሱ ጉባኤ በተሾ ሙት ጳጳሳት አማካይነት የሚፈጸም ነበር።[251] የጥምቀት ስነ-ሥርዓት ለእያንዳንዱ አማኝ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ሲሆን፣ ቊርባንና ንስሐ ግን ክርስቲያኖች ሁልጊዜ የሚፈጽሙት የአንድ

[249] See foort not #15
[250] Archimandrit Meletios Webber, Bread & Water & Wine & Oil, 111-160* መጽሐፉ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ሰባቱ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን በመባል የሚታወቁትን ምሥጢ ራት በሰል ባለ መልኩ ተብራርቶ ቀርቦበታል። በሊቀ ጉባኤ አበራ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት በሚል የተጻፈ መጽሐፍ ተመሳሳይ ሐሳብ አለው፤ በመጽሐፉ ከገጽ 245-272 ይገኛል።
[251] Metropolitan D.Zizioulas Eucharist Bishop, Church, 45 ልዩ ማሳሰቢያ በዚህ ርእስ ውስጥ በብዛት የምንጠቀመው ይህን መጽሐፍ ስለ ሆነ ተመሳሳይ ወይም Ibid or Zizioulas በሚል አጠቀማለሁ; ሁኖም ገጹን ስለማስቀምጥ መጽሐፉን ማገኘት የቻለ ሰው ለማንበበ የሚቸገር ላይመስለኝም፤ ምክንያቱም በዚህ ርእስ ላይ ከፍተኛ ጥናት የተጠናበት መጽሐፍ ስለ ሆነ ነው።

ነታቸውና የህልውናቸው መሠረት ሁኖ ይቀጥል ነበር፤[252] በዚህም መሠረት የጳጳሱ ሥራ የቅዱስ ቊርባንን ሥርዓት የበላይ አለቃ ሁኖ መምራት ነው።[253]

ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ልትባል ትችል የነበረው በጳጳስ መሪነት የቅዱሰ ቊርባን ሥርዓት የሚካሄድበት ጉባኤ ሲሆን ብቻ ነበር።[254] ይህ በመሆኑም፣ የክርስቶስን ሥጋና ደሙን ከምስጋና መሥዋዕት በኋላ ለተሳታፊው ጉባኤ ለማደል ሥልጣን የነበረው ሊቀ ጳጳስ ብቻ ነበር።[255] በእያንዳንዱ ከተማ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በነበራት አንድ ጳጳስ አማካይነት የቅዱስ ቊርባንን ሥርዓት ታከናውናለች። ያ ጳጳስም ራሱ በሾማቸው፣ ካህናትና ዲያቆናት አማካይነት በመታገዝ የቅዱስ ቊርባንን ሥርዓት ያካሂዳል።[256] የዚች ጉባኤ አንድነት ቤተ ክርስቲያን ናት የክርቶስ አካል የሆነች ቤተ ክርስቲያን ትባል የነበረው።[257]

ይህ ሥርዓት አንድ ጳጳስ፥ አንድ መንበር፥ አንድ ቊርባን፥ አንድ እግዚአብሔር፥ የሚለውን ሥነ መለኮታዊ አስተምህሮ ይገልጣል

[252] *Ibid. 48*
[253] *Eucharist Bishop Church, 49; SusabK. Wood One Baptism Ecumenical Dimenstions of the Doctrine of Baptism, pp. 21-29*
[254] *Metropolitan John D.Zizioulas, The one and the many stusdies on God, Man, The Church,and the world today, p. 73.*

[255] *Ibid*
[256] *Ibid, 65*
[257] *Eucharist Bishoip Church, 53*

ተብሎ ይታመን ነበር።[258] እንደ አሁኑ ከህነቱን የሰጠው ጳጳስ እንኳ የማይታወቅ ቄስ፥ ካህን ነኝ ብሎ ቤተ ክርስቲያንን የግል እያደረገ እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ፥ ይህ ሥርዓት የጸና ነበር። ይህ ሥርዓት ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ዓመት የቀጠለ ሥርዓት ነበር።

እስከ ተወሰኑ መቶ ዓመታት ከቀጠለ በኋላ፥ ለእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ለእያንዳንዱ ከተማ ጳጳስ የማይዳረስ ሲሆን፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ለአስተዳደር ያመች ዘንድ እያንዳንዱ ጳጳስ፣ ካህናትንና ዲያቆናትን እያሠለጠነና እየሾመም፣ አገልግሎቱ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲካሄድ ተደረገ።[259] ያ ማለትም ጳጳሱ ያለ በት መንበር አለቃ የሆነው ጳጳስ በመንፈሳዊ ሥልጣኑ የዚያ መን በር ኃላፊ ነው የሚለውን የእምነት መርሕ በመያዝ ነበር።[260] ስለ ዚህ ቅዱስ ቊርባንን ለማከናወን ያንድ ቀን ቅዳሴም ቢሆን ያለ ጳጳስ ፈቃድና ቡራኬ ሊከናወን አይችልም።[261]

1.4. ጳጳስ የሃይማኖቱ ጠባቂ ነው፤

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ የተካሄዱ ጉባኤዎችን፥ የተቀነኑ ቀኖናዎችን፥ የተጻፉ

[258] *OrthodoxyToday.org.* Eucharist Bishop Church, p. 90; *ሐሳቡ የተወሰደው የሐዋርያት ቀኖና ቀኖና 14 ላይ ነው። የዚህ ትምህርት ምንጭ ግን ለእንበሳ ተሰጥቶ በሰማዕትነት የሞተው ለማናጥዮስ ምጥው ለእንበሳ ነው።*
[259] The Aposotolic Canon Canon I and II

[260] Eucharist Bishop Church, p. 89

[261] Ibid

ሰነዶችን፣ ስንመለከት፤ የቤተ ክርስቲያን አንድነቷ ወጥ ሁኖ ሊቀ ጥል የቻለው በጳጳሳቱ አንድነት ምክንያት ነበር።[262] ከላይ በመግ ቢያው እንደ ገለጽነው፥ በሐዋርያት ቀኖናም እንደ ተጠቆመው፥ ጳጳሳት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሚጠብቁ ጠባቂዎች ናቸው።[263] የብዙዎቹን የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሰማዕትነት ሞት ስንመለ ከት አሟሟታቸው ለተሾሙበትና ለተቀበሉት አደራ በእግዚአብ ሔር ቃል ላይ የታመነ ምስክር ሁነው እንደ ነበር እንመለከታ ለን።[264]*

ይህ ታሪክ የነቀለሚንጦስን፣ የእነአግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳን፣ የነተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስን፣ የነአትናቴዎስን፣ የነዮሐንስ አፈ ወርቅንና የሌሎችንም ዕውቅ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆችን የሚያጠ ቃልል ታሪክ ነው። አሁንም በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ፣ የምናካሂደው የቅደሴ ሥርዓት፣ የምናካሂደው የሥርዓቱና የአምል ኮቱ ሂደት በሙሉ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች በነበራቸው የእግዚአብሔር ቃል ታማኝነትና በከፈሉት መሥዋዕትነት የተገኘ ነው፤ ምንም እንኳ አሁን የቊጥር ልዩነት በእያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ይለያይ እንጂ ጠቅላላ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን የያዘውን ይዘት እንደያዘ ለኛ የተላለፈው በሲኖዶስ ጉባኤ ወይም በጳጳሳት ጉባኤ ነው።

[262] Joseph Cardinal Ratzinger. Called to Communion, p. 47
[263] Ibid
[264] *በዓመት የሚነበበውን ሰንክሣር ስንመለከት የዚህን ታሪክ አውነተኝነት በዝምታ እንዳናልፍ የሚያደርጉ ጉዳዮችን እንመለከታለን።

ይህ ጉባኤ፣ በላዩ የሌለው በቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት የማይመራ ቤተ ክርስቲያን እውነት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመ ሠረተ፣ ትምህርትና ሥርዓተ አምልኮ፣ ያካሂዳል ማለት ስህተት ነው። በጎች ያለ ጠባቂ እና ያለመጋቢ ረኃብ ይሞታሉ፤ ወይም ለአራዊት ይዳረጋሉ። የአሁኑ ትውልድም ኦርቶዶክሳዊ ነኝ ወይም ጥንታዊ ነኝ ሲል፣ ይህንንም ሀቅ ማስታወስ አለበት። ሁሉንም የጥንት መዛግብት ስንመለከት፣ የአባቶችን ጽሑፎች ስናጠና፣ እንዲሁም ቀኖናዎቹንም ስንመረምር፤ የምናገኘው ሀቅ አንድ ብቻ ነው፤ እሱም ለቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ወይም የቅዱስ ሲኖ ዶስ አስፈላጊነት አጠያያቂ አለመሆኑን ነው፤ ይህ ትውልድም ሊያ ስተውለው እና ሊመረምረው የሚገባው ይህንን ሀቅ ነው።

1.5. [redacted]

ከአባቶች ጽሑፍ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምናጠናው፤ ሕጋዊ የክህነት ውክልናን ወይም የጵጵስናን አስፈላጊነትና ዓላማ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ በስፋት ተዘርዝረው የምናገኛቸው፤ ሐዋርያውያን አበው በተባሉ በሐዋርያት ተከታዮች በአግናጥዮስ፣ በቀሌምንጦስና በቱርቱርያኖስ ነው።[265] እነዚህ አባቶች ከሐዋር ያት ቀጥለው ሐዋርያትን የተኩና የእነሱ ደቀ መዛሙርት የነበሩ ናቸው። ሥራዎቻቸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ ለትምህርትና ለሃይማኖት መረጃነት እስከ አሁን ድረስ በሥራ ላይ

[265] Apostolic Fathrs

ከመሆናቸውም በላይ በሕይወታቸው ተመክሮ አሁንም ድረስ ለቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምሳሌ ሁኖ ይኖራል።[266]

ሀ/ አግናጥዮስ ምንው ሰአንበሳ፤

አግናጥዮስ ስለ ጵጵስና ያለው አስተምህሮ ሰፊና መሠረታዊነት ያለው ነው። በአግናጥዮስ ትምህርት ጳጳስ የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ነው።*[267] እግዚአብሔር አብ ካለው መለኮታዊ ፍቅር የተነሣ፣ ዓለምን ወድዶ ልጁን መሥዋዕት ሁኖ ሰውን እንዲያድን እንደ ላከው ሁሉ፥ ጳጳስም እግዚአብሔር እሱን በወደደው መለኮታዊ ፍቅር ተነሥቶ ሕዝቦቹን በመውደድ፤ በቅንነት እሚያገለግል የተወደደ ካህን ሊመድብላቸው ይገባል፤ በሌላ መልክ ጳጳስ አብን ሲወክል፣ ካህናት ወልድን፥ ዲያቆናት ሐዋርያትን ይወክላሉ።[268] ለአግናጥዮስ ካህናት የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌዎች ናቸው።[269]

እግዚአብሔር ወልድ በዚህ ምድር ላይ ሰው ሁኖ ሲመላለስ በአባቱ ፈቃድ ብቻ ካልሆነ በቀር በራሱ ፈቃድ አንድም እንዳላደረገ ሁሉ፤ ካህናትና ዲያቆናትም የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ የሆነው በምእመናኑ ፍቅር ላይ ተመሥርቶ ምእመናንን የሚያስተዳድረው

[266] St Irenaeus Of Lyons on the Apostolic Preaching, pp. 13-26
[267] Ibid,9, the Apostolic Fathers The Late of Ignatis of Antioch * *በዚህ ከፍልም በብዛት ለመረጃነት የቀረበው በዚሁ በአግናጥዮስ መልእክት ላይ ነው፣ ምክንያቱም በክህነት ሙሪያ ላይ በብዛት የሠራው እርሱ ስለ ሆነ ነው። ከዚህም ቀጥሎ በተከታታይ የምንመለከታቸው አባቶች ተመሳሳይ ሁኔታ ይኖራል ፥ ስለ ሆነም ዝኒ ከማሁ ወይም Ibid የሚለውን ሥርዓት አከተላለሁ።*
[268] *Ibid ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጸ ጳጳሳት ይመልከቱ ተመሳሳይ ሐሳብ አለው።* Johannes Quusten, Pareology, 66
[269] Ibid ዝኒ ከማሁ አንቀጽ አምስት ፍትሐ ነገሥት ገጽ 57

ጳጳስ ፈቃድ ፈጻሚዎች ናቸው።[270] ጳጳስ የተሾመው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እኔ በውስጤ እግዚአብሔር ገልጦልኛል።[271] ይህ መገለጥ እግዚአብሔር ካለው መለኮታዊ ፍቅሩ የተነሣ ለምእመናኑ የሚያስብ ጳጳስ ይሾማል ብዬ አስባለሁ። የጳጳሳት ሥራ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ ለዓለም መስጠቱንና በአንደበት ሊገለጥ የማይችለውን ፍቅሩን ማስተማር ነው።[272]

ካህናትም በጳጳሳቸው መሪነት ይህንን ከአእምሮ በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቸርነትና ሥጦታ ማስተላለፍ ነው። ያለ ጳጳስ ፈቃድ ከሆነ ጥምቀት እንኳ ተቀባይነት የለውም።[273] ጳጳስ ሊያ ደርገው የሚገባው ትልቁ ነገር የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ ነው። የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነውም የእግዚአብሔርን ፍቅርና ክብር በሥራ ስለሚፈጽም ብቻ ነው።[274] ካህናትም ይህንኑ በጳጳሱ አማካይነት ያገኙትን የእግዚአብሔርን ፍቅር በሥራና በቃል መግለጥ አለባቸው። አግናጥዮስ እንደሚለው ጵጵስና የቤተ ክርስቲያን ምሰሶ ነው። ካህናትና ምእመናን እግዚአብሔርን የሚያዩት በጳጳሱ አማካይነት ነው።[275] የእግዚአብሔር ፍቅርና የአባትነት ምንጭ ሊገለጥ የሚችለው የጳጳሱ በቤተ ክርስቲያን መገኘት ነው ፤ ይላል አግናጥዮስ።[276]

[270] Ibid ዝኒ ከማሁ
[271] Ibid Johannes Quusten, Pareology, p. 67
[272] Ibid Johannes Quusten, Pareology, p. 58

[273] Ibid Johannes Quusten, Pareology, p. 78
[274] Ibid and Iabid
[275] *Johannes Quusten, Pareology, 68 Epistle of Iginatus to the Ephesians Ch V*
[276] *Ibid Epistle of Iginatus to the Ephesians,ch XX*

አግናጥዮስ ስለ ጳጳሱ ሲናገር አንተ እንደ ማንኛውም ሰው አይደለህም፤ የእግዚአብሔርን ፍቅር የምትገልጥ የፍቅር ሰው ነህ።[277] የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጠው ባንተ ስለ ሆነ ግሩምና ድንቅ ጳጳስ መሆን ይገባሃል።[278] በአግናጥዮስ ሐሳብ መሠረት ጵጵስና ማለት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመምራት ኃላፊነትን መሸከም ማለት ነው።[279] አግናጥዮስ ምእመናኑን ሲመክር፣ ጳጳሳቱ እሚያደርጉት ጸሎትና ሥርዓተ አምልኮ ካህናትንና ምእመናንን የሚያስደስት ልብንም የሚመሥጥ ነው።[280] ምእመናን በዚያ ሰዓትና በዚያ ቦታ ጳጳሱ የክርስቶስን ሥጋ በሚፈትትበት ጊዜ እንዴት እንደምትደሰቱ አስቡ።[281]

ይህ የእግዚአበሔር ስጦታ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚካሄድ ትልቅ ሥርዓት ነው። ሁኖም ጳጳሳት የእግዚአብሔር ተጠሪዎች በመሆናቸው ሊጠነቀቁና እግዚአብሔርን ሊያከብሩ ይገባል።[282] አግናጥዮስ በጻፋቸው አምስት መልእክታት በሁሉም ማለት ይቻላል፣ የጵጵስናን አስፈላጊነት ያልገለጠበት ቦታ የለም። አግናጥዮስ የጵጵስናን ሥልጣንና አስፈላጊነት የገለጠውን ያህል፣ የኃላፊነቱን ክብደትም በሰፊው አብራርቷል።[283]

[277] *Epistle of the Magnesians, ch XIII*
[278] *Epistle of Iginatus to the the Trallians, ch II*
[279] *Epistle of Iginatus to the Ephesians,ch,IV*
[280] *Ibid (ሁሉም)*

[281] *Ibid,V*
[282] *Ibid*
[283] *Justo L. Gonzalaz A History of Chrisian Thought, p. 73*

ለ/ ቀለሚንጦስ ዘሮም፤

ቀለሚንጦስ የጴጥሮስ ደቀ መዝሙር እንደ ነበር ተነግሮለታል።[284] ከጴጥሮስ በመቀጠልም የሮሜ ጳጳስ የነበረ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።[285] ሐዋርያትን ያየና ከሐዋርያት የተማረ ስለ ሆነ ጽሑፎቹና ምስክርነቱ እውነት ነው ተብሎ በብዙዎች ይታመናል።[286] በብዙ ቦታ ላይ ስለ ጵጵስናና ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ጽፏል።[287] ቀለሚንጦስ ዘሮም በመጀመሪያ መልእክቱ ላይ የጻፈው፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ከእርሱ የተማሩት ሐዋርያቱ ከእግዚአብሔር ተቀብለው እንደ ሰበኩት ያምናል።[288]

ከክርስቶስ የተማሩት ሐዋርያትም በኢሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል አንጻር፥ የአዲሲቱ እሥራኤል ዘነፍስ የቤተ ክርስቲያን መሥራች አባቶች ሁነው ሠርተዋል ብሎ ያምናል።[289] እሱም ያንን ወንጌል ከእነርሱ ተቀብሎ ለማስተማር እንደ ተሾመና ሥልጣኑን እንደ ተቀበለ ይገልጣል።[290] የቤተ ክርስቲያን የክህነት ሥልጣንም ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር እንደ ተያያዘ ያስረዳል።[291] የቤተ ክርስ

[284] *Ibid*
[285] *The Apostolic Fathers Introductory Note,land p. 2*
[286] *Justo L. Gonzalaz A History of Chrisian thought, p. 67*
[287] *The first Epistil of Clement, Ch XLII*
[288] The first Epistil of Clement, Ch XLII* *የቀለሚንጦስ መልእክት ብዙ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን የያዘ መልእክት ነው። በክህነታዊ አገልግሎት ላይ የሸፈነው ጠቅላላ ስምንት አጫጭር ምዕራፋትን ያጠቃለለ ነው። በእነዚህ ምዕራፋት ውስጥ በተለያየ የቃላት አጠቃቀም ተጠቅሞ ገልጦአል በዚህም መሠረት የተለመደውን ተደጋጋሚ የግርጌ ማስታወሻ መጠቀሜ አልቀረም።*

[289] Ibid Ch XLIII
[290] Ibid
[291] Ibid ChXLII

ቲያን ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ኃይል የተመሠረተ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ይህንኑ አረጋግጧል።

ለቀለሚንጦስ የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት፥ በክርስቶስ ትን ሣኤ ላይ የተመሠረተችው የቤተ ክርስቲያን ማንነት ነው።[292] የእ ግዚአብሔር መንግሥት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ በሞቱ፥ በትንሣኤው፥ በዕርገቱ የተመሠረተች ስለሆነ፥ ዋና ሥራዋ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት ይህንን ለዓለም ማወጅ ነው።[293] ይህ እምነት ከሐዋርያት ተያይዞ የመጣ ነው። ጳጳስ ማለት የዚህ ሥራ ዋና አለቃ ሲሆን ካህናቱንና ዲያቆናቱን ደግሞ ለዚህ ሥራ ያሰል ፋል።[294]

ለቀለሚንጦስ ጳጳሳት፣ ካህናትና ዲያቆናት አንድ የሆነችውን የእግ ዚአብሔርን ቤተ ክርስተያን፣ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ በመንፈስ ቅዱስ የተመደቡና የተሾሙ ናቸው።[295] ጠቅለል ባለ መልኩ ለቀለ ሚንጦስ የጵጵስና ሥራ እንደ አግናጥዮስ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ጥንካሬምና ውበት እጅግ አስፈላጊ ነው።[296] ለቀለሚንጦስ ጳጳሳት ማለት ለቤተ ክርስተያን ጠባቆችና ጠበቆች ማለት ነው።[297]

ሐ/ ቱርቱርያኖስና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣

በመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት፣ ከቱርቱርያኖስ ጋር ሌሎ

[292] Ibid
[293] Ibid
[294] Early Christian Fathers Edited by Cyril C Richardson, p. 39.
[295] Ibid ch,42 ሁሉም
[296] Ibid ch,44
[297] Ibid.

ችም ፖሊካርፕ፥ ሲብሪያን፥ የተባሉ ሐዋርያውያን አበው በዚሁ በምሥጢረ ክህነት ወይም በጵጵስና ብዙ የሠሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ነበሩ።*[298] ለነዚህ አባቶች ቤተ ክርስቲያን የሚለው ራሱ ስያሜው በጳጳስ አማካይነት ምሥጢረ ቍርባንን የምታካሂደዋ የተቀደሰ ጉባኤ ማለት ነው። ስያሜው ሲተረጎም በሁሉም ያለች አንዲት ወይም ካቶሊካዊት፣ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። ይህ ማለትም በተለይ ሲብሪያንና ፖሊካርፕ ሲገልጹ በሁሉም ከተማ በሕጋዊ የክህነት ውክልና ውስጥ የሌለች ቤተ ክርስያን እንደ ቤተ ክርስቲያን አትቆጠርም።[299] ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ለመባል የሚያስችላትን መስፈርት የጳጳሱን ይሁንታ ወይም ቡራኬ ስላላ ገኘች ነው።[300]

ዙዙሊዮስ የተባሉ የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሊቅ እንደ ገለጹት የምሥጢረ ክህነት አድገት ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እስከ ኒቅያ ጉባኤ ድረስ የነበረ የጵጵስና ሥልጣን፣ መጀመሪያ እያን ዳንድዋ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያን መባል የምት ችለው፣ በጳጳስ መሪነት የምሥጢረ ቍርባንን ሥርዓት የምትፈጽ

[298] Justol, Lgonzalez, A History of the Christinan Thought, 183-184 *በዚህ ዙሪያ ላይ በብዙት የሠራው ሲብሪያን የተባለው የካረቴጅ ያሁኗ ቱኒዝያ ተሰወጅ ነው። የጵጵስናን ሥልጣን አስመልክቶ ብዙ ደብዳቤዎችን ጽፏል፤ የጻፈው ደብዳቤዎች ተሰበስበው በአንድ ላይ በቅዱስ ሽላዲመር የኅትመት ድርጅት On the Church Selected Letters, St Cypiane of Carthage በሚል ታትመው ወጥተዋል፤ ለምሳሌም ያህል pp 29-53, መመልከት ይቻላል።*
[299] On the Church Selected Letters, pp. 53-54.

[300] *ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አንድ ቍጥር 2*

መዋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች።[301] በመጀመሪያው መቶና መቶ ኀምሳ ዓመት በምኵራብ መሰብሰብ ወይም በሌላ ሕንጻ ተሰብስቦ ትምህርት መማር ወይም ጉባኤ ማድረግ ብቻውን በቂ ስላልነበር፣ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስያሜ ለማግኘት አያስችልም ነበር።[302]

ቤተ ክርስተያን የሚለውን ስም ታገኝ የነበረችው፤ በጳጳሷ መሪነት ቅዱስ ቊርባንን የምትፈጽመዋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች።[303] በሌላ አባባል፣ የቤተ ክርስተያን ራስ የሆነውን የማይታየውን ክርስቶስን የወከለው የሚታየው ጳጳስ፥ ሥጋውንና ደሙን በሚፈትትበት መንበር ላይ ሁኖ መታየቱ ነው፣ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስሟን ሊገልጠው ይችል የነበረው።[304]

ይህ ሥርዓት በየጊዜው እያደገ ሲሄድ፣ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ከፍ ማለት ጀመረ። ይኸም ያከባቢ ጳጳሳት በመሰባሰብ አንዲቷን የአግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በሚገልጽ አንድነት የጳጳሳት ጉባኤ ሁነው እነሱ በእግረ ሥጋ በማይደርሱበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከእነሱ ሥልጣን በመቀበል ካህናት የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን ክርስቶስን በወከለው በጳጳሱ ፈቃድ ምሥጢረ ቊርባንን እንዲፈጽሙ ሥርዓት ተሠርቷል።[305] ይሄው የጵጵስና ሥርዓት በጣም ከፍ በማለት፣ የምሥጢራትን ሥራ መፈጸም ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መምራትና

[301] John D. Zizioulas, Eucharist Bishop Church, 48
[302] Ibid.
[303] Ibid.
[304] Ibid, 49
[305] Ibid, p. 53 ሁሉም

መጠበቅም ጭምር ሆነ። [306] ይኸም አሁን ሀገረ ስብከት የምንለውን የአስተዳደር ሥርዓትን መሠረተ።[307]

በዚህ ረጅም ጉዞ ላይም አሁን ያለው ዓይነት የማንነት ቀውስ አልታየም። በተለይም ምሥጢረ ክህነትን የመርገጥና አላስፈለጊ ነው የሚል ከሥተት አልተፈጠረም።[308] አሁንም ቢሆን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በስተቀር ሌሎች ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን አይሞከሩትም። የእኛ ችግር የት ላይ እንደ ሆነና ከየት እንደመጣ በሚቀጥለው ከፍል እንመለከታለን።

1.6. ምሥጢረ ክህነት በአሁኑ ዘመን ሊቃውንት፤

በአሁኑ ዘመን ያሉ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ስለ ምሥጢረ ክህነት ምን ይላሉ? በቤተ ክርስቲያናችን *"ምሥጢረ ክህነት"* ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ሁኖ በመመደብ ይታወቃል። [309] በመሆኑም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በሚነሣበት ሁሉ ምሥጢረ ክህነት ይወሳል፤ በጽሑፍ ደረጃም ለብቻው ተጠንቶ የቀረበ ነገር ብዙ አይታይም። ያም ቢሆን እንዲያው ስለ ክህነቱ አግልግሎት ብቻ ይገለጣል እንጂ፥ መሠረታዊ የክህነት አስፈላጊነት ምን ያህል እንደ ሆነ ተብራርቷል ማለት አይቻልም። በሌሎች ኦርቶዶክሳውያን ግን በሰፊው ጥናታዊ ሥራ ተሠርቷል::

[306] Ibid
[307] *ፍትሕ መንፈሳዊ ለንቀጽ ለንድ ቊጥር*
[308] *ዝኒ ከማሁ*
[309] Eucharist Bishio Church, pp. 11-16

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል። John D.Zizioulas Metropolitan of Pergamon John H.Erickson Profssor of Cacon Law and Church History Cat St. Vladimmir Orthodox Theological Seminary.John Meyendorff use tibe professor of Church History Miro slav Vole Professor of Systematic Theology and Others የሚለውን መጥቀስ ይቻላል ። ዙዚሊዮስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ሲገልጹ፣ በቅዳሴው የሚገለጠው የጳጳሱ ቅዳሴን ማክ በር የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ታሪካዊ ሂደት መመሪያ እንደ መርሕ በመግለጽ ነው።[310]

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያን ለመባል የምትችለው በኤጲስቆጶስ መሪነት አኰቴተ ቍርባን ታካሂድ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ነበረች።[311] በዚያ ዘመን በምንም መንገድ በኤጲስቆጶስ የሚመራ ቅዳሴ ወይም ሥርዓተ አምልኮ የማታካሂድ ቤተ ክርስ ቲያን፣ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ክርስቶስን መግለጥ አትችልም። ይህን ሐሳባቸውን ለማዳበር ዙዙሊዮስ ሲኖዶሳዊ ምሥጢረ ከህነትን በሦስት ምድብ ይመድቡታል።[312]

ሀ/ <u>የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያንና የጳጳሳት ግንኙነት ነው፤</u>

በዚህ ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን ምንነት ማለትም ቤተ ክርስቲያን መጠሪያወቿን የሚገልጥ ሐሳብ የተብራራበት ክፍል ነው፤ የጥንቷ

[310] Ibid
[311] Ibid
[312] Ibid

ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቦታዎች በጎብረት ቢሆንም ወይም የብ ዙዎች ስብስብ ብትሆንም፣ በአንዱ በክርስቶስ የሆኑና የተገኙ በክ ርስቶስ አንድ ሕዝብ ናቸው። አንድ ቊጥርን ከተጠቀምን አንድ እንጂ ብዙ ሊሆኑ አይችሉም። ስለ ሆነም የምትጠራው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አንድ ጉባኤ ተብላ ነው።[313]

መጠሪያ ስሟን ያገኘችው ከምታካሂደው ሥርዓተ አምልኮ በመነ ሣት ነው። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ተብላ እንድትጠራ ያደረጋት፣ በጳጳስ መሪነት የሚካሄደውን የምስጋና መሥዋዕት ማቅረቧ ነው እንጂ፣ አምልኮቱ ብቻውን አልነበረም[314]። የእግዚአ ብሔር ቤተ ክርስቲያን ማለት በጳጳሷ መሪነት ሥርዓተ ቅዳሴ ሥርዓተ አምልኮ የምታካሂድ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። ያ ካልሆነ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምንም ዓይነት የተሟላ ትርጉም አይኖረውም። ስለዚህ ይላሉ ዙዚሊዮስ፣ በአንድ ጳጳስ መሪነት የቅዳሴ ሥርዓተ አምልኮ፣ በአንድ መንበር፣ ከአንዱ ማዕድ፣ የክርስቶስን ሥጋ የተቀበለ፣ ካንዱ ጽዋዕ የክርስቶስን ደም የተቀበለ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነው። አንዲቷን የእግዚአብር ቤተ ክርስቲያን ስያሜ ሊገልጥ የሚችለው ይህ ሲሆንና ሲሟላ ብቻ ነው።*[315]

ለ/ <u>ሁለተኛው፣ የቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ እድገት ነው፤</u>

በዚህ ክፍል ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እያደገች ስትሄድ አንድ ጳጳስ

[313] Ibid, p. 21
[314] Eucharist Bishop Churcuh, p. 87
[315]* ibid, 88- ይህ ክፍል የሚሸፍነው ከመጽሐፉ ገጽ 88-106 ነው በሳቸው አባባል

ብቻ ለብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት ሲመደብ ወይም አንድ ጳጳስ ብቻ ሲሆን ከአንድ በላይ ለሆኑት አብያተ ክርስቲያናት የሥልጣኑ መጠን ካለበት ቤተ ክርስቲያን ያነሰ አይደለም:: ምክንያቱም የአባቶች ጽሑፍ ለዚህ ሐሳብ በቂ መልስ ይሰጣል።

ጸሐፍቱ እንደሚሉት ጳጳሱ በካህናትና በዲያቆናት ይታገዛል፤ የሚለው አባባል የጳጳሱን ሥልጣን በካህናቱ ላይ ፍጹም ያደር ገዋል። ስለ ሆነም ከልሉ ወይም ሀገረ ስብከቱ የእርሱ እስከ ሆነ ድረስ ባለበት ሁኖ የመደባቸው ካህናትና ዲያቆናት የሚሰጡት አገልግሎት ጳጳሱ እንዳካሄደው እንዲቆጠር ሆነ።[316] ቤተ ክርስ ቲያን ያለ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያን ልትባል አትችልም። በአንጻሩም ጳጳስ ያለ ካህናትና ዲያቆናት ብቻውን ቤተ ክርስቲያን ሊያስብላት አይችልም::

ዙዙሊዮስ ከአግናጥዮስ በመውሰድ፣ እሚታየው ጳጳስ የሚፈጽ መው የቅ‹ርባን ሥርዓት በመንፈስ ከእኛ ጋር የሆነውን የማይታየውን ክርስቶስን ይገልጣል።[317] አንዲ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ቅዱስ ቁ‹ርባንን በምታካሂድበት ጊዜ፥ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለችም ። በሊቀ ጳጳሱ እንደምትመራዋ እግዚአብሔርን የምትወክል የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ናት።[318] ይህም አንዱን አኰቴተ ቁ‹ርባን በአንድ ጊዜ በተለያየ ቦታ መፈጸማቸው አንዲን ሙሉ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ይገልጣሉ።

[316] Ibid,89-93
[317] Ibid, 84-97
[318] Ibid,98-103

ዙዙሊዮስ ይህን ሐሳብ በዓለም ያለችውን አንዲቷን ቤተ ክርስቲያን አንዱን አኰቴተ ቁ‹ርባን ሕጋዊ ዕውቅና ባለው ጳጳስ እስከ ፈጸመች ድረስ በየትም ቦታ በማንኛውም ጊዜ ብትሆንና ብታደርግም የአንዱ አምላክ የልዑል እግዚአብሔር አንዲት ቤተ ክርስቲያን ናት ፣[319] በማለት ያብራራሉ ።

ሐ/ የጳጳሳቸው ያደሳቸው ቤተ ክርስቲያን

ያደገችው ቤተ ክርስቲያን አንድነትና የአንድ ጳጳስ ሥልጣን በብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ላይ፤ የሚለው ጉዳይ ነው።*[320] ይህ ክፍል በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያን በማደጓ ምክንያት በእያንዳ ንዱ ከተማ ያለችው ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች በገጠሩ ያለውን ሕዝብ ስትቆጣጠር፤ አንድ ጳጳስ፣ አንድ መንበር፤ ለአንድ ከተማ የሚለውን የአዳጊዋ ቤተ ክርስቲያን መርሕ በነበረው ትውፊት መቀጠል የማይቻል እየሆነ መጣ።[321] እንዳውም ታሪካዊ ሂደት እንደ ነበረ እንጂ በተግባር ለመከተል አዳጋች ሁኖ ታየ።[322]

በሌላ በኩል አኰቴተ ቁ‹ርባን ወይም ቅዳሴ ያለ ጳጳስ ማከናወን፤ አንድዋን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አንድነት ለመግለጽ ያለዚህ ሥርዓት የማይቻል ሆነ። ስለ ሆነም ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያድርጋት የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን እንደ ተጠበቀ ሁኖ፥ በያካባቢው የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን የራስዋን

[319] Ibid
[320] Eucharist Bishop Chuch,*ይህ ክፍል ደግሞ ከገጽ 107-162 ያለውን የመጽሐፉን ክፍል የሸፈነው ክፍል ነው።
[321] Eucharist Bishop Chuc, pp. 107-118
[322]Ibid

ካህናትና ዲያቆናት በመምረጥ በዚያው በአንዱ የክልል ጳጳስ ሿሚነትና የበላይነት ሥርዓተ ቍርባንን ማከናውን ቻለች።[323] ይህ ሥርዓተ ቍርባን ጳጳስ እንዳከበረው ተቆጥሮ አጥቢያዋ ቤተ ክርስቲያን በተመደባላት ካህን አማካይነት የምትፈጽመው ቅዱስ ቍርባን በጳጳሱ መሪነት የቅዳሴዋን ሥርዓት እንደምታካሂደው ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን የመግለጥ ኃይል አላት::

በሌላ አባባል በሁሉም ያለች አንዲት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲ ያን ትባላለች።[324] ምክንያቱም ካህናቱ ቍርባንን በኃላፊነት የሚያ ካህዱት የጳጳሱን ዕውቅና በማግኘታቸው ነው። ይህ ሐሳብ የሚያ ስረዳው እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ቤተ ክርስቲያን ልት ባል እምትችለው በጵጵስና ሥልጣን ሥር ሁና ምሥጢራትን ስት ፈጽም በመሆኑ ነው፤ በሌላ አባባል ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕጋዊ የከህነት ውክልና ያለው ጳጳስ የሚመራትና የሚያስተዳድራት ማለት ነው።*[325]

ጆን ኤሪክሰን የትውፊታዊ ቀኖናን ምንነት ሲያብራሩ፣ ቤተ ክርስ ቲያንን ሕጋዊ አካል እንድትሆን ያደረገ ትልቅ ኃይል እንደሆነ ይገ ልጻሉ።[326] እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያን ከንዋኔ ሕጋዊና ቋሚ የሚያደርገው ትውፊታዊ ቀኖና ነው።[327] ሕጋዊ የከህነት ውክልና

[323] Ibid
[324] Ibid
[325]* *ተመልሰን የምንሄደው ያለ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያን የለችም ፥ ያለ ቤተክርስቲያን ጳጳስ የለም የሚለውን የሲቢሪያንን የነገረ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ያደረገው ያለ ጳጳስ ፈቃድ ቅዳሴ የምታካሂድ ቤተ ክርስቲያን ለዘላለም አይቀደሰባት፥ የቀደሰው ካህንም የተከተሉት ምእመናንም የተወገዙ ይሁኑ ያለውን አንቀጽ ማጠናከሪያ ሐሳብ ነው።*
[326] *John H.Erickson, The Challenge of Our Past, pp. 9-37*
[327] Ibid, 11-15

ያለው እያንዳንዱ ካህን ሊያደርግ የሚገባውን የሚወስነው ሕግ የሚገኘው በትውፊታዊ ቀኖና ነው። ቤተ ክርስቲያን በሮማውያ ንና በቢዛንታውያን ዘመን፥ እነሱ የተጠቀሙበትን ሕግ በማስታ ከክ የራሷን ምሥጢራት አገልግሎት ሕጋዊ የሚሆኑባቸውን ትው ፊታዊ ቀኖና አዘጋጅታለች።[328] ይኸም ከንውን ምሥጢረ ክህነ ትን፣ ንስሐን፣ ጋብቻንና ፍችን የሚያጠቃልል ሕግ ነው።

የጆን ኤሪክሰን ጥናት እንደ ዙዙሊዮስ ሁሉ የተመሠረተው በጥንት አባቶች ትውፊታዊ ቀኖና ላይ ነው፤ በተለይም ክህነትን መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ምሰሶ አድርገውታል። ለኤሪክሰን ክህነት ማለት የምሥጢራትን አገልግሎት ፈጻሚ ብቻ አይደለም ፤ ቋሚ ሃይማኖታዊ ውሳኔዎችን ወሳኝና የተወሰኑትንም ጠባቂና አስተባቂም ነው።[329]

የጆን ኤሪክሰን ሐሳብ የቢዛንታይንን ማለት የሮማውያንንና የምሥ ራቁን አንድነትና ልዩነት የተነተኑትን ትንተናና አስተያየት አልፈን ስለ ሲኖዶስና ክህነታዊ አገልግሎት የጻፉትን በአንድ ዓረፍተ ነገር እንግለጠው ብንል፥ ቤተ ክርስቲያን፥ ቤተ ክርስቲያን ሁና የቆየች ውና አሁንም ያለችው፣ ወደ ፊትም የምትኖረው፣ ከሐዋርያት ተያ ይዞ በመጣው ትውፊት መሠረት፥ የቅዱስ ሲኖዶስን ሥልጣን ስትቀበልና ለሥልጣኑም ተገዥ ስትሆን ነው የሚል ይሆናል።[330]

[328] Ibid, 16-21
[329] *John H.Erickson, The Challenge of Our Past, pp. 23-37*
[330] Ibid, 25

ሚሮስላቭ ቮልፍ የዙዚሊዮስንና ጆሴፍ ራትዚነግር የአሁኑ ፖፕ የሆኑት ቪኒ ዴክት አሥራ ስድስተኛ በጻፏቸው መጻሕፍት ላይ ትንታኔያዊ ግምገማ ሰጥተዋል።

በዚሁ ግምገማ ላይ ሁለቱ ሊቃውንት በትውፊታዊ ቀኖና ላይ ያላቸው እምነት አንድ ዓይነት ከመሆኑም በላይ ከብደትና አክብሮት እንዳላቸውም ጸሐፊውን አሳምነዋቸዋል።*[331] ሁለቱም ቤተ ክርስቲያን ያለ ምሥጢረ ክህነት፣ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ልትጠራ አትችልም፤ ቤተ ክርስቲያንም ብቸኛ ሁና ልትኖር አትችልም።[332] ቤተ ክርስቲያን በጳጳሳት ጉባኤ አማካይነት በተሰጣት የክህነት አገልግሎት ምሥጢራትን በአንድነት ስትፈጽም፣ ኮሚኒዬን አንዲት ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ሰያሜ ታገኛለች ነው የሚሉት።[333]

ከዚህ በላይ ለምሳሌ በጥቂቱ የገለጥናቸው ነጥቦችን መሠረት በማ ድረግ፣ የሚከተለውን ማለት እንችላለን።

አሁን ባለንበት ዘመን፣ ያሉ የተለያዩ አገሮች፣ ብሔራዊ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናኖቻቸው በዓለም ሲበተኑና በዚያው በዝ ተው አገር በቀል[334] ትውልድ ሲያፈሩ፣ ነጻ ቤተ ክርስቲያን ለማቋ ቋምም በእናት ቤተ ክርስቲያን ሥር ለመኖርም፣ ትውፊታዊ ቀኖ ናን መሠረት ባደረገ ጥናታዊ ትንተና በማድረግ ችግራቸውን ከት

[331] Miroslav Volf, After Our Likeness, The Church as the Image of the Trinity, pp. 29-123* በዚህ መጽሐፍም
[332] Ibid

[333]Ibid
[334] Ibid

ውፊታዊ ቆኖና ጋር እንዲስማማ ያደርጋሉ እንጂ[335] ችግራቸው ከትውፊታዊ ቀኖና አስወጥቶ እንዲበታተኑ አላደረጋቸውም።

ከፍ ብለን እንዳየነው ትውፊታዊ ቀኖናው ከመበተንና ከመከፋ ፈል አድኗቸው እናገኛለን። ለዚህ ችግር ዋና መፍትሔ የሆናቸው የመጀመሪያውን ትውፊታዊ ቀኖና ጠንቅቆ መረዳትና ለቀኖናው ተገዥ መሆን ነው። ለሕጉ ተገዥ ካልተሆኑ በቀር የሕጉ መኖር ብቻውን አንድነቱን ሊያመጣው አይችልም።

ሌላው ክህነት፣ በታላፊነት ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት በክርስ ቶስ የተሰጠ መለኮታዊ ስጦታና ታላቅም አደራ መሆኑን ማመን አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባል። ክህነትንና ምንጩን ከካድን ግን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እያገለገልን ነው ማለት እንደ ሌለብን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ቀደም ሲል ስለ ክህነት፣ በተለያዩ ርእሶች የቀረበውን ገለጻ በሚከ ተለው መልኩ ማጠቃለል እንችላለን። በትውፊታዊው ቀኖና መሠረት፥ ለሐዋርያዊው ሕጋዊ የክህነት ውክልና፥ የተሰጠው ከብር ምን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው።[336]

አሁን የኛ ችግራችን ሁኖ የተገኘው፣ ከሁለት አንዱን መምረጥ አለመቻል ነው። ክህነት የጥሪ ሥራ ነው። ሥራውም ደመወዝ ለማግኘ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በታማኝነት መጠበቅ ነው። የክህነት ዋና ዓላማ ይህ መሆኑ ከገባን፣ ከሁለቱ ምርጫወች አንዱን ልንመርጥ ይገባል።

[335] Ibid
[336] Lewis J.Patsavos, Spiritual Dimensions of the Holy Canons, pp. 11-15

አንደኛው ምርጫ ሕገ ቀኖናው በሚያዘው መሠረት መመራት ነው።

ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ ይህንን ከዶ በቤተ ክርስቲያን ስም የራስን ኑሮ መሥርቶ መኖር ነው። ሁለተኛውን ከመረጥን ግን ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንሣት አንችልም። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን ሊያሰኛት የሚችለውን መመዘኛ ስላላሟላን፣ ለክህነትም የተሰጠውን አክብሮት ስላልተቀበልን፣ ትክክለኛ ቤተ ክርስቲያን ነን ብለን እንድንናገር አያደርገንም።

2. የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አቋም፤

ቤተ ክርስቲያንንና ታሪኳን ስናጠና የእድገቷ፣ የስፋቷና የጥንካሬዋ መሠረት በትውፊታዊ ቀኖና መመራቷ ሁኖ እናገኘዋለን::[337] ይህንን እውነት አለመረዳት፣ በሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት የተወሰነውን ውሳኔ በተግባር/አምኖ አለመቀበል፣ ውሳኔው ለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አቋም የሰጠውን ጥቅም አለማስተዋል ሲሆን።[338] በእምነታችንና በመንፈሳዊ እድገታቻን ላይ ያመጣውና ወደ ፊትም ሊያመጣ የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምን ያህል እንደሚሆን እንመረምራለን::

ቤተ ክርስቲያን ስትጀመር አንሥቶ ያለ ሲኖዶሳዊ ጉባኤ የኖረች በት ጊዜ የለም። አሁን ባለንበት ዘመንም ቢሆን፣ ከአርቶዶክስ ውጭ ያሉት እንኳ ሳይቀር ቤተ ክርስቲያንን በበላይ የሚመራ

[337] Hippolytus, On the Apostolic Tradition, pp. 53-78
[338] John Meyendorff, Catholicity and the Church, p. 121

የበላይ አካል አላቸው።[339] እሱም አንዳንዶቹ ጉባኤ ይሉታል፣ ሌሎች ደግሞ ሲኖዶስ ይሉታል። በየትኛውም ስም ይጥሩት፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን በባለቤትነት የሚመራ አካል አለ። ይህም ትውፊት የተገኘው ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ነው።[340] ከሐዋርያት ጀመሮ የሲኖዶሳዊ ጉባኤ ዋና ዓላማ በቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ችግር ሲፈጠር ተሰብስቦ ችግሩን ማስወገድ ነው።

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት፣ለመን ጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማ ይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፣ ደቀ መዛሙርትንም ወደኋላቸው ይሰቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከ ላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ"።[341] ተብሎ እንደ ተጻፈ። የተቀ በሉትን አደራ ይወጡ የነበረው፣ እንደዚሁ በመሰባሰብ ነበር። በዚሁ መሠረት፣ ከክልላዊ ሲኖዶስ ውሳኔና ጉባኤ ውጭ፣ ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ዓለም አቀፍ ጉባኤያት አሉአት ።[342]

በነዚህ ጉባኤያት የተወሰኑ የሃይማኖት መግለጫዎች፣ የተቀነኑ ቀኖናዎች በሙሉ አሁን የምናምነውን እምነት፣ የምንመራበትን

[339] Francis Turretin, Institues of Elenctic, p. 41
[340] Ibid
[341] *የሐሥ 20: 28*
[342] Arch bishop Peter'Huillier, The Church of the Ancient Councils the Disciplinary Work of the First Four Ecumenical Councils ከአራቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ውስጥ እኛ የምንቀበላቸው ሦስቱን ብቻ ነው። የመጽሐፉ ገጽ ያላስፈለገበት ምክንያት መጽሐፉ በሙሉ የዓለም አቀፍ ጉባኤያትን የያዘ ስለሆነ ቀኖናዎቹን በጉባኤው ስያሜ ጉባኤ በተካሄደባቸው ቦታዎችና ዓመተ ምሕረት ስለ ሚገኝ ነው።

ሕግና ሥርዓት ይዘዋል።[343] ስለ ቀኖና ቀጣይነት በፍትሐ ነገሥት መቅድም ላይ የተዘገበው ቃል እንዲህ ይላል። *"ቍጥራቸው ሰባ አንድ ከሆኑት ቀኖናት ውስጥ በሠላሳኛው ትእዛዝ እንዲህ አሉ። ከሥራ ማናቸውንም ያንደልን ብንሆን እናንተ በሚገባ አሚሉት፤ ለሁላችንም የእግዚአብሔር መንፈስ አለንና። በቀኖና ውስጥ በሠላሳ አምስተኛው ትእዛዝ ከእኛ የቀረ አንዳች ነገር ቢኖር ኤጲስ ቆጶሱ ያሰባስብ" ማለታቸውም ይህንኑ ያስረዳል።*[344]

ይህ ሐሳብ የሚያስረዳው ሲኖዶሳዊ ጉባኤ ለቤተ ክርስቲያን አንድ ቦታ ላይ የማይቆምና ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ እስከ ኖረች ድረስ አስፈላጊዋ መሆኑን የሚያስረዳ ሐሳብ ነው። ከዚህ በመነ ሣት ይኸው የፍትሐ ነገሥት መቅድም እንዳስቀመጠው እንድ ናነባቸው በተወሰኑት የመጻሕፍት ውሳኔ እንጠቀማለን።[345] ግን መጻሕፍቱ በሚሉት አንስማማም፤ እንዳውም ብዙ ጊዜያችንን ስናጠፋ የምንገኘው የጥንት አባቶች እንደ ትልቅ ችግር ባልቆጠ ሩት በምግብና በመንጻት ጉዳይ ላይ ነው። እኛ የምንቀበላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት፥ በወሰኗቸው ውሳኔዎችና በቀነኗቸው ቀኖናዎች ውስጥ በሁለት የተመደቡ አጀንዳዎች አሉ።[346]

<u>አንደኛው አጀንዳ፣</u> የእውነተኛውን ሃይማኖት ምንነት በትክክል መግለጥና ማስረዳት ነው።

[343] የፍትሐ ነገሥት መቅድም ይመልከቱ።
[344] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ አንድ
[345] ዝኒ ከማሁ
[346] በሦስቱ ጉባኤያት የተወሰኑትን ወሳኔዎችና ቀኖናዎች መመልከት በቂ ነው። Arch bishop Peter'Huillier, The Church of the Ancient Councils

<u>ሁለተኛው አጀንዳ፣</u> እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምትተዳደር የሚያዘው ቀኖና ነው።[347] ይህ ውሳኔ የቤተ ክርስቲያን አቋምዋ እንዲጸና ያደረገ ውሳኔ ነው ። ፍትሐ ነገሥት በየጊዜው የተቀነኑ ቀኖናዎችን ምልከታቸውንና የቀኖና ውን ዓላማ ይዘረዝራል።[348] አሁን ባለንበት ደረጃ ሁሉም ማለት ይቻላል፤ ዓለም አቀፋዊው ጉባኤ የወሰነውን ውሳኔ እንቀበላለን እንላለን፣ በተግባር ሲታይ ግን የምንጥሰው እየበዛ ነው።

በየዓለም አቀፉ ጉባኤያት የተወሰኑት ውሳኔዎች ምን ምን ናቸው? <u>የጉባኤ ኒቅያውን</u> እንመልከት። በዚህ ጉባኤ ስለ ተሰበ ሰቡ የሲኖዶስ አባላት ቍጥር የተለያየ ሐሳብ ቢኖርም፣ ከፍም ዝቅም ብሎ በሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት ጸንቷል። [349]

የጉባኤው መነሻ የሆነው፣ አርዮስ የወልድን ፈጣሪነት በመካዱ ምክንያት ነው። አርዮስ ከአባቶቻችን ተቀበልኩት ብሎ ያስተም ረው የነበረው ትምህርት፤ አብ ሁል ጊዜ አባት ሁኖ አልኖረም፤ በአድ ወቅት አባት ያልነበረበት ጊዜ አለ። ወልድም ሁል ጊዜ ልጅ ሆኖ አልኖረም፣ በአንድ ወቅት ልጅ ያልነበረበት ጊዜ አለ፤ በሚል አስተምህሮው የአርቶዶክስን ሃይማኖት ተፈታተነው። [350] ይህ ማለት በአብና በወልድ መካከል የዘመን መቀዳደም አለ ማለት ነው፤ ይህ የስሕተት አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያንን ከመከፈል አልፎ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ በሙሉ ሊደመስሰው ሆነ::

[347] Ibid
[348] የፍትሐ ነገሥትን መቅድም ይመልከቱ።
[349] Arch bishop Peter'Huillier, The Church of the Ancient Councils, p. 31
[350] Chistology of the Later Fathers, Editor, Edward R. Hardy the Letter of Arius to Eusebius of Nicomedia. p. 329

ይህ ሁኔታ የኒቅያ ጉባኤ እንዲካሄድ አስገደደ።[351] ጉባኤው ወልድ በአካልና በግብር ከመለየቱ በቀር፣ የአብ ሁለተኛ አካል በመሆን፣ መጀመሪያም መጨረሻም ሳይኖርበት በዘላለማዊነት የነበረ፥ ያለና የሚኖር፥ ፍጹም ሰው ሁኖ ግን ዓለምን አዳነ የሚለውን ሃይማኖታዊ ውሳኔ አስተላለፈ። የሃይማኖታችን መግለጫ "ጸሎተ ሃይማኖት" የዚህ ጉባኤ መግለጫ ነው።[352] ሲኖዶስ ማለት ይህን ውሳኔ በኃላፊነት የሚያስጠብቅ ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሲኖዶስ ሃይማኖት አስጠባቂ ብቻ ሳይሆን፣ በየጊዜው እየተሰበሰበ የቤተ ክርስቲያንን ችግር እየመረመረና እያጠና መመሪያ የሚያ ወጣ ጭምር ነው።[353]

በኒቅያ ጉባኤ በርካታ የቤተ ክርስቲያን መመሪያዎችና ድንጋጌዎች ወጥተዋል። የፍትሐ ነገሥት መቅድም ስለ ኒቅያ ጉባኤና ስለ ወሰኑት የቀኖና ብዛት እንዲህ ይላል፤

"ለክርስቲያን ነገሥታት መጀመሪያቸው የሆነ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በነገሠ በአሥራ ዘጠነኛው ዓመት በኒቅያ ሰብሰባ የተደረገበት ነው፤ ቍጥራቸው ሦስት መቶ አሥራ ሰምንት ኤጲስቆጶሳት ነው፤ አሊህም ከሁለት ሽህ ሦስት መቶ አርባ ኤጲስ ቆጶሳት ውስጥ እን ደተመረጡ ተነገረ። አርዮስ ወልድ ፍጡር ነው ባለ ጊዜ፣ በእርሱ ክህደት ምክንያት የተሰበሰቡ ናቸው። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳ ሳት አለ እስክንድሮስ ተከራክሮ ረታው። እርሱን በማውገዝና በመለየት ማኅበር ከእርሱ ጋር ተባበሩ። የቀናች ሃይማኖት ያለችበትንም መጽሐፍ ጻፉ። ክፍርድ በኋላም ኣጅግ የበዙ ቀኖናትን ጻፉ፣ በዚች መጽሐፍም ሁለት ክፍሎች አሉ፤ ከእነርሱ የአንዱ ቍጥር ሃያ ቀኖና ነው[354] ይላል።

በብዙ አርቶዶክሳውያን፣ ተቀባይነት ያላቸው ሃያ ቀኖናዎች ናቸው፤ እነዚህ ሃያ ቀኖናዎች የሚያተኩሩት በቤተ ክርስቲያን ከህነታዊ አስተዳደር መዋቅርና ሥርዓት ላይ ነው፤ በሊቀ ጳጳስ ፒተር ምደባ መሠረት ሃያዎቹን ቀኖናዎች ርእስ በርእስ ብንመድ ባቸው የሚከተለውን ምድብ ይይዛሉ።[355]

ቀኖና አንድ፥ ሁለት፥ ዘጠኝና አሥር፣ ከክህነታዊ አገልግሎት አን ጻር ይመደባሉ፣ ቀኖና አራት፥ አምስት፥ ስድስትና ሰባት ደግሞ ከክህነታዊ አገልግሎት ሥልጣንና አስተዳደራዊ መዋቅር አንጻር ይታያሉ። ቀኖና ሦስት፥ አሥራ አምስት፥ አሥራ ስድስት፥ የክህ ነትን ሕይወትና የሥልጣን ደረጃ ይዘዋል። ቀኖና አሥራ አንድ፥ አሥራ ሁለት፥ አሥራ ሦስትና አሥራ አራት፥ ከክርስትና ሕይወት ለወጡ የመመለስና የንሥሐ ሁኔታ በከፉ ቀን የከዱ ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚመለሱ ያሳስባል።

ቀኖና ስምንትና አሥራ ዘጠኝ፣ ሕጋዊ ያልሆነ ክህነትና ጥምቀት ምን መሆን እንዳለበት መንገዱን ያሳያል። ቀኖና አሥራ ስምንትና ሃያ ከቅዳሴ አገልግሎት ጋር የሚሄዱ ሲሆን፣ ዲያቆን ምን ማድ ረግ እንዳለበትና እንደሌለበት የሚያስረዱ ቀኖናዎች ናቸው።[356] የሌሎችን ጉባኤያት ቀኖናዎችና ውሳኔዎችን ሳንጨምር፣ የኒቅያን ጉባኤ ውሳኔና ቀኖና ብቻ እንኳ አሁን ከምንጠቀምበት የቤተ

[351] The Church of the Ancient Councils J.N.D.Kelly, Early Christian Creeds third Edition, p. 205
[352] Ibid
[353] Lewis J.Patsavos, Spiritual Dimensions of the Holy Canons, p. 36

[354] ፍትሐ ነገሥት መቅድም ይመልከቱ።
[355] The Cchurch of the Ancient Councils, p. 30
[356] Ibid, 31

ከርስቲያን ሥርዓት ጋር ስናነጻጽረው በሙሉ በአገልግሎት ላይ ውሎአል ማለት እንችላለን።[357] ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ካሰብንና በእሷም እንኑር ካልን፣ በዚሁ ሕግ መቀጠል አለብን። አለበለዚያ የሚጥመንን እየወሰድን፣ እሚገሥጸንን የምንተው ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥጋዊ ጥቅም እየተጠቀምን ነው እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገልን አይደለም::

እስከ አሁን ከቀረበው ገለጻ፣ ለመረዳት እንደሚቻለው፤ ቀኖና ለቤተ ክርስቲያን አቋም ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ መጠነኛ ግን ዛቤ አግኝተናል:: በመሆኑም ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ መሠረት ለሆነው ለዚህ ሥርዓት ሁሉም መሥራትና መገዛት አለበት። ይህ ማለት የጳጳሳትን ክብር አስጠብቁ ማለት ብቻ ሳይሆን፣ ጳጳሳትም ለዚህ ሥርዓት ራሳቸው እየተገዙ ሕዝቡም እንዲገዛ አጠንክረው መሥራት አለባቸው ማለት ነው።[358] ይህ ሥርዓት ካልተጠበቀ፣ የጵጵስናው ሥልጣን ብቻውን ምንም ሊያደርግ አይችልም። ምክንያቱም የጵጵስናው ሥልጣን ሊሠራ የሚችለው የቀደምት አባቶቻችን ቀኖና ሲጠበቅና ውሳኔያቸው ሲከበር ብቻ ነውና።

መጀመሪያውኑም ጵጵስና ያስፈለገውእኮ ይህንን ሥርዓት በአግ ባቡ ለማስጠበቅ ነው።[359] ቀኖናውን የሚጥስና የማይጠብቅ ጳጳስ ሥልጣኑን በራሱ የሻረ ማለት ነው። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ የሚያ

[357] Ibid

[358] On the Apostolic Tradion, p. 60

[359] Creeds of the Churches, Eidited by Joh H. leith, pp. 22-24

ስገነዝበን፣ በዘመናችን የትም ይሁን የት ያሉ ጳጳሳት ከላይ የተመ ለከተውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸው አክብረው ምእመናንም እንዲያከብሩ የማድረግ የአባትነት ግዴታ አለባቸው።

3. ለፖለቲካዊ ተጽዕኖ ቀኖናው የሰጠው መፍትሔ፤

በፖለቲካ ሳቢያ በቤተ ክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ደርሷል። በዘመናት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንና ፖለቲካ (መንፈሳዊና ሥጋዊ) እያልን በምንጠራው ተቋማት መካከል ፍጥጫው ቀጥሏል:: የፍጥጫው ምክንያትም፣ ዓላማና ግባቸው፥ መነሻና መድረሻቸው እየብቻው የሆነ፥ ሁለት የተለያዩ ድርጅቶች በአንዲቱ ዓለም ላይ፥ አልፎ አልፎም በአንድ ሰው ላይ ስለሚከናወኑ እንዲሁም፥ አስፈላጊና ወሳኝም ስለሆኑና፥ በአንድ ሰው ሕይወት ላይም ቦታ ስለሚኖራቸው ነው።

ሰው መንፈሳዊ እንደ መሆኑ መጠን መንፈሳዊ ማንነቱን የሚገል ጽበት ሁኔታ እንዲመቻችለት ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛ ነጻ መሥመር ይፈልጋል። ለዚህ ዓላማው ደግሞ የፖለቲካ ነጻነት ይፈልጋል። ይህን ነጻነት ለማግኘት ሲል ከፖለቲከኞች ጋር ፊት ለፊት መጋጨት የማይቀር ነገር ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን:- *"ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ አኔ ወደማሳ ይህ ምድር ውጣ"*[360] ብሎ ከጠራው በኋላ፤ የአብርሃም ገዥ እግዚአብሔር ብቻ ነበር። በየትኛውም ቦታ ላይ አብርሃም ለሰው ተገዛ የሚል ቃል አናገኝም።

[360] ዘፍ 12: 1

እሥራኤልም ከነጻነት በኋላ በዚሁ መርሕ ተጠብቀዋል፤ የግብጽ ነጻነት የፖለቲካ ነጻነት ነበር።[361] በእሥራኤል ታሪክ ውስጥ በሌ ሎች የመገዛቱ ነገር የሚመጣው እነሱ በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ሲለዩ ብቻ ነበር።[362] በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምንረዳው እግዚአብሔር ነጻ ያወጣው ሕዝብ አለ፥ የእግ ዚአብሔር ሕዝብ በነጻነት የሚኖርባት ምድር አለች፥ የእግዚአ ብሔር ሕዝብ የሚመራበት ሕግ አለ። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሾማቸው ነገሥታት አሉ።[363] ንጉሡ ሁልጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር ወኪል ነው። በአገሪቱ ሕግ መተላለፍ ሲኖር እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ለንጉሡ መልእክቱን ያስተላ ልፋል።[364]

መጀመሪያ ምድራዊ ሰዋዊ ንጉሥ የፈለጉት የእግዚአብሔር ሕዝ ቦች የእግዚአብሔርን ንጉሥነት ንቀው እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል።[365] በኋላም እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ ያለውን ዓላማ በነገሥታቱ አማካይነት ለመፈጸም ምን ያህል ይናገር እንደ ነበር የነቢያት መጻሕፍት በሰፊው ይዘረዝራሉ።[366] በኋላም የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ እግዚአብሔር የላከውን የሰላም ንጉሥ ክርስቶስን የቤተ መቅደሱ ሰዎች ከቄሣር በቀር ንጉሥ የለንም።[367] በማለት

[361] ዘፀ
[362] 1 ሳሙ
[363] Paul Nadim, Tarazi, The Old Testament, Introduction, p. 159.
[364] Ibid
[365] Ibid,162
[366] Paul Nadim, Tarazi, The Old Testament, Introduction to Prophetic Traditions, p. 25

[367] N.T.wright Jesus, The Victory of God, pp. 250-251

ለዓለሙ ባለ ሥልጣናት አሳልፈው በመስጠት ክርስቶስን አሰቅ ለው መግደላቸውን ስናጤነው፣ የሰዎች ሥርዓት ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በጣም ተቃራኒ እንደ ሆነ ለመረዳት እንችላለን።[368] አሁንም በዚህ ንዑስ ክፍል ፖለቲካ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሰውን ተጽዕኖና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ተጽዕኖ የሰጠ ውን አጸፋ በመጠኑ እንመለከታልን።

በየትኛውም ጉባኤ የተቀነኑት ቀኖናዎች ዋና ዓላማቸው የእግዚአ ብሔርን ቤተ ክርስቲያን ማስጠበቅ ነው።[369] በተለይም በመጀመ ሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ ነገሥታት እየተሳደደች በነበረችበት ጊዜ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፖለቲካውን በከፍተኛ ደረጃ ተቋቁሞታል።[370] ቤተ ክርስቲያን እያደገች ስት ሄድ መሪዎቿን በሥልጣን በማታለል ለመጥለፍ ቢሞክሩም የተጠ መደላቸው አልነበረም። በኋላ ቤተ ክርስቲያን ነጻነት ስታገኝ ግን ነገሥታት አንዳንድ መንፈሰ ደካማ ጳጳሳትን በመጠቀም ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።[371] *Creeds,Councils and Controvsies Documenets illustrating the history of the church,AD 337-461* በሚል ርእስ አንድ መጽሐፍ ተጽፏል። ይህ መጽሐፍ የሃይማኖት መግለጫ ሰነዶችን፣ ውሳኔዎችንና ሲኖዶሳዊ ቀኖና ዎችን ይዟል።[372]

[368] Ibid
[369] Arch bishop Peter'Huillier, The Church of the Ancient Councils
[370] The Apostolic Creeds on The Apostolic Tradition, p. 71
[371] *Creeds, Councils and Controversies, Documenets Illustrating the History of the Church, A. D 337-461*
[372] Ibid, 30-36

መጽሐፉ ከኩኒስታንቲን ለአከሱም ነገሥታት፥ አትናቴዎስን አስመ ልከቶ በመጽሐፉ የተዘረዘሩት ብዙዎቹ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጥቅም የሰጡ ቀኖናዎች ሲሆኑ፤ በዚያው ልክ ደግሞ በቤተ ክርስ ቲያን ላይ የፖለቲካ ተጽዕኖ ምን ያህል ሚና እንደተጫወተ ያብራ ራሉ፤ በመሆኑም፣ የሳረዲካ ቀኖና በሚል የተዘገበ ቀኖና፣ የጳጳሳት ቦታ መልቀቅ ከትንሽ ሀገረ ስብከት ወደ ትልቅ ሀገረ ስብከት፣ እን ዴት መዛወር እንዳለበት ይገልጽና፣ ይህ ሁሉ መሆን ያለበት ግን በጳጳሳት ስምምነት መሆን እንዳለበት ያስረዳል:: በዚሁ የሠነዶች ስብስብ መጽሐፍ ላይ፣ በከፍል በከፍል ከሁለት መቶ ስድሳ አንድ በላይ የእምነት መግለጫዎችና ቀኖናዎች፤ ተዘርዝረዋል።

ለምሳሌም ያህል በአንጾኪያው ጉባኤ አትናቴዎስ በአርዮስ ተከታ ዮች ላይ ያቀረበው ሙግት አንጾኪያ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት በማለት በሁለተኛው ምድብ አትናቴዎስና የምሥራቅ ጳጳሳት በተ ባለ ክፍል ላይ የተዘረዘረ ሲሆን፤ የመሚገቻ መብቱን የሰጠው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ያብራራል።[373] ስለዚሁ ጉዳይ በተ ጻፈ ደብዳቤ ተመዝግቧል።[374]

ይኸው ደብዳቤ በመጀመሪያው አንቀጽ የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጥና ይህ ታላቅ አምላክ በአከሱማውያኑና እነሱን በመሰሉ መገለጡ፣ ምን ያህል ትልቅ ነገር እንደ ሆነ በማብራራት ሁሉም እንደየተሳትፏቸው፣ እንዳላቸው እምነት፣ ከእግዚአብሔር በሚ ያገኙት ዕውቀትና በሚያደርጉት እውነተኛ ፍትሕ፣ ልዩነት የላቸ ውም:: በመሆኑም እነሱም እንደ ሮማውያንና እንደ ሌሎቹ እው

[373] Ibid, 31
[374] Ibid, 37

ነተኛ ፍርድ ሊሰጡ እንደሚገባ በመግለጽ፤ የአከሱም መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ያገኙት ከአትናቴዎስ እንደ መሆኑ መጠን፥ ወደ አትናቴዎስ የሥልጣን መሻር ይሄዳል።

አትናቴዎስ በተለያዩ ውንጀላዎች የተከሰሰ በመሆኑና ለተከሰሰ በትም በቂ መልስ ስለሌለው ከእናንተ በቀር ሁሉም ጠልቶት በመንከራተት ላይ ይገኛል። በመሆኑም፣ በምትኩ ታላቁ ጊዮርጊስ ተሹሟል። ፍሬ ምናጦስ የጵጵስናው ሥልጣን እንዲሠራ ካስፈለገ ወደ ግብጽ በመሄድ ከህነቱን አሳድሶ ይቀጥል። ያ ካልሆነ ፍሬም ናጦስ ለከህነቱ ቀጣይነት ዋስትና እንደማይኖረው በመግለጽ የነገ ሥታቱ ፍራቻ አትናቴዎስ ወደ አከሱም ሂዶ ሕዝቡን ካሳመነ የሠ ራው ጥፋት እጅግ የከፋ ይሆንና ቤተ ክርስቲያንም እውነተኛውን ትምህርት ልታጣ ትችላለች በማለት፣ ፍሬምናጦስ ወደ ቤቱ እንደ ሚመለስና ከተከበረው ጳጳስ ትእዛዝን በመቀበል፣ መልካም ሥራ ውን እንደሚሠራ ያለውን ተስፋ ይገልጻል። [375] የደብዳቤው አጠ ቃላይ ሐሳብ እንጂ ሙሉ ትርገሙ አልተቀመጠም። ለተነሣንበት ነጥብ ግን በቂ ግንዛቤ ይሰጠናል:: በመሆኑም መሠረተ ሐሳቡ በሚከተለው መልክ ተቀምጧል።

1. ቅዱስ አትናቴዎስ ፖለቲካው ያቀረበበትን የሐሰት ክስ ያስሠረዘ ውና ወደ ሥልጣኑ የተመለሰው በቀኖናውና በሲኖዶሳዊ ጉባኤው በተወሰነው የእምነት መግጫ ነበር:: ይኸውም የኒቅያው ጉባኤ ያወገዘው የአርዮስ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ቦታ እንደሌለው በማስረዳት *"በአንጾኪያ አትናቴዎስና የምሥራቅ ጳጳሳት"* በሚል ስያሜ የተቀመጠው ጉባኤ፣ የአትናቴዎስን ጉዳይ የያዘው

[375] Ibid, 38

አትናቴዎስ አርቶደክሳዊት እምነትን ተከትሏል ወይስ አፋልሷል? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ነበር::[376]

በጉባኤው ላይ የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫ ተቀባይነት አግኝ ቷል:: ከዚህ ተነሥቶ አትናቴዎስ በሰጠው መልስ፥ እምነቱን ያፈ ረሱትና አባቶች ያስቀመጡትን የእምነት መግለጫ የረገጡት አርዮ ሳውያን እንጂ አትናቴዎስ እንዳልሆነ ተገለጠ። አትናቴዎስ በጉባኤ የተወሰነውን ሃይማኖት ከጠበቀ ቀኖናው የአትናቴዎስን ክህነት ለማገድ አይችልም:: በመሆኑም ቀኖና ፖለቲከኞች በፖለቲካ ድጋፍ የሰጧቸውን የመናፍቃንን ሥልጣን ሲገፍ፣ የቤተ ክርስቲ ያንን ክብርና ሃይማኖታቸውን ለጠበቁት እንደነ አትናቴዎስ ላሉት ግን ሥልጣናቸውን አጸደቀ። ቀኖና በአዎንታዊ ጎኑ ይህን ሲያደ ርግ በአሉታዊ ጎኑ ግን ቢዛንታውያኑ ለአከሱማውያኑ እንዲጽፉም እድሉን የሰጣቸው፤ በሁሉም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን የሚ ለው ሲኖዶሳዊ ወሳኔና ቀኖና ነው።

2. በአዎንታዊ ጎኑ ደግሞ ለአከሱም ነገሥታት ቤተ ክርስቲያን መመራት ያለባት በመንፈሳዊ ቀኖና እንደ መሆኑ መጠን፥ የቢዛንታውያንን ጣልቃ ገብነት እንዳይሰሙ ከማድረጉም በላይ የዚያን ጊዜው አቋማቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ጋር ታሪካዊ አንድነቷን ጠብቃ እድትኖር አድርጓል:: ከዚህም ጋር አትናቴዎስ ወደ ቦታው እንዲመለስ፣ ልዩ ልዩ ጉባኤ እንዲያደርግና እንዲረታ እድሉን የሰጠው ቀኖናው ነው። ስለዚህ ቀኖናው፣ ፖለቲካ በቤተ ክርስቲያን ላይ ላመጣው ተጽዕኖ ከፍተኛ መከላከል በማድረጉ፣ በተለያዩ ነጻ አገሮችና

[376] Ibid, 34

መንግሥታት ሥር ያለችው ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንዲት በሁሉም ያለች ቤተ ክርስቲያን ተጠብቃ እያደገች፥ እየሰፋች፥ እየበረታች፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈች ትኖር ዘንድ፣ ቀኖና ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደ ነበረው ያስረዳል።*[377]

ባለንበት ዘመንም ቢሆን ከኢትዮጵያ በቀር የየትኛውም አገር መንግሥት ሕግ ይህን ዛሬም አይቃወምም፤[378] የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ለሃይማኖት የሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ነጻነት ጥሶ፥ ቀኖናውንም አረግጦ፥ በፈጸመው ሕገ ወጥ ተግባር ምክንያት፣ አሁን ያለው ቀውስ ተፈጠረ።[379] ቀኖና ግን አሁንም በሕገ ወጦች የሚደረገውን ተጽዕኖ ያወግዛል።

3. ቀኖና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነትን ያወግዛል። በአንጻሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለልጆቿ ፍትሕና ነጻነት እንድትቆም ያበረታታል:: በክርስትና ታሪክ፣ የቤተ ክርስቲያን መለያዋ ለድሆችና ፍትሕ ላጡ ጥብቅና መቆሟ ነው።[380] በአንጻሩ ደግሞ በሀብትና በሥልጣን ጣልቃ በመግባት የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ለግል ጥቅም ለማዋል የሚተባበሩትን ሥጋውያን ጳጳሳትና ካህናትን ያወግዛል:: ይህን በተመለከተ በፍትሐ ነገሥት እንዲህ ተጽፏል ።

[377] *Creeds,Councils and Controvrsies Documenets Illustrating the History of the Church, AD337-461* በዚህ መጽሐፍ በጣም ብዙ ጉባኤያትና የጉባኤያት ቀኖናዎች ተሰብስበዋል በቀኖናዎችና በጉባኤዎቹ የሚታዩት ቀኖና ለቤ ክርስቲያን መሰፋፋት ፤ ለቤተ ክርስቲያን ነጻነትና ጥንካሬ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳለው የሚያስረዳ ነው*

[378] የአሜሪካን ሕገ መንግሥት መመልከት ይቻላል

[379] የዮሐንስ አፈ ወርቅ የሕይት ታሪክ ስለ ደሆች ከሰበከው ስብከት መመልከት ነው

[380] የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያንን ማየት ይቻላል። ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 መንግሥት በሃይመኖት ጣልቃ አይገባም የሚለውን ጥሶ ነው ያደረገው

"እሾማለሁ ብሎ ከውጭ ሰዎች ጋር ወይም ከዓለም መኳንንት ጋር ስለ ቤተ ክርስቲያን ሹመት ይረዱት ዘንድ የተማፀነ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር በዚህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊያዋርድ በማይገባ በላያቸው ሊታበይ ወይም የባልንጀራውን ቤተ ክርስቲያን ሊወ ሰድ ፈልጎ የተማፀነ ቢኖር ፈጽሞ የተወገዘ ነው። በዚህ ሥራ የሚረዱት ሁሉ ፈጽመው የተወገዙ ናቸው"።[381]

ይህ ቀኖና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ምክንያት አድርጎ፣ ለራስ ክብርና ዝና በልዩ ሥልጣንና ጥቅም ለተጠቃሚ መስጠት የተወገዘ መሆኑን ያስረዳል። በዚህ መልክ ሥልጣን ይዘው ሕጋ ውያን ነን የሚሉት ሁሉ፣ ቀኖናው ስለማይደግፋቸው ወይ አጭበ ርብረዋል ወይ በጉልበት ተጠቅመዋል። ይህን ዓይነት ሥራ፣ የሚ ሠሩ ሰዎች ከህነታቸውን እንዲያጡ የሚያደርገው ዋናው መመ ዘኛ ነው። *"እመቦ ኤጲስ ቆጶስ ዘተማኅፀነ በመኳንንት ወበሥዩ ማነ ዝንቱ ዓለም ከመ ይርድኦ ላዕለ ሢመተ ቤተ ክርስቲያን ውእቱ ርጉም ወውጉዝ ወይትመተር እምቤተ ክርስቲያኑ ለእግዚ አብሔር።"*[382]

ቀኖና ቤተ ክርስቲያን፣ በጉልበት፥ በብልጠት፥ በገንዘብ ሥልጣን የያዙ ሰዎች ለሚያሳድጇቸውም የስደት ከለላና ክብር ይሰጣል። ከህነታቸውም በስደት ምክንያት ተቀባይነት ሊያጣ አይችልም፤ እንዲያውም ከክብር ላይ ክብር ያስጨምራል። ይህን ይበልጥ ለመረዳት ቀጣዩን መመልከት ጠቃሚ ነው።

[381] አንቀጽ አምስት፣ ረሰጣ 24 ቍ.178
[382] አብጥሊስ፥ አንቀጽ 29

"ኤጲስ ቆጶሱ የሚሰደድበት አገር አሰኪያጣ ድረስ ደርሶ፥ ምክን ያቱ በሚያሳድዱት ጊዜ ቢሆን፥ በዚህ ጊዜ ይገባዋል፤ ንጽሕናውና የአስተዳደሩ ችሎታ ሃይማኖቱም በዚህ እንዳልተለወጠ ካወቁ፣ ወደ ሌላይቱ ሊሰዱት ይገባዋል። ያፈልሱት ዘንድ የሚበቃ ከሆ ነም ወደ ከፍተኛ መዓርግ ያውጡት፣ ከቦታው የወጣ በራሱ ፈቃድ ኣይደለምና"[383] በማለት ያብራራዋል።

በዚህ ቀኖና መሠረት ስደት የጵጵስናን ሥልጣን አያስቀርም፤ ቤተ ክርስቲያንን ገንጥሎ መጠቀሚያ አስካላደረገ ድረስ። ቤተ ክርስ ቲያንን ከገነጠለ ግን ሥልጣኑም አጠያያቂ ነው። ገነጠለ ማለት ያችን ቤተ ክርስቲያን አላውቅም ብሎ፣ የእርሱን ሥልጣን ብቻ መሠረት አድርጎ ቤተ ክርስቲያኒቱን የግል መጠቀሚያ ማድረግ ማለት ነው። ከዚህም ጋር መገንዘብ እሚገባው መሰደድ ብቻውን ሕጋዊ ሊያደርግ አለመቻሉን ነው። ስደቱ ለቤተ ክርስቲያን ሳይ ሆን የራስን ስሜት ለመግለጽ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያንን መብትና ሕጓን ማስከበር አይደለምና ሊታሰብበት ይገባል።

በዲዲስቅልያ ስም የተመዘገበው ቀኖና፣ ጳጳሳት ያለ ፍርሃት ማስተ ማር እንዳለባቸው ያዝዛል። በዚህ ጊዜ በፖለቲከኞች መሳደድና መጠላትን ያስከትል ይሆናል፤ ሁኖም ይህ ሁኔታ ከሃቅ መራቅ አግባብ እንዳልሆነ ቀኖናው ያስጠነቅቃል። ይህም ራስን በመግ ዛትና ዝቅ በማድረግ መሆን አለበት።

[383] አንቀጽ አምስት ቍጥር አንድ መቶ ጎምሳ ዘጠኝ ኒቅያ፤

4. ሥልጣነ ክህነት ከቀኖና አኳያ ሲታይ፤

ቀኖና የሕጋውያን አባቶችን የክህነት መብት ያስጠብቃል፤ ሕገ ወጦችን ደግሞ ከሥልጣናቸው ይሽራል። በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከተጠቀሱት መሠረታዊ አንቀጾች አንዱ የሥልጣኑ መሻርና አለመ ሻር መብት ነው። እንደ ማንኛውም የክህነት አገልግሎት ሁሉ ለጵ ጵስናም፥ ለጥትርከናም፥ ከሥራና ከሥልጣን ለመታገድ የሚያስ ችሉ ምክንያቶች አሉ። ከዚህ በታች የቀረቡት ነጥቦች ሥልጣን ከህነትን ከሚያሽሩ ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሀ/ በጉቦ የተከናወነ ሢመት፤

"እመሂ ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ አው ዲያቆን ዘይእኅዝ መዓርገ ሢመት በሕልያን ይሰዐር፤ ወይሰዐር ዘሢሞሂ ወይትመተር ለዝ ሉፉ እምሥርዓተ ክህነት"።
"ከኤጲስ ቆጶሳት ወይም ከካህናት ወይም ከዲያቆናት ሢመተ ክህነትን በጉቦ የተቀበለ ቢኖር ይሻር፥ የሾመውም ይሻር፤ እስከ ዘላለም ድረስ ከሥርዓተ ክህነት ይለይ"።[384]

ለ/ ክህነትን ለገል ጥቅም ማዋል፤

"ኢትሢጥ ወልድየ ሀብተ ክህነት ወጸጋ መንፈስ ቅዱስ በሤጥ፤ ወኢትንሣእ ላቲ ዐሰብ እም ቅድመ ትባርክ ኢእም ድጎሬሁ ... ዘወሀበ ወዘነሥአ ሕልያነ አልቦቱ ክህነት፤ ወውጉዝ በጎቤየ እነ ጴጥሮስ ዘአውገዝከዎ ለሢምን መሠርይ"።
"ልጄ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተቀበልከውን ሃብተ ክህነትን አት ሸጥ፥ ቡራኬ ከመስጠትህም በፊት ሆነ ከመስጠትህ በኋላ፥ በአሷ ሰጦታ አትቀበል"። [385]

ሐ/ የታይነም ሢመት፤

"ለአመ ተረክበ ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ አው ዲያቆን ክልኤ ጊዜ ተሠዲሞ ይሰዐር ውእቱኒ ወዘሢሞ"
"ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ሁለት ጊዜ ተሹሞ ቢገኝ ተሿሚውም ሿሚውም ይሻር"። [386]

መ/ ኑፋቄ ትምህርት፤

ለምሳሌ፤ እንደ ግኖስቲኮች ጋብቻ ርኩስ ነው ብሎ የሚያስተምር ካህን ቢኖር፥ ከሥልጣኑ መሻር እንዳለበት ፍትሕ መንፈሳዊ ያዝዛል።[387]

ሠ/ ሥልጣነ ለማግኘት መጣጸን

የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ለማግኘት የዓለም ባለሥልጣናት እንዲረዱት የተማፀነ ቢኖር አርሱ የተረገመ የተወገዘም ነው፤ ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም የተለየ ነው። [388]

---

[384] *ሥርዓተ ማጽው አንቀጽ 20*

[385] *ጦማረ ጴጥሮስ አንቀጽ 5: 2*

[386] *ማጽው አንቀጽ 31*

[387] *ፍትሕ መንፈሳዊ*

ረ/ **ዓለማዊ ባሕርያት፤**

"ኤጲስ ቆጶስ ለው ቀሲስ ለው ዲያቆን ዘየሐውር ኀበ ተውኔት ወያበዝኀ ስካረ ለይኅድግ፤ ወእመ ለኮ ይሰዐር"
"ወደ ጨዋታ ቤት የሚሄድ ስካርንም የሚያበዛ ጳጳስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ይተው፥ ባይተው ግን ከሥልጣኑ ይሻር።[389]

ሰ/ **በቁጣ ስሜት በፍጥነት ግውጠዝ፤**

በግል ቂም ምእመናንን ከቀኖርባን መከልከል፤ የጵጵስናን መዓርግ ትቶ ዓለማዊ ሥራን መሥራት፣ በጥንቆላ ሥራ ተሳታፊ መሆን፤ የጳጳሱን ጥሪ ንቆ የራስን ቤተ ክርስቲያን መመሥረት፤ እነዚህ ሁሉ ሥልጣነ ክህነትን የሚያሸሩ ሕጎች ናቸው::

ፍትሕ መንፈሳዊ እንደሚለው ስለ ጳጳሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተጨባጭ/በቂ ማስረጃ በትክክል ከተገኘ ሥልጥነ ክህነታቸው ይሻራል፣ የጥትርክና ሥልጣንም ይሻራል።[390] ይህ የሚሆነው ግን በእጅ ብልጫ ሳይ ሆን ምልዓተ ጉባኤ ተሰብስቦ የጉባኤው አባላት በአንድነት ሲሰ ማሙበት ነው።[391] ያ ካልሆነ እንደ ሽረት አይቆጠርም፤ በተሻረው

[388] *የአብጥሊስ፡ አንቀጽ 29*

[389] *ግጽው፡ አንቀጽ 32*
[390] *ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጸ ጳጳሳት ወካህናት ይመልከቱ።*
[391] *በአሁኑ ጊዜ በሕገ ወጥ መንገድ መፈንቅለ ሊድርጎ ሕገ ወጥ ፓትርያርክ የመረጠው የአዲስ አበባው ሲናዶስ በምልዓተ ጉባኤ ነው ምርጫውን ያካሄድኩት የሚለውን አባባል ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አይቀበለውም።*
በተጨማሪ የማይገለጥ የተከደነ የለም የሚለውን መጽሐፍ ከገጽ 45-48 ይመልከቱ።

ምትክ የተሾመውም ሹመቱ ሊጸናለት አይችልም።[392] የቤተ ክርስ ቲያን ሥልጣን፣ ከዓለማዊ ሥልጣን የሚለየው በግፊት ከሥርዓት ውጭ ቢወርድ እንኳ መንፈሳዊ ሥልጣኑ ሊነካ አለመቻሉ ነው።
[393] ስለዚሁ ጉዳይ የቀኖና ከለላ ሲያብራራ፤

"ይህች ሹመት በአንድ ዘመንና በአንድ አገር ለሁለት ሰዎች ልት ሆን አይገባም። ይህ በአንድ አገር ከተደረገ ግን አስቀድሞ ለተሾ መው ትጽና። ለሚገባቸው ሰዎች በሁለት ሀገሮች ብትሰጥ ልማድ ተገቢ በሚያደርገው አገር አስቀድሞ ለተሾመው ትጽናለት። ይህ በአንዲት ቦታ ቢሆን አስቀድሞ ለተሾመው ትጽና ። ይህ በአንድ ጊዜ ቢሆን ከእነርሱ አንዱም አንዱ ሊተዋት ይገባል። መራጮ ቹም አስቀድሞ የተሾመውን መምረጥ ይገባቸዋል። ተካከለው ቢገኙ በታቦቱ ፊት ቁመው በእጣ ይሁን" ። [394]

ይህ ቀኖና እስከ አሁን የሚሠራበት የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው:: ይህ ሕግ ባይኖር ኑሮ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ተጠብቆ አይቆ ምም ነበር:: እኛም ሥራዎችን መመዘን ያለብን በዚህ አንቀጽ መሠረት መሆን አለበት::ማንም ባለሥልጣን የሻረው ሕግ መብ ቱን ሊያስጠብቅለት አይችልም። በርካታዎች መቀበል የተሳናቸው ይህንን እውነት ነው። በመሆኑም ትውፊታዊ ቀኖናን ሳናከብር ቤተ ክርስቲያንን መምራት እንደማንችል ልናውቅ ይገባናል።

[392] *ዝኒ ከማሁ*
[393] *የአትናቴዎስን ታሪክ ያስታውሱ።*
[394] *ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 4 ቍ 70።*

5. ቀኖናና የኢ. አ. ተ. ቤ.ክ

ቀኖናን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ አር ቶዶክሳውያን ሁሉ በመመሪያነት ትጠቀምበታለች። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቀኖናዋ መሠረቱ ከእስክን ድርያው መንበረ ማርቆስ እንደ መሆኑ መጠን [395] የጥንቱን ትው ፊታዊ ቀኖና ታከብራለች። የቀኖና ምንጮቹ ከተለያዩ ክፍሎች እንደ ሆኑ በፍትሐ ነገሥት ተዘርዝረዋል። የፍትሐ ነገሥቱ ስብ ስብ ግን የሲቪልንም ሕግ ስለ ያዘ (ፍትሕ መንፈሳዊ፥ ፍትሕ ሥጋዊ) የቀኖናውን ዋጋ ያሳነሰው አስመስሎታል። [396]

የፍትሐ ነገሥቱ መቅድም የዘረዘረው የሐዋርያት ቀኖና፣ በቀለሚን ጦስ የተሰበሰበ፥ በራሳቸው በሐዋርያት የተዘጋጀ፥ በልዩ ልዩ ሊቃ ውንት የሚታመን ሲሆን፣ በኋላ በሊቃውንት ተደጋጋሚ እርማት እንደ ተደረገበት ይታመናል።[397] በእኛ ቤተ ክርስቲያን "ዲዲስቅ ልያ" በመባል የሚታወቅ፣ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጽሐፍ አለ።[398] ይኸው ዲዲስቅልያ የተባለው መጽሐፍ፣ በግብ ጻውያንም የታወቀ ቀኖና እንደ ሆነ ፍትሐ ነገሥት ይገልጣል።[399] የእንቆራ ጉባኤ፣ የቂሳርያ ጉባኤ፣ የግንግራ ጉባኤ፣ የአንጾኪያ ጉባኤ ቀኖናዎች በዚህ ዝርዝር ውስጥ አሉ።

[395] *Stephen J. Davis, The Early Coptric Papacy, The Egyptian Church and its Leadership in Late Antiquity, pp. 14-20*

[396] *ለምሳሌ የባሪያ ሽያጭ ሕግን በሚመለከት ብዙ የሚተቹ ሰዎች አሉ፣ ግን ይህ ሕግ ቤተ ክርስቲያንን ኣይመከትም፣ በዐለም አቀፉ የቀኖና ሰብስብም ይኸው ስብስብ አለ።*

[397] *ዲበ ኩሉ ዘወዴ ዶክተር ፍትሐ ነገሥት፥ ብሔረ ሕግ ወቀኖና. ገጽ 84-89.*

[398] *መጽሐፈ ዲዲስቅልያ በግእዝና በእንግሊዘኛ፣*

[399] *ፍትሐ ነገሥት መቅድም ገጽ 13*

ቀደም ሲል የተዘረዘሩት የቀኖና ምንጮች ጉባኤያት የከልል ጉባኤ የቀኖና ምንጮች ናቸው።[400] የመጀመሪያው የዓለም አቀፍ የኒቅያ ጉባኤ ቀኖናዎችን የዘረዘረ ሲሆን አሁንም የከልል ሲኖዶስ ጉባኤ ዎችን በብዛት ይዘረዝራል። [401] የሎዶቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች፥ የስርዲ ቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች፥ ከሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ሌላ የአቡሊ ዲስ ዘሮም ቀኖና ፥ የአባ ገብርኤል ዘእስክንድርያ ቀኖና፥ የታላቁ ባስልዮስ ቀኖና፣ በዚህ ቀኖና ውስጥ የከህነትና የጋብቻ ቀኖናዎች ተጠቃልለዋል።ከዚህ ሌላ ዓለማውያንና አሪታውያን ሕጎች በቀ ኖና ስም እንደ ገቡ የፍትሐ ነገሥቱ ስብስብ ያስረዳል።[402]

ለዚህ የኢትዮጵያ ቀኖና ምንጭ የሆነው ፍትሐ ነገሥት የያዘው ቀኖና ችግር የለውም። ችግር ያለው ያስመሰለው በስብስቡ መደ ባለቅ ምክንያት ነው። ሁኖም አርቶዶክሳዊ ቀኖና በሁሉም ያለች አንዲት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመግለጽና አንድነቷ ንም ለማስጠበቅ የበለጠ ውስብስብ ነው። [403] የኦርቶዶክስ ትውፊታዊ ቀኖና አንዲት በሁሉም ያለች የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ሥርዓት አንደኛው መመዘኛ የሐዋርያት ትውፊት ወይም አሠረ ሐዋርትን ቀጣይነት ነው።[404] ከዚያ አንጻር የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና አከባሪነት የማይናጋ ነው ማለት ይቻላል።

[400] *ዝኒ ከመሁ*

[401] *ዝኒ ከማሁ The Sevene Ecumenecal Ccouncils, A Bibliographical Introduction, XVIII*

[402] *ዝኒ ከማሁ*

[403] *John Meyendorff, Catholocity and the Church, p 112*

[404] Alexander Bogolepv, Toward an American Orthodox Church, the Establishment of an Autocephalous Orthodox Church, pp. 3-6

አሁን ባለንበት ወቅት ትውፊታዊ ቀኖናን አስመልክቶ በዓለም በሦስት የተመደቡ፣ አብያተ ክርስቲያናት አሉ።[405] እነዚህም አርቶ ዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት በመባል ይታወቃሉ። የኦር ቶዶክስን ቀኖናዊ ሕግ ውስብስብ የሚያደርገው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት በሠሩት መመራቱ ነው። [406] በተለይም በሁሉም ያለ ችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን በተለያየ አገርና ቦታ ሁና እንዴት አንዷ ከሌላዋ ጋር አንድ ትሆናለች? የሚለው ጥያቄ በቂ መልስ ማግኘት አለበት።[407] አርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ይህንን ጥያቄ የሚመልሱት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተጠቀመችበትን የቤተ ክስቲያን አመሠራረት መሠረት በማድረግ ነው።[408]

ለዚህ ጥያቄ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት አይጨነቁበትም። ካቶሊክ በጴጥሮስ ወንበር የተቀመጠውንና የክርስቶስ ወኪል የሆነውን ፖፕ እስከ ተቀበለች ድረስ ቤተ ክርስቲያን ናት።[409] የፖፑን ሥልጣን የማታውቅ ቤተ ክርስቲያን እንደ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ተቆጥራ፣ የክርስቶስ አካል ናት፤ የሚለውን ስያሜ ልታገኝ አትችልም:: ከዚህ በተጨማሪ የጴጥሮስን ሥልጣን ብቻ በመቀበል፣ የሌሎችን ሐዋርያት ሥልጣን የበታች አድርጋ

[405] Ibid
[406] Ibid. Meyendorff, Cahtolicity and the Church, p. 116
[407] *Erickson, The Challenges of Our Past, pp. 75-86*
[408] *Alexander bogolepv toward an American Orthodox Church the Establishment of an Autocephalous Orthodox Church, pp. 3-6*

[409] *Ibid. Veli-Matti/Karkkanene, An Introduction to Ecclesiology, p.27, Miroslav volf,After Our Likeness, The Church as the Image of the Trinity, pp. 221-230*

ትመለከታች። [410] በካቶሊክ እምነት ቤተ ክርስቲያን ለመባል የጴጥሮስን የሥልጣን የበላይነት መቀበል ወሳኝነት አለው።[411]

የፕሮቴስታንቱ ተከታይ ደግሞ የሐዋርያትን ሥልጣን ከምሥጢረ ክህነት ቀጣይነት አንጻር ስለማይቀበሉ፣ እንደ ትውፊት አድርገው የሚቀበሉት መጽሐፍ ቅዱስንና በክርስቶስ ማመንን ብቻ ነው። [412] በዚህ ምክንያት በፕሮቴስታንት አንዲት የተባለች ቤተ ክርስ ቲያን የለችም። ፕሮቴስታንቶች የተለያየ እምነትና ሥርዓት ያሉአ ቸው ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ናቸ።[413]

አርቶዶክስ ግን እንደዚህ አይደለም። የአንዲት በሁሉም ያለች፣ ቤተ ክርስቲያን ጽንሰ ሐሳብ ዓለም አቀፍ ጉባኤያትን መሠረት ያደረገ ነው።[414] እኛ የምንቀበላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት፣ በሁ ሉም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን የተባለችውን ነው፤ በዚያ ዘመን የነበሩትን መናብርት በእኩልነት በማስቀመጥ የአስተዳደር አንድነት ሳይሆን፤ የመንፈሳዊ አንድነት ቀኖናዊ መዋቅርን፣ የሐዋ ርያትን ሥልጣንና ትውፊትን፣ አርቶዶክሳዊ ሥርዓተ አምልኮንና ከአራቱ የአንዱን መንበር የበላይ ሥልጣን የሚያጠቃልል ዕውቅ ናን መሠረት ያደረገ ነው።[415] በዚህም መሠረት በአርቶዶክስ እም ነትና ሥርዓት ሁለት ዓይነት አስተዳደር ያላቸው ቤተ ክርስቲያ

[410] *Ibid*
[411] *Alexander Bolgolepov, p. 21*
[412] *Ibid*
[413] *Ibid*
[414] *Karkkanene, An Introduction to Ecclesiology*
[415] *Alexander Bolgolepov, Meyendorff Cahtoliciy, p. 102*

ኖች አሉ እነሱም፤ አንደኛው "አቶሰፋሎስ"[416] ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "አቶናሞስ" ይባላል።

አቶሰፋሎስ ማለት በበላዩ የማንም ሥልጣን የሌለበት፣ በራሱ የበላይ ሁኖ/ራስ ሁኖ/ የሚኖር ማለት ነው።[417] አቶናሞስ ማለት ግን በተወሰነ ደረጃ ራሱን የሚመራ ሁኖ፣ በመንፈሳዊ ሥልጣን አቶሰፋሎሶች ከሆኑት በአንዱ ሥር ያለ ማለት ነው። የሮም፥ የእስክንድርያ፥ የኢየሩሳም፥ የቁስጥጥናያ፥ የኤፌሶን፥ መናብርት አቶሰፋሎስ ናቸው።[418] ኢትዮጵያን ጨምሮ የሌሎቹ ግን አቶናሞስ ስለሆኑ፤ መንፈሳዊ ሥልጣናቸውን የእነሱ የበላይ ከሆኑት አቶሰፋሎሶች ከአንዱ በማግኘት ይመራሉ። ለምሳሌ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የበላይ ሁና ስትመራ የነበረው በዚህ ትውፊት መሠረት ነው።[419]

ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ተብሎ የተመሠረተው ቀኖና እየቆየ ግን እናት ቤተ ክርስቲያን ነን ለሚሉት ሥልጣን ማሳያና ጥቅም ማግኛ ሁኖ ለብዙዎች አብያተ ክስቲያናት እድገት እንቅፋት ከመ ሆኑም በላይ፣ ነጻ ወጥቶ ራስን ለመቻል ብዙ ዋጋ አስከፍሏል። ይህ ችግር የተከሠተው በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም። በጠቅላላው አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ

[416] *Erickson,The Challenge of Our Past, p. 110*
[417] *Ibid ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ ለንቀጽ አምሰት ቁጥር 40*
[418] *የግብጽ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳሳት መሾም አይችሉም፤ ጳጳሳቸውን ከአርሱ ወገን ይሹምላቸው ለንጂ የሚለውን ለንቀጽ በሥርዋጽ አሰገብታ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ስትገዛት የኖረችው፣ በዚህ ምክንያት ነው።*
[419] *ዝኒ ከማሁ*

ነበር እንጂ።[420] ሁኖም የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን የነጻነት መለኪያ መሠረት በማድረግ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነጻ ሲወጡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን ረጅም ጊዜ ወስዶባታል።[421] ነጻነት መለኪያ የሚባሉት፣ ምእመናን፥ ቋንቋ፥ በአገሩ ቋንቋ የተማሩ በቂ ካህናት፥ ትምህርት ቤቶችና ነጻ መንግሥትን ያጠቃለለ ነው።[422]

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ ነጻ ለመውጣት መመዘኛውን ያሟላች ሁና ሳለ፣ ነጻ ያለመውጣቷ ዋና ምክንያት፥ በአንድ በኩል የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተንኮል፣ በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያን ለቀኖና ያላቸው ከብር ነበር።*[423] ስለዚህ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የጠቀመበትም የጎዳበትም ሁኔታ መኖሩን ያሳያል:: ይህ ማለት ግን ቀኖናው ስህተት አለበት ወይም ነበረበት እያልን አይደለም። ስህተተኞች ቀኖናውን ያለአግባብ በመተረጎም ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት ሰዎች ናቸው:: ይህ ስህተት፣ ድንበር የለሽ እየሆነ መታየቱ ደግሞ በጣም አሳሳቢ ሁኗል።

በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በተለይ መንፈሳዊ አባቶች፥ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ከማሳወቅ ባሻገር ለምእመናን በተግባራቸው አርዓያ

[420] *Alexander Bogolepv, Toward an American Orthodox Church, The Establishment of an Autocephalous Oorthodox Church, pp. 3-6, Erickson, the Challenge of Our Past, p. 110*
[420] *Ibid ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ*
[421] *የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት ራስን የመቻል ,ታሪክ በቤተ ክህነት የተዘጋጀ መጽሐፍ*
[422] *ዝኒ ከማሁ ገጽ*
[423] *ዝኒ ከማሁ *በዚህ መጽሐፍ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሸፍጥና የኢትዮጵያውያን መንፈሳዊነት በብዛት ተንጸባርቋል።*

ሊሆኑ ይገባል ብለን እናምናለን። አሁን ያለብን ችግር በሕግ አለመስማማት ብቻም አይደለም፡፡ ችግሩ ሕግንም፥ ታሪክንም፥ እውነትንም መካድ ነው። በክርስትናውም ሆነ በፖለቲካው ያለው ችግር ሁሉም ከራሱ ሐሳብ በቀር የሌላውን ሐሳብ መቀበል አለመቻል ነው። በሕግ ያለመገዛት፥ ጀብደኝነት፥ ግትር አቋም፥ ይኸ ሁሉ መታረም ያለበት ነው።[424]

ሕጋዊ ነን ከሚሉት ወገኖችም ከእርስበርስ ገመድ ጉተታ ያለፈ ሥራ ይጠበቅባቸዋል። ብዙውን ጊዜ ሲታይ ያለው ችግር ቀኖና ያለመኖር ሳይሆን፣ ቀኖናውን አስፈጻሚው አካል በቀኖናው ሕግ ብቻ መመራት ሲገባው በማይጠቅም ግላዊ ስሜት መነዳቱ ነው፤ ማለትም ብዙ ጊዜ ቀኖናውን የምንጠቅሰው የቤተ ክርስቲያን ሕግ ሲሻር ሳይሆን የእኛ ግላዊ መብት ሲነካ እየሆነ መጥቷል። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ደግሞ ፈጽሞ መታረም የሚገባው ባሕርይ ነው።

6. <u>ቀኖናና ፖለቲካ በኢ. አ. ተ. ቤ.፤</u>

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንነቷ፣ ለቀኖና ተገዥ ናት፤ ቀኖናንም ታከብራለች። እንደ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያንነቷ ደግሞ የአገር ብሔራዊ አጀንዳ ሁና አገልግላለች። ሁለቱ ጉዳዮች፣ ሳይጋጩ ለብዙ ዘመናት እንዴት አብረው እንደ ሄዱ ስንመለከት ክርስትና በኢትዮጵያ የገባው በነገሥታቱ አማካይነት ሲሆን የፖለቲካ ማራመጃ ሁኖ

[424] ለሰደተኛው ሲኖዶስ <u>ድጋፍ ሰጭ ከሚቴ</u> ነን የሚሉት ግለሰቦች ያወጡትን ሰነድ ማየት በቂ መልስ ነው።

ለረዥም ጊዜ አላገለገለም፡፡ ከዚያ ይልቅ ራሱ የአገር አጀንዳ ሁኖ ተገልግሏአል፤ ማለትም እምነቱ ከገባ በኋላ እራሱ የሀገር አጀንዳ ሁኖ በፖለቲካ መልክ ተስፋፍቷል።[425]

ይህም ሲሆን፣ ዓለም አቀፋዊ ቀኖናን በማክበር፣ ቤተ ክርስቲያን ራሷን የመቻል እድል በነበራት ጊዜ ከዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ሳትለይ ቀኖናዊ ሥርዓትን መጠበቋና ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት መኖሯ፤ ለቀኖና ተገዥነቷን የሚያስረዳ ነው።[426] ነገሥታቱ ቤተ ክርስቲያን ሲሠሩ ለቤተ ክርስቲያን መሬት ሲሰጡ እምነታቸው ስለ ሆነ ነው እንጂ፣ በዚያ ሊወደዱ፣ ወይም ከሥልጣን ሊቆዩ አልነበረም። ትምህርቷና ሌላም ለሀገር የሚጠቅም ጉዳይ የሚደረገው በቤተ ክርስቲያን ቢሆንም ነገሥታቱ የሚያደርጉትን ሁሉ ለጽድቅ ብለው እንደሚያደርጉት ጠቋሚ ሐሳቦች አሉ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የበዓለ ሢመታቸው ዕለት ባደረጉት ንግግር ላይ ይህ ሐሳብ ተገልጿል፡፡ *"አባትዎ ቀዳማዊ ምኒልክ ቀዳማዊነቱን በሰም ብቻ ሳይሆን በዘመኑ አምልኮተ አግዚአብሔር ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ እንዲስፋፋ፣ በማድረግ ቀዳማዊ ሲሆን ፥ ግርማዊነትዎ ደግሞ ቀዳማዊነቱ በሰም ብቻ ሳይሆን ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን የከህነት ሥልጣን ወደ ኢትዮጵያውያን ተላልፎ ኢትዮጵያዊ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከኢትዮጵያውያን መካከል እንዲገኝ በማድረግ ቀዳማዊ ነዎት"*።[427] በማለት የነገሥታቱ ሚና በቤተ ክርስቲያን ምን ያህል የጎላ

[425] ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ሁለት ገጽ 67
[426] ዝኒ ከማሁ
[427] የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት ራስን የመቻል ታሪክ በቤተ ክህነት የተዘጋጀ።

እንደ ነበር መስክረዋል፡፡ በዚህም የተነሣ ከርስትና ለመስፋፋት ብዙ ችግር አልገጠመውም፤ ነገሥታቱ ቤተ ከርስቲያኑን አሠር ተው ሲገለገሉ፥ ሲጸልዩም የምናያቸው በእምነቱ ስለሚኖሩበት ነበር። ከርስትና በነገሥታት በመያዙ ምክንያት የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ሲያበቃ ቤተ ከርስቲያን ችግር ላይ የወደቀችው በሁለት መንገድ ነበር።

በአንድ በኩል ዋና ኃላፊነቱ የነገሥታቱ ስለ ነበር የተጠያቂነት ችግር አጋጥሟል። የሶርያ አርቶዶክስ ቤተ ከርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ኃላፊ በአንድ ወቅት ያሉት ይህንን ነበር ። *"የአምሰቱ አሐት አብያተ ክርስቲያናትን ጎብረት ለማስጠበቅ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያለ በነጻ መንግሥት የሚንቀሳቀስ አርቶዶክሳዊ ንጉሥ ያስፈልጋል"*፤ በማለት ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የነገሥታቱን ሥልጣን የሚቃወሙት ከፍሎች ቤተ ከርስቲያንን በጠላትነት ፈርጀዋታል።[428]
ለምሳሌም ያህል ዮዲት፥ ግራኝ፥ ደርግ፥ የወያኔ መንግሥት፥ ዋና ተጠቃሾች ናቸው።[429] አሁን ላለው ጥልቅ ችግር ግን ቤተ ከርስቲያን ራሷን የመምራት ችግር እንዳለባት ያስመሰለው ጎጂ ባህል በሕዝቡ አእምሮ ስለ ሠረፀ ነው። ለዚህ ማስጃ የሚሆነን፥ በውጭ አገር ባለችው ቤተ ከርስቲያን የሚገለገሉ ምእመናን ቤተ ከርስቲያንን የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ቅጥያ አድርገው መመ ልከታቸው ነው።*[430]

[429] ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፤ ትግላችን ገጽ 21
[430] የደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤልን የመተዳደሪያ ሕግ ፥ በየቤተ ከርስቲያኑ ያለውን ደንብ ሲመለከቱት መንፈሳዊና አስተዳደር ይላል፣ የደንቡ መሠረተ ሐሳብ የሚያሳየው ቤተ

በዘመናውያኑ ሊቃውንት ሐሳብ መሠረት ቤተ ከርስቲያን ሁለት ዓይነት አስተዳደር አላት ። አንደኛው መንፈሳዊ ሌላኛው ደግሞ ሥጋዊ። መንፈሳዊው የቤተ ከርስቲያንን ምሥጢራት የሚመለከ ተው ካህናትን ሲሆን፣ ሥጋዊውን አስተዳደር ግን፣ ምእመናን መያዝ አለባቸው ብለው ያምናሉ። ምክንያታቸውን ሲገልጡ፣ "ካህናቱ የመምራት ችሎታ የላቸውም" ይላሉ ።[431] አሁን ያለብንን የቀኖና ችግርም የምንመለከተው ከዚሁ አንጻር ነው። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ከርስቲያን ቀኖናን በማከበር ምክንያት ለአንድ ሺህ ስድት መቶ ዓመት ራሷን ያልቻለች ሁና ቆይታለች፤ ይህ ሊሆን የቻለው በሁለት ምክንያት ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡

<u>አንደኛው</u> ቀደም ብሎ እንደ ተገለጠው አርቶዶክሳዊ ቀኖናን በማ ክበር፣ ግብጻውያን በተንኮል ያስቀመጡትን ሕግ፣ እንደ እውነት በመቁጠር ለዚያ ተገዥ መሆን ሲሆን።[432]

<u>ሁለተኛው</u> የግብጻውያን ራስ ወዳድነትና ምቀኝት ከዚያም አልፎ ድክመት ያመጣው ተጽዕኖ ነበር ብሎ ማሰብ ይቻላል። ይህ ሁኔታ የዘመኑ ሥልጣኔና የንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ብርታት ታክሎበት፣ ነጻነት ከተገኘ ገና አርባ ዓመቱ ነው።[433] ስለዚህ ፖለቲካና ቀኖና በኢትዮጵያ ቤተ ከርስቲያን በእኩልነት ተስተናግደዋል። ይህን ስንል፣ የቤተ ከርስቲያንን ሥርዓት ማክበርም ሆነ ለፖለቲካው መርሕ አብረው በመከባበር ኑረዋል፤

ከርስቲያን፥ በሁለት አመራር የምትተዳደር ተቅዋም መሆኗን ነው ።
[431] ዝኒ ከማሁ
[432] ፍትሐ ነገሥት፥ ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቀኖጥር 50 ገጽ 30
[433] የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ከርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት ራስን የመቻል ታሪክ በቤተ ክህነት የተዘጋጀ።

አንደኛው በሌላው ተጠቃሚ ሳይሆን ለረዥም ጊዜ መኖራቸውን የሚከድ የለም።

7. የኢ. ኦ. ተ. ቤ. ክ/ስብን የመቻል ጥያቄ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ራስን የመቻል ጥያቄ ያቀረበችው በቅዱስ አጼ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት እንደ ነበር ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ *በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ* መጽሐፋቸው ገልጸዋል። ሁኖም በአቡነ ጎርጎርዮስ ገለጻ መሠረት ግብፃውያን ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ይልቅ ሥጋዊ ጥቅማቸውን ስላስቀደሙ ፈቃደኛ አልሆን ብለው እንደ ቀሩ ይገልጣሉ።[434]

ከዚህ ጊዜ በኋላ ስለ ራስ መቻል እንደ ዋና አጀንዳ ሁኖ የቀረበውና ተመዝግቦ የተገኘው በአጼ ዮሐንስና በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ነው።[435] ከዚያም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ተፈጻሚነት እንዳገኘ ሰነዶች ያስረዳሉ። ይህ ጉዳይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ያደረገው የዘመኑ ሁኔታ ቢሆንም በወቅቱ በቦታው የነበሩት ሰዎች ላደሩጉት ሥራ ምስጋና ይገባቸዋል። ነጻነቱን በዐይን ያዩ ሰዎች ያስቀመጡት ቃል ለዚህ ዋቢ ነው።

"እጅግ የሚገርመውና የሚያስደንቀው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኦርቶ ዘመን ሙሉ ተሰፋ ባለመቁረጥ

[434] አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 36

[435] ሉሌ መላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ ገጽ 134-136

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መብት ለማስገኘት፣ መታገላቸውንና በኦርቶ ዘመን ሱባኤ ያሰቡትን ከግቡ ማድረሳቸው ነው፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባደረጉት ሃይማኖታዊ ተሰፋ፣ ትዕግሥትና ፍቅር፣ የተመላበት ሰላማዊ ጥረት ነው፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ራስዋን የማስቻል ትግል አውን ሊሆን የቻለው። የኢትዮጵያ መብት ግን በሁለቱም አጎትማማች አገሮች ምንም ቅሬታ ሳይፈጠር በመከባበርና በመፈቃቀር ነው የተፈጸመው። ወንድማማችነትን ያጠነከረ በመሆኑ፣ በመላው ዓለም ድንቅ ሁኖ ታይቷል። ስለዚህም መንፈሳዊ ሰው ሁሉን ይመረምራል፤ አሱን ግን ማንም አይመረምረውም፤ የተባው ቃል በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደ ተፈጸመ ሰንመለከት በከሃሊነቱ ፈጥሮ በረድኤቱ ለሚመራቸው ልውል ለግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና ወሰን የለውም።[436] በማለት ግራሞታቸውን የገለጹት።

ይህንን ዐቢይ የመጽሐፉ ክፍል ሦስት፣ በተከታታይ በቀረቡት ሐሳቦች ማጠቃለል ይቻላል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁሉንም በሕጋዊ መንገድ ስላደረጉት ግብጻውያንን ለጠብ የሚያነሣሣ በር አልነበረም፤ ቀኖናዊ ሕግ የጠየቀው በሙሉ ተሟልቷል። ይህ አካሄድ ለዛሬ ሕገ ወጦች፣ ትልቅ ማሳፈሪያ የሚሆን ነው። ከዚህ ለመድረስ ግን ቀላል ጉዞ እንዳልነበር፣ የነጻነቱን ዝርዝር ጉዳይ የሚተርከው ጽሑፍ እንዲህ ይነበባል፤

[436] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት ራስን የመቻል ታሪክ በቤተክህነት የተዘጋጀ።

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተወላጆቹ ጳጳሳት በማግኘቱ ከሚሰማው ደስታ በላይ ከጎጃምና ከጎንደር፣ ከትግራይና ከኤሉባቡር፣ ከቀሩትም ከኢትዮጵያ አውራጃዎች ከሆኑት አገሮች ሁሉ ለከህነት የሚመጡ ሕጻናት ውኃ እየወሰዳቸውና አውሬ እየበላቸው በከንቱ ሙተው ይቀሩ ሰለ ነበር፤ ይህ ችግር ተወግዶ ሕፃናቱም ሆነ ሽማግሌዎቹ በየደረጃቸው ከህነትን ለማግኘት ሰለ ቻሉ ግርማዊ ነጉሠ ነገሥት በቤተ ከህነት በኩል ያደረጉትን ታላቅ ሥራ የማያደንቅና ፈጣሪውን የማያመሰግን የለም"።

ይህን ሐሳብ በሚገባ የሚገልጠው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖትና የሥርዓት መጽሐፍ፣ ለዚሁ ሥራ ተብሎ የታተመ መጽሐፍ ነው። ከላይ የቀረበውን ጥቅስ አስተውለን ብንመለከተው አጅግ ብዙ ስሜትን የሚነኩ ሁኔታዎችን በልባችን እናስተውላለን። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመንበረ ማርቆስ ሥር አንድትኖር <u>የሚያደርጋት</u> ቀኖና ስለሌለ *'አቶኖምስ'* ሁና በሊቀ ጳጳስ የምትመራ፤ ከእስክንድርያ ጋር አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሁና እንድትኖር ፍቀዱ፣ የሚለው ባለስድስት አንቀጽ ደብዳቤ በመልእክተኛ አማካይነት ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ልከዋል።

በደብዳቤው የተጠቀሱት ሐሳቦች በግብፅ ሲኖዶስና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስለሚኖረው መንፈሳዊ ግንኙነትና ሥልጣን፣ የገዳማት የጋራ ሥራ ልምድ፣ የወደፊት የጵጵስና ሥልጣን የሚቀበሉ መነኮሳት ዕውቀት የሚያገኙበት ትምህርት ቤት ስለ መከፈትና መጠቀም፤ ስለ ግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሚና ይገልጽና *"በማንኛውም ረገድ የእኛ ጥያቄ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመ ልካሙም ሆነ በመከራውም ሰዓት ምእመናኖቿን ያለችግር ጠብቃ*

ከእስክንድርያም ሳትለይ የምንኖርበት አኳኋን ነው የምንለም ነው"።[437] በማለት ለቀረበው ጥያቄ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የሰጠችው መልስ ግን *"ቀኖናና ሕጋዊ ትውፊት ሳይሆን፥ ረጅም ጊዜ በማታለል የገዛቸውን የግዛት ዘመን ነው"*፤ እንደ ሕግና ቀኖና አድርጋ ያቀረበችው። መልስ ሲነበብ"

አንዳንዶች ከቀረቡት ጥያቄዎች ሳያቋርጥ አንድ ሽህ ሰድት መቶ ዓመት የቆየውን ኦኗኗር አኳኋን፣ ለመለወጥ ያመሩ ስለሆኑ በነዚህ ጥያቄዎች ሰለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍርሃታችንን አንደብቀዎትም፤ አግዚአብሔር በነዚህ ሽህ ሰድት መቶ ዓመታት ሁሉ ኢትዮጵያን ጠብቆ አድኗታል። ያለከርከር በነዚህ ሽህ ሰድት መቶ ዓመታት የነበሩት ሰዎች ከእነዚያ ያነሰ የተማሩና ለኢትዮጲያም ከነዚህ ያነሰ የማያሰቡ አልነበሩም። ደግ ሞም ሰለ ኢተዮጵያ ሕዝብ፣ ሰለ ክብረዎና ሰለ እድገቷ ያለንን ጥልቅ የሆነ ፍቅራችንንና ታላቅ በን እድራንታችንን ግርማዊነተዎ ያውቃል[438] *"* በማለት ነበር እንደ ሕግና ቀኖና አድርጋ ያቀረበችው።

መልሱ የተጠየቁትን ጥያቄ ወደ ጎን ገሸሽ በማድረግ ነበር የተሰጠው፤ በዚህ መልስ ላይ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና አልተጠቀሰም፤ ይህንን መብት ኢትዮጵያውያን እንዳይጠቀሙ የሚከለክል ሕግ አላቀረቡም፤ ያቀረቡት ለኢትዮጵያውያን እንደሚጸልዩ ሕዝቡንም እን ደ ሚወዱ ብቻ ነው። ያ ደግሞ ሥራቸው እንጂ የጵጵስና ሥልጣን ስላገኙ መሆን የለበትም ያም ሆነ ይህ፥ ከዚህ ሁሉ

[437] ዝኒ ከማሁ

[438] ዘኒ ከማሁ

ውጣ ውረድ በኋላ ነው የራስን መቻል መብት የተገኘው። እስከ አሁን የተመለከትነውን ጥናታዊ ጽሑፍ ስናጠቃልለው፤

<u>አንደኛ</u> ቤተ ክርስቲያንን የሚያንቀሳቅሳት ሲኖዶሳዊ ጉባኤ መሆኑን፣ የዚህ ጉባኤ ሰብሳቢና አባላትን ሥልጣንና መብታቸውን ቀኖና ከለላ የሰጠውና የሚጠብቀው መሆኑን ነው። [439] ይህ ከተሻረ ግን፣ ጠቅላላ ቤተ ክርስቲያኒቱን መካድና ማፍረስ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል። ስለዚህ ሁላችንም ለግለሰቦች ሳይሆን ለሕጉና ለሥርዓቱ መቆምና ያን ሥርዓት ማስጠበቅ ግዴታችን ነው።

<u>ሁለተኛ</u> በቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ በሕገ ወጥ መንገድ በመቀመጥ ሥልጣኑን የያዙት ሰዎች፥ ቀምተው አንጂ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፈቅዶላቸው አለመሆኑን በግልጥ ማሳወቅ ነው::

[439] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 183 ይመልከቱ።

ክፍል አራት

በሰበካ ጉባኤያችን ማወቅና መሥራት ያለብን ጉዳዮች

ቤተ ክርስቲያናችን ባላት ቀኖና መሠረት፣ ኃላፊነቷን ለመወጣት በምታደርገው ያላሠለሰ ጥረት የሚገጥሙአት ዘርፈ ብዙ ችግሮ ችና መሥራት የሚገባን ሥራ፤ በዚህ ዐቢይ ክፍል ውስጥ በዝር ዝር ተብራርተዋል። ለዚህም ትምህርት ይሆነን ዘንድ፣ የሌሎች አገሮች አብያተ ክርስቲያናት ችግሮችና መፍትሄዎች ቀርበዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት የሚፈታተን ሥርዓተ ቀኖና የመጣስ ከፍተኛ ችግር ገጥሞናል። ይህንንም አሳሳቢ ችግር ለቤተ ክርስቲያናችን ተቆርቋሪ የሆኑ ጳጳሳት፣ ካህናትና ዲያቆናት፣ እንዲሁም ምእመናን ተባብረው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይህ ክፍል በዝርዝር ያስረዳል። በዚሁ መሠረት ገለጻው ቀጥሎ በተመለከቱት ስድስት ንውሳን ክፍሎች በዝርዝር ስለ ተብራራ አንብበን ይህንኑ በሥራ ላይ ለማዋል የጋራ ጥረት እናድርግ።

1. ከታሪክ ምን እንማራለን?
2. የቤተ ክርስቲያን ችግርና መፍትሄ ሰጭ ውይይት፤
3. የውይይቱ አቅጣጫ ሂደትና ጠቃሚ ነጥቦች፤
4. ለሕዝብ መገለጥ ያለባቸው ሁኔታዎች፤
5. ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች፤
6. ውይይቱ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ጥቅም፤

1. ከታሪክ ምን እንማራለን?

ከታሪክ እንደምንረዳው ቤተ ክርስቲያን ብዙ ዓይነት የተላያዩ ችግሮች ስትጋፈጥ ኑራለች፤ የችግሮቹ መነሻም የዓለም ፖለቲካ ተጠቃሚዎች በክርስትናውም ዘርፍ ውስጥ ረዳት መስለው መግባታቸው ነበር።[440] ቤተ ክርስቲያን፣ የዓለማውያን ነገሥታት ጣልቃ ገብነት ሰለባ የሆነችውም በቆስጠንጢኖስ ዘመን በተወሰደው እርምጃ ነበር።[441] ያ እርምጃ ብዙ የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ አባቶችን እንዳሳደደ፥ እንዳሳሳረና አዳንገላታ፤[442] ብዙ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ሰነዶች፣ ይህን እውነት ቁልጭ አድረገው ያሳያሉ።[443]

አሁን ባለንበት ዘመንም በእኛ ላይ የተደቀነው ችግር ቀደም ባሉት ዘመናትም በዓለም ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተከሠተ ችግር ነው። የችግሩ መነሻም የዓለም ፖለቲካ መሆኑ በዚህ ዙሪያ ላይ የተደረጉ ጥናቶች አረጋግጠዋል። ለምሳሌ የምናቀርባቸው፡-

- የሩሲያ አርቶ ዶክስ ቤተ ክርስቲያን፤
- የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፤
- የአንጾኪያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፤
- የአርመን አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፤

[440] *Timothy D. Barnes ,Athanasius and Constantius, Theology and Politics in the Constantian Empire, pp. 19-32*
[441] *Ibid J.Stevenson, Creeds, Councils and Controversies, Documents Illustratimg the Historyof the Chuch A. D 337-461, pp. 1-42,.Hohn Meyendorff Imperial Unity and Christian Divisions, p 39.*
[442] *Creeds, Councils and Controversies, Documents Illustratimg the History of the Chuch.*
[443] Ibid

እነዚህ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በፖለቲካ በተፈጠረው ችግር ምክንያት፥ በዚሁ መንገድ አልፈዋል።[444] አንዳንዶቹም እስካሁን በዚሁ ችግር ውስጥ አሉ። የፖለቲካውን ችግር፣ ማዕበል ተቋቁመው ከችግሩ የወጡት ሩሲያዎችና ካቶሊኮች ብቻ ናቸው።

<u>የሩሲያዎቹ</u> የችግር መነሻና ከችግር እንዴት እንደ ወጡ እደሚከ ተለው በመጠኑ እንመለከታለን። ችግራቸውን ከማየታችን በፊት የሩሲያ ቤት ክርስቲያንን ታሪክ ምንነት ገለጻ ማድረግ ስለሚያስፈልግ መጠነኛ ማብራሪያ እንመልከት፤ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች የታሪክ ሂደታቸውን በአምስት የታሪክ ጊዜ ምድቦች ይመድቧቸዋል።[445]

<u>የመጀመሪያው፤</u> የሞንጎላውያን ጊዜ የሚባለው ነው። ይህ ጊዜ የአዲሱ ክርስትና እምነት በሩሲያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሁኖ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የታየበት፣ የመጀሪያው የክርስትና መንፈስ ዘመን ይባላል።[446]

<u>ሁለተኛው፤</u> የታሪክ ጊዜ ይኸው የሞንጎላውያን ዘመን ሲሆን፣

[444] Steven Ozment, The Age of Reform pp. 1250-1550, An Intellectual and Religious History of Late Medeival and Reformation Europe, pp. 135-175.
[445] Dimitry Pospielovsky, The Orthodox Church in the History of Russia, pp. 15-35. Neicolas Zernvo, The Russians and Their Curch, pp. 18-114 በዚህ መጽሐፍ የሩሲያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እሚልቶ የያዘ ስለ ሆነ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረታዊ ዕውቀት ለማወቅ የሚፈልግ ሰው እንዲያነበው ነው ለመረጃነት የቀረበው።
[446] Ibid

1238-1480 ዓ.ም ነው። [447] ይህ ዘመን በሩሲያ የክርስትና ዘመን ውስጥ የሞንጎላውያን ነገሥታት ጭቆና ዘመን የተባለውና የአዲሲቷ የራሻ ዋና ከተማ የሞስኮ እድገት የታየበት ዘመን ነበር።

<u>ሦስተኛው፤</u>[448] የታሪክ ክፍለ ጊዜ የራሽያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ ራሷን የቻለችበት ዘመን ስለ ሆነ፣ የነጻነት ዘመን ይባላል[449]

<u>አራተኛው፤</u> የታሪክ ክፍለ ጊዜ፣ የራሽያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሲቪል አስተዳደር ጋር የገጠመችበት ዘመን ይባላል።[450]

<u>አምስተኛው፤</u> የፓትርያርኩን ሥልጣን ማደላደልና፥ ቀጣዩ የኮሚኒስት ክፍለ ጊዜ የተባለው ነው፤[451] በዚህ ጊዜ ውስጥ የራሽያ ቤተ ክርስቲያን መልካምም፣ ክፉም አጋጣሚዎች ገጥመዋታል።[452]

ዋናውና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የምትመሳሰልበት ግን በኮሚኒስቱ ዘመን የገጠማት ችግር ነው። የመጀመሪያው ችግር እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ የመንግሥት ቤተ ክርስቲያን እንደ መሆኗ መጠን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሲያከትም ጥቅሟና ክብሯ አብሮ አከተመ። ከዚያም[453] የአምላክ የለሹ ኮሚኒስት

[447] Ibid,81

[448] Ibid, p. 82
[449] Ibid, p. 83
[450] Ibid
[451] Ibid
[452] Ibid
[453] Ibid

መርሕ ያለ የሌለ ኃይሉን ጣለባት። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከሚያገለግሉት ጳጳሳት መካከል ግማሾቹ የኮሚኒስቱን መርሕ ደጋፊዎች ሁነው በመገኘታቸው ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሦስት ተከፈለች።[454]

<u>አንደኛዋ</u> የአምላክ የለሹን የኮሚንስቱን መንግሥት የምትደግፍ የኮምኒስት ደጋፊ ቤተ ክርስቲያን ሆነች።

<u>ሁለተኛዋ</u> ደግሞ እውነተኛዋ የራሻ ኦርቶዶክስ በመባል የግበበ ምድር (ካታኮፕ) ቤተ ክርስቲያን በመሆን ራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን ሆነች።

<u>ሦስተኛዋ</u> ደግሞ ዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን በማለት ራሷን ሰይማ የምትንቀሳቀስ ቤተ ክርስቲያን ሆነች።[455]

ይህ ሁኔታ ከራሻ ውጭ ያሉት ሀገረ ስብከቶችን በሙሉ እንዲሁ ከሦስት ከፈላቸው፤ እንደ ሀገር ውስጡ ሁሉ አንደኛው የመንግሥትን መጠነኛ ፈቃድ አግኝቶ በአገር ውስጥ በሞስኮ ፓትርያርክ ሥር የሚንቀሳቀስ ሲሆን፤[456] ሌላኛው ደግሞ በውጭ አገሩ ሥር በመሆን፣ የጥንቱ ራሽያ የሚባለውን ስም የያዘ ሆነ።
ሦስተኛ ምድብ የጥንት ራሽያ በመሆን የውጭዎቹም በተመሳሳይ መንገድ ተከፈሉ። በዚህ ሂደት አንደኛው ሌላውን በማውገዝ፤

[454] Ibid. p. 291
[455] Eastern Christianity and Politics in the Twentieth Cenry, Edited by Pedro Ramet, pp. 61-135; ይህ ክፍል ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪካዊ ሂደት ባጭሩ የሚያሳይ ጥናታዊ ጽሑፎችን የሰበሰበ መጽሐፍ ነው። በዚሁ መጽሐፍ በኮሚኒስት ሥር ያሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ባጭር ባጭሩ ተገልጿል።
[456] Ibid

ለረዥም ጊዜ ከቆዩ በኋላ እንደ ነበረው ወደ አንድነት ለመመለስ ብዙ ዋጋ፥ ጊዜ፥ ጉልበት ፈጅተዋል። አሁን ግን ውግዘቱ ተፈትቶ ተስማምተው በተለያየ አስተዳደር በሁሉም ያለች፣ አንዲት ሐዋር ያዊት ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቀኖናዊ መርሕ ተከትለው ቀጥለ ዋል።[457] ለአንድነቱ መምጣት የረዷቸው ሦስት ምክንያቶች አሏ ቸው፤ እነ ዚህ ምክንያቶችም ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው።

1ኛ/ የችግሩ መነሻ የሚሆነውን ዐቢይ ጉዳይ በመመርመር እውነት በሆነው ጉዳይ ላይ መስማማት፤

2ኛ/ የችግሩን ምንጭ መረዳትና የችግሩ ፈጣሪና ተጠያቂ ማን እን ደሆነ ዐውቆ፣ አጥፊውን በተጠያቂነት ማቅረብና ማሳመን፤[458]

3ኛ/ በችግሩ ውስጥ ያሉትን የችግር መነሻ ናቸው የተባሉትን ቅደም ተከተል አውጥቶ ቀላልና ከባድ የሆኑትን ለብቻ በመለየት፤ በችግሩ ውስጥ ሁለቱን ተደራዳሪዎች አንድ የሚያደርጓቸውን ችግሮች ማውጣትና ለመፍትሔአቸውም እንደ ቀኖና ቤተ ክርስ ቲያን አካሄድ በዚያ በከብደቱ መጠን ተራቸውን ጠብቆ ጥናት ማድረግ ነው።[459]

የችግራቸው መነሻ የነበረው የኮሚኒስት መንግሥት መሆኑ በሁ

[457] John H. Erockson, The Challenge of Our Past.pp. 91-11, Alexander Bogolepv, Toward an Amrican Orthodox Chrch, The Eestablishment of an Autocephalous Orthodox Church. pp. 7-21.

[458] Erockson, The Challenge of Our Past p. 97.
[459] John Meyendorff, Vision of Unity, pp. 74-75.

ሉም ስምምነት ተደረሰ። በመሆኑም የኮምኒስቱ መንግሥት መው ደቅ ለአንድነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።[460]

ለእኛ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ጠንቅ የሆነው የችግሩ እንብርት ደግሞ አሁን ያለው የወያኔ መንግሥት ፖለቲካ ነው።[461] ስለ ሆነም የችግሩ ዓይነት መታየት ያለበት በዚህ መንግሥት የፖለቲካ አካሄድ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ማስጠበቅ ይቻላል ወይ? የሚ ለው ጥያቄ ነው መመለስ የሚኖርበት።

ለራሻዎቹ አንድነት ትልቅ ጠቀሚታ የነበረው ተጨማሪ ኃይል ግን የአሚሪካዋ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ ነበር።[462] የአሜሪካዋ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መጠንከር ራሷን የቻ ለች ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን እድል ከመስጠቱም በላይ፣ በዓ ለም ላሉት ኦርቶዶክሳውያን የትምህርት ማዕከል መሆኗ የስደተኞ ቹን ኃይል ብርታት ሰጥቶታል።*[463]

የመጨረሻውና ዋናው ነገር ግን የኢኪዮሚኒካል ዓለም አቀፋዊ የሆነው የሁሉም ኦርቶዶክስ የአንድነት ፓትርያርክ መኖርም ለተከ ፋፈሉት አንድነት ጠቀሜታ ነበረው፤ አሁን ባለንበት ዘመንና አገር የምሥራቁ ኦርቶዶክስ በሁሉም ያለች አንዲት ኦርቶዶክሳ ዊት ቤተ ክርስቲያን በማለት በዓለሙ ፓትርያርክ ሥር የሆነች

[460] Erockson, Orthodox Christians in America, pp. 85-108
[461] የማይገለጥ የተከደነ የለም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሕገ ወጡ የወያኔ ሲኖዶስ የተሰጠ መልስ በሚል ርእስ የተዘጋጀ መጽሐፍ በመጀመሪያው ከፍል ከገጽ 10-30 በዚህ ዙሪያ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ተጽፎበታል።
[462] *Erockson, Orthodox Christians in America, pp. 94-108*

[463] *ለምሳሌ የቅዱስ ቭላዲመርን የድጎረ ምረቃ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት፥ የቅዱስ ቲካን የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት መጥቀስ ይቻላል።*

ቤተ ክርስቲያን ናት።[464] ሁሉም ራሱን የቻለ ሁኖ ግን የእስታንቡሉን ፓትርያርክ የበላይ አባትነት በመቀበል ሐዋርያዊ ትውፊትንና ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ አምልኮን መሠረት ያደረገ አንድነት ነው ያላቸው።[465] ይህም፣ አንዱ የእድገት ምልክት ነው።

<u>የካቶሊክ</u> ቤተ ክርስቲያን ሁለት ትልልቅ የሆኑ ችግሮች ነበሩባት። <u>አንደኛው</u> የፈረንሳይ ነገሥታት ገሚስ አውሮፓን ይገዙ በነበረበት ወቅት ንጉሡ ከፖፑ ጋር ባለመግባባቱ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ከአንገላታው በኋላ፣ አስገድዶ አቪገኖን ወደ ተባለች የፈረንሳይ አጎራባች የደንበር ከተማ ወሰደው።[466] ከዚያ ለቀጣዮቹ ስድሳ ስምንት ዓመታት በተከታታይ ፈረንሳይ ተወላጆቹን እያሾመ ከሮማው የበለጠ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ገንብተው ኑረዋል።[467] በኋላ በአንዲት መናኝ ቅድስት አማካይነት ወደ ሮም እንደ ተመለሰ ታሪ ካቸው ያስረዳል።[468]

<u>ሁለተኛው</u> ከ1309-1387 ዓ. ም.እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በዚሁ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ካቶሊክ ሌላ ችግር ገጠማት፤ 1387 የተመረጠው ፖፕ ለውጥ ለማምጣት ሲያቅድና ሲያውጅ የፈረንሳይ ተወላጆች ጳጳሳት ለውጡ ስላስደነገጣቸው ፖፑን

[464] *Olvier Clement ,Conversation with Ecumenical Patriarch Bartholomew L., From the French by Paul Meyendorff, pp. 21-54.*
[465] *Ibid*
[466] *Steven Ozment The Age of Refotm, 1250-1550 An Intellectual and Religious History of Late Medeivla and Reformation Europe, p. 157.*

[467] *Hans Kung, Christianity Essence, History, and Future, pp. 461.*
[468] *Ibid, Steven Ozment, p. 175.*

ሳያወርዱም፣ ሳያወግዙም፣ ከአሥራ ሁለት በላይ የሚሆኑ ጳጳሳት ሌላ ፖፕ ይመርጣሉ።[469] ይህ አስቀድሞ የተመረጠው ፖፕ ዩርባን ስድስተኛ ሲሆን፤ ይህ እንዳለ ፈረንሳዮቹ ቀለሚንጦስ የተባለ ጳጳስ መርጠው፤ ቀለሚንጦስ ሰባተኛ ብለው ሾሙ።[470] እነዚህ ሁለት ፖፖች እያንዳንዳቸው እውነተኛው እኔ ነኝ በማለት ተወጋገዙ። ይህ ጊዜ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ክፍፍል በመባል ይታወቃል።[471]

ይህ ብዙም ሳይቆይ የቆንስጣንጢን የሰላም ጉባኤ በማለት የሁለቱን ጳጳሳት ችግር ሊፈታ ያሰበ አንድ የሰላም ጉባኤ ተቋቋመ። ይህ ጉባኤም ብዙ ሳይቆይ ሁለቱን ተፎካካሪ ፖፖች ትቶ ሌላ ሦስተኛ ፖፕ መረጠና አለከሳንደር አምስተኛ ብሎ በመሾም የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን የሦስት ፖፖች ባለቤት አደረጋት።[472]

ይህም ሁሉ ሁኖ አብዛኛዎቹ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ይህ ጊዜም እንኳ ቢሆን ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስለ ሆነች ካቶሊክ ሶስት ፖፖች አልነበሩዋትም፤ አንድ እውነተኛ ፖፕ፣ ሁለት የሐሰት ፖፖች፣ ነበሯት እንጂ፤ ብለው ይተርካሉ።[473] አሁንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተወሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተከሠተው ችግር፣ የዚህ ዓይነት ችግር ነው።

[469] *Ibid, 464*

[470] *Ibid,465*
[471] *Steven Ozment, p. 155.*
[472] *Hans Kung, p. 467. Steven Ozmen, p. 159*

[473] *Ibid, 468፣ ibid, p. 160*

ሁልጊዜም፣ እውነተኛው በሕጋዊ መንገድ ተመርጦ የተሾመው፤ የመጀመሪያው ነው። ጉልበትንና ጊዜን መከታ አድረገው በፖለቲካ ድጋፍ የተቀመጡት እውነት በመጣ ጊዜ ከእውነት ጋር መጋፈጥ አይቀርም፤ የካቶሊኮቹ ችግር በመጨረሻ የተቃለለው ሁለቱ የሐሰት ፖፖች በግዴታ ውዴታ፣ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ሲለቅቁ፣ በሕጋዊ መንገድ ተመርጦ የተሾመው እውነተኛው ፖፖ እስከ ጊዜ ሞቱ አገልግሎ አርፏል። ከዚያም በምትኩ እየተመረጠ እስከ አሁን የቀጠለ ሥርዓት አላቸው።: ይህንንም መምረጥ አንደኛውና ዋነኛው ቀኖናዊ መንገድ ነው።

የኦርቶዶክሶቹ ግን ከዚህ የተለየ ነው። የተከተሉት መርሕ የተመሠረቱበትን ዓለም አቀፋዊ ቀኖና መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ግማሾቹ በአስተዳደር ራሳቸውን እንደቻሉ ሁነው በአስተዳደራዊ አንድነት ሳይሆን ቀኖናው በሚያዘው መሠረት ሐዋርያዊ ቀጣይነትን ፣ የአምልኮ ሥርዓትን፣ የዓለሙን ፓትርያርክ እና እውነተኛውን እምነት በመቀበል ነበር። ስለ ሆነም፣ በያሉበት ሁነው አንዲት ኦርቶዶክሳዊት የክርስቶስ አካል የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት፤ የሚለውን የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መርሕ በመቀበል ችግሩን አቃልለውታል።[474]

እስከ አሁንም ችግሩ ገና ያልተቃለለላቸው ብዙዎች አሉ፤ በኦርቶ ዶክሱ ዓለም በአሁኑም ጊዜ ይህን የሚከታተል ኮሚቴ አለ፤ [475]

[474] *Erickson, The Challenge of Our Past, p. 110. Orthodox Christian in Ammerica, p. 89.*
[475] *የአንድነት ወይብ ሳይት*

ኮሚቴው ልዩነቱ ሲፈጠር ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዳይጣስ ከፍ ተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል።፤ ጥንቃቄው እነሱ የተቀበሏቸው ጉባኤ ያት በቀኖናዎች መሠረት መሄዳቸውን ማረጋገጥ ነው።[476] የእኛ ጉዳይም መታየት ያለበት ከዚህ አንጻር ነው።

<u>የአርመን</u> ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ አሁንም ችግራቸው እንዳለ ቢሆንም አሁን ያሉት ሦስት ፓትርያርኮች አንዱ በአንዱ ዕውቅና አግኝቷል፤[477] ሦስቱም ራሳቸውን የቻሉ ፓትርያርኮች ይሁኑ እን ጂ፣ በእምነት አንድ ስለ ሆኑ ሳይወጋገዙ እያንዳንዱ ፓትርያርክ የተቀበለው ሕዝብ አባት ሁኖ፣ በሌላኛው ፓትርያርክ ዕውቅና በማግኘት ሥራቸውን እየሠሩ ነው።[478] ይህ ማለት በአሁኑ ጊዜ በአርማንያ አንዲት በሦስት ፓትርያርኮች የምትተዳደር፣ የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አለች ማለት ነው።

እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፣ ችግራቸውን በማቃለል ላይ ናቸው። ይህ ሁኔታ ግን እንዲሁ የተገኘ አይደለም። ብዙ ትዕግ ሥትን፣ አርቆ ማየትን፣ የእኔነትንና ጥቅምን የመሳሰሉትን ዋጋ ዎች ያስከፍላል።

<u>የአንጾኪያ</u> ቤተ ክርስቲያን በችግር ምክንያት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤቷን ወደ ችጋጎ አዛውራ ሥራዋን እየሠራች ትገኛለች።[479]

[476] *ዝኒ ከማሁ*
[477] *Armenian Apostolic Church, Armenian Church, Holy Synode of Cilicia, The Armenian Apostolic Orthodox Church*
[478] *Arch Bishop Trian Nersoyan, Armenian Church Historical Studies, Matters of Doctrine and Admininstration, p. 177.*
[479]

እነዚህን ሁሉ ችግሮች ስንመለከት የእኛ ችግር የትኛውን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማፈላለግ ወደፊት ለምናደርገው ውይይት መጠነኛ እገዛ እናገኛለን፤ ችግሩ አንድ ዓይነት ላይሆን ይችል ይሆናል። መፍትሄውን ለማፈላለግ ግን ያስተምረናል። ችግሩም የእኛ ብቻ አለመሆኑን ካወቅን መፍትሄውን ለማግኘት አንቸገርም።

ይህም ትዕግሥትን፥ ቅንነትን፥ እውነተኝነትን፥ የሚጠይቅ ሥራ ነው። ከዚህ ውጭ እሠራለሁ ማለት፣ ሕዝብን ከማሳዘን፣ ራስንም ከማታለል ያለፈ ፋይዳ የለውም። በዚህም ምክንያት ወይ ከፖለቲካው ፖለቲከኞች አልሆን፣ ወይ ከሃይማኖቱ ሃይማኖተኞች አልሆን፣ ከሁሉም ሳንሆን እንዳው በከንቱ መድከም ብቻ ይሆናል። ይህን ከላይ ለምሳሌ ያህል የገለጥነውን መሠረት አድርገን መሆን ያለበትን ቁም ነገር በይበልጥ ለመገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦች እንመልከት።

2. የኢ.ኦ.ተ.ቤ ችግርና መፍትሄ ሰጭ ውይይት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ችግር በጥቅሉ ስንመለከታቸው፤ ከጠቅላላው ትውፊታዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንና ከቤተ ክርስቲያኒቷ ታሪክና ሥርዓት ጋር መጋጨት መሆኑን ከላይ ቀደም ሲል የዘረዘረናቸው ታሪካዊ ሂደቶች በጥልቀት አስረድተውናል።[480] ከዚህ ተነሥተን ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ችግሮች ስናጠና፣ የምንጀምረው ከአመሠራረቷ ነው።

2.1 የኢ.ኦ.ተ.ቤ ቀኖና መሠረት የችግሩ ምንጭ፤

ከላይ በቦታው እንደ ተገለጠው ክርስትና በኢትዮጵያ በነገሥታት አነሣሽነት ስለ ተጀመረ፣ በነገሥታቱም ተይዞ ስለ ኖረ፣ እንደ አገር አንድነት አስተባቂም፤ ሁኖ ኑሯል።[481]

ቤተ ክርስቲያን ራሷን ስትችል ንጉሠ ነገሥቱ የተጫወቱትን ሚናና የግብጽን ቤተ ክርስቲያን አጸፋ ስንመለከት፤ የነቅዱስ ሐርቤን፣ የነአጼ ቴዎድሮስን ታሪክ ስንመለከት፣ የቤተ ክርስቲ ያኒቱ የበላይ ጠባቂዎችና መሪዎች፣ ነገሥታቱ መሆናቸውን በእርግጠኝነት ማወቅ ይቻላል። [482] ይህ ከሆነ ደግሞ በሀገር የሚመጣ ማንኛውም ፖለቲካዊና ሕዝባዊ ጥቅምም ሆነ ጉዳት ቤተ ክርቲያኒቱን በቀጥታ ይመለከታታል።[483]

በዚህም ምክንያት በአገር ችግር ሲመጣ ችግሩ የሚመለከተው አገርን ብቻ አይደለም። በችግሩ በመካፈልም ሆነ ችግሩን በማቃ

---

[480] የኃይለ ሥላሴን፥ የጣሊያንን ወረራ፥ የጳጳሳትን ሹመት፥ ኃይለ ሥላሴ በተሾሙት ላይ የወሰዱትን አርምጃ፥ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ሞት፥ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ሲደት፥ አሁንም በገለልተኝነት ያለውን እንቅስቃሴ መመልከቱ በቂ ነው።

[481] አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መቅድሙን ይመልከቱ

[482] ዝኒ ከማሁ ገጽ 20።

[483] ዝኒ ከማሁ ይልማ ዴሬሳ የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ሰድስተኛው ክፍለ ዘመን የሚል መጽሐፍ የዚህን ዘመን የክርስቲያን አልቂት የተረከ መጽሐፍ ነው። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ትግላችን የኢትዮጵያ ለብዮታዊ ትግል ታሪክ ገጽ 21-25

ለል ደረጃ ቤተ ክርስቲያቱ ትልቅ ሚና ነበራት።[484] በዚህም መሠ ረት የክርስትናውን ሃይማኖት ለማስጠበቅ ይደረግ የነበረው ጥን ቃቄ አገርን ለማስጠበቅም እንደሚደረገውና ለአገር አንድነት የሚ ጠይቀው የጥበቃ ሥራ ጋር አንድና ተመሳሳይ ነበር።[485] የአጼ ምንይልክን የጦር አዋጅና የካህናቱ ታቦት ይዘው መዝመት ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለ አገር የነበራትን ሚና የሚሳይ ነው።[486]

ይህ የመንግሥት ከለላና ጥበቃ ሲቀር፣ ሌሎቹ መንግሥት ይደግፋቸው በነበሩ የአርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሆነው ሁሉ፣ ሃይማኖቱን የሚመሩት ነገሥታት ችግር ሲገጥማ ቸው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ችግር በተመሳሳይ መጠንና መልክ ተከሥቶአል።[487] ቤተ ክርስቲያኒቱ አገራዊ አንደ መሆኗ መጠን የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር የሚከሠተው፣ በአገር ላይ ችግር በተፈጠረ ጊዜ ነው።

በመሆኑም የቤተ ክርስቲያናችን የቀኖና ጥሰት ችግር የተጀመረው በአገሪቱ የኢጣልያ ወረራ በተካሄደበት ወቅት ነበር። [488] ይህም ማለት የአገር ወረራ የቤተ ክርስቲያን ወራራ ጭምር ነበር ማለት ነው። [489] በነበሩት ግብፃዊ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስና በኢጣልያ

[484] ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ ቢጋሻው ገጽ 83-84
[485] ዝኒ ከማሁ

[486] ዝኒ ከማሁ
[487] ዝኒ ከማሁ ሉሌ ማላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 136-137
ለባ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 67-79
[488] ዝኒ ከመሁ በሁሉም መጻሕፍት ይህ ታሪክ ይገኛል ቡተለይ ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ ቢጋሻው በግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 45 ያለውን ይመልከቱ።
[489] ዝኒ ከማሁ

ፖለቲከኞች መካከል የተፈጠረው ችግር፣ ሊቀ ጳጳሱን እንዲሰ ደዱ ማድረጉ ይህን የሚያረጋግጥ ነበር። [490] የዚያ ውጤትም ቤተ ክርስቲያኒቱ በሕገ ወጥ መንገድ ጳጳሳትን እንድትሾም አደረገ። በሕገ ወጥ መንገድ መሾሚን ተከትሎ የመጣው ችግርም አሁን ላለንበት ችግር መጠነ ሰፊ አስተወጽአ አድርጓል።[491]

ይህ የታሪክ ክሥተት የተፈጸመው ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ውጭ ሀገር በስደት ላይ ሳሉ ነበር።[492] ያን የቀኖና ጥሰት ተከትሎ፣ በንጉሠ ነገሥቱ የተወሰደው እርምጃም ቤተ ክርስቲያንን ትዝብት ላይ የጣለ ውሳኔ ነበር። በዚህ ቦታ ላይ በሠፊው መግለጥ አዳጋች ቢሆንም በመጠኑ ግን ማብራራት ወሳ ኝነት አለው።

ከኢጣልያ ወረራ በፊት በግብፃውያን ሥር የነበረ፥ አምስት ኤጲስ ቆጳሳት አባላት የነበሩበት አንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ የሚመሩት ሲኖዶስ ነበር።[493] ኢጣልያ አገሪቱን ስትወርና ነጉሠ ነገሥቱ ሲሰደዱ ግን፣ ሊቀ ጳጳሱም ዘግይተው ይሁን እንጂ እሳቸውም ተሰደዱ። በዚህ ጊዜ ሁለቱ ሰማዕታት፥ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና፥ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በግፍ ተገደሉ። የግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ መሰደድ ግን ሁለት ግልጽ ምክንያቶች ነበሩ።

<u>አንደኛው</u> ምክንያት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ወደ ኢትዮጵያ መድቦ የሚልከው ጳጳስ፥ ቃለ መሐላውን የሚፈጽ

[490] ዝኒ ከማሁ
[491] ዝኒ ከማሁ
[492] ጎንደሬ ቢጋሻው ገጽ 93-100 በዚህ መጽሐፍ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የተያያዘ ባለ ሠላሳ ስድት አንቀጽ የቤተ ክርስቲያን ደንብ ወጥቶ በሥራ ላይ ውሎ ነበር።
[493] ሉሌ መላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

መው ለንጉሠ ነገሥቱና ለመንግሥታቸው ታማኝና ጠባቂ እንዲ ሆን ስለ ነበር፣ ንጉሡ ሲሰደዱ የጳጳሱ ብቻቸውን መቀመጥ አስፈላጊም፥ ሕጋዊም አልነበረም።[494] ምክንያቱም አንዱ የንጉሥ ነት ሥልጣን ይገባኛል ባይ ተነሥቶ፥ ጳጳሱን አስገድዶ ንጉሥ ሊሆን ስለሚችል ነው፤ ይህም ከሆነ ደግሞ ወደፊት በንሡና በግብፅ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት እንዳያሻክር ስለሚያስፈራ ነው።

<u>ሁለተኛው</u> ምክንያት ግብፅን በምትገዛው በእንግሊዝና ኢትዮጵ ያን በወረረቺው በኢጣሊያ መካከል ያለው የፖለቲካ አለመግባ ባት ያመጣው ተጽዕኖ ነው፤ በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያችን ለገጠማት ችግር መሠረት የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አምጥቷል።[495] ኢትዮጵያውያን የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎችም የችግሩን መነሻ አንጥረው ማውጣት አልቻሉም። እንደ ዋና አንኳር አድ ርገው የሚገልጹት የጳጳሱን መሾሽ ብቻ እንጂ፣ የችግሩ ምንጭ የሆነውን በእንግሊዝና በኢጣሊያ መካከል የነበረውን የፖለቲካ ልዩነት፣ ተጠያቂ አድርገው አላዩትም።[496]

ዋናው ችግር የኢጣልያው ወራሪ ኃይል የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የመደበቻቸውን ሊቀ ጳጳስ፣ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ እናት ቤተ ክርስቲያን ለይተው ራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን ያድ ርጉና፣ እርሰዎ ፓትርያርክ ይሁኑ እንጂ ከግብጽ ጋር ያስተዳደር ጎብረት የማይቻል ነው፤ የሚለው የኢጣሊያ የፖለቲካ መርሕ

[494] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት፣
[495] ሉሌ መላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 137
[496] ሉሌ መላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 170.

ነበር ሊቀ ጳጳሱን ወደ ሮማ ለይግባኝ እንዲጓዙ ያደረጋቸው። ገሪማ ታፈረ የወቅቱን ሁኔታ ሲገልጹ፤

"ሊቀ ጳጳሱን አባ ቄርሎሰን የሐበሻ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ የሚያ ስተሳስራቸውን ማሠሪያ ለመፍታትና አርነት ለማውጣት የእሽታ ፈቃዳቸውን ቢጠይቅ፣ እንቢ ቢሉትና ብውዕ ፓትርያርኩንም ሳልከድም ከአርሳቸውም የመንፈሳዊ ልቅና ሳልወጣም ብለው በመመለሳቸው ነው"፤[497]

ብለዋል ይህም የጳጳሱን ከህደት ሳይሆን ጥንካሬ የሚያሳይ ነው።

ይህ አቤቱታ ሳይሳካ፣ ሁለቱን የበላዮች ማለትም የቤተ ክርስቲያ ኒቱ የበላይ የሆኑትን ንጉሠ ነገሥቱንና የከህነት የበላይ የሆኑትን የግብፁን ፓትርያርክ ከዶ የፓትርያርክነት ሥልጣን ተቀብሎ ኢት ዮጵያ ከመቀመጥ ይልቅ፣ ወደ ላከቻቸው እናት ቤተ ክርስቲያን ወደ ግብጽ መሄዱ ነው የተሻለ አማራጭ የሆነው።[498] ከህደት ነው ከተባለም አገራቸውንና ጦራቸውን ጥለው ወደ እንግሊዝ ከተሰደዱት ንጉሥ የበለጠ ከህደት ነው ሊያሰኝ አይችልም።[499] ሁኖም ግን ይህ የታሪክ ክሥተት በሕገ ወጥ መንገድ ሥልጣን ለያዙና እነሱን ለሚደግፉ ወገኖች እንደ መረጃ አድርገው ስለሚ ጠ ቀሙበት በመጥፎ ጎኑ ተጽእኖ አድርጓል።

ይህን ሐሳብ እንደ ትልቅ ነጻነት አድርገው ካሞገሱት ኢትዮጵያ ውያን አንዱ መምህር ገብር ዮሐንስ ገብረ ማያም "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ሁለት" በተሰኘች ትንሽ መጽሐፍ

[497] ገሪማ ታፈረ ጎነደሬ በጋሻው ገጽ 89
[498] ሉሌ መላኩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 173።

[499] ሉሌ መላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 136።

ላይ ሐሳባቸውን ገልጠዋል። መምህር ገብረ ዮሐንስ የግብጽን ክፋት አብራርተዋል። ከዚያም በኢጣልያ ቀስቃሽነት የተሾሙትን አወድሰዋል። ስለ ሕገ ወጥ ተሿሚዎች መሻርም እንዲህ ያስነብቡ ናል። *"የአሥራ ሁለት ጳጳሳት መኖር የተሟላ ሲኖዶስ እንዲኖር ያደርጋል፣ ታሪክ መሥመሩን ሰቶ ከተመዘገበ ውድቅ የሚሆንበት ጊዜ መኖሩ አይቀርም። የአፄ ኃይለ ሥላሴ ከሰደት መመለስ ተጠ ናክሮ የነበረውን የኢትዮጵያ ሲኖዶስ እንዲፈርስ አደረገ"።*[500]

የመምህር ገብረ ዮሐንስ አባባል እርስበርሱ ይጋጫል። በአንድ በኩል የተዛባ ታሪክ እውነት ሲመጣ ከእውነት ጋር መቆም አይች ልም ይልና በሌላ በኩል የተጠናከረው የኢትዮጵያ ሲኖዶስ ይላ ል፤ ለዚህ ነው ኢትዮጵያውያን ቀኖናን ከተንኮልና ከበደል ጋር ማዛመድ የለባቸውም የምንለው። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተንኮል መታየት ያለበት በታሪክ ነው። ያም ታሪክ ራሱን ችሎ ስሕተት ይባላል፤ ግን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መታየት ያለበት፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያከበረችውን ሕግ ነው።

መምህር ሉሌ መላኩም በመጽሐፋቸው ላይ በሰጡት አስተያየት ከዚሁ አድር ባይነት አላመለጡም። የእኛ ጸሐፍያን የግብጽን ቤተ ክርስቲያን ድክመትና የረቀቀ ተንኮል፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለመጣስ መግቢያ መንገድ አድርገው ተመልከተውታል።[501] በመ ሆኑም ሁኔታውን ለማስጨበጥ መጠነኛ ግንዘቤ እንዲኖረን ከዚህ ላይ መጠነኛ ማብራሪያ ማቅረብ ያስፈልጋል።

[500] ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም የኢዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 82.
[501] ሉሌ መላኩ የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 172

2.2. የሊቃ ጳጳሱ ስደት ያስከተለው ቀኖናዊ ተውሰ፤

ሊቀ ጳጳሱ ወደ ሮማ ለይግባኝ ሲሔዱ አቡነ አብርሃም የተባሉ ትን ጳጳስ ወከለው ነበር የሄዱት።[502] የወከሏቸው አቡነ አብርሃም የውክልናውን ቦታና ሥልጣን ወደ ሊቀ ጳጳስነት ከፍ አደረጉት። ገሪማ ለዚህ ሐሳብም የሚሉት አላቸው፤

"ሊቀ ጳጳሱ የሮማን ወሬ ሲጠባበቅ የሐበሻ ሊቃውንት ተሰብስ በው ወደ ግርማዊ የኢጣልያ መንግሥት እንደራሴ በአከቶበር ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም የአበሻ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲ ያን እንድትለያይና በአርነት አካሄድ እንድንኖር እንፈልጋለን፤ ስለዚህ ብፁዕ ፓትርያርኩ የቀቡዋቸው አባ አብርሃም ለሐበሻ ሊቀጳጳስ ይሁኑልን አሉ፤ ተብሎ የግርማዊ የኢጣልያ መንግሥት እንደራሴም ፈቀዱላቸው፤ የሚል ጋዜጣ ወጥቶ ተነቧል፤ ሲሉ ከአዲስ አበባና ከሮማ የተላለፉት ቴሌግራሞች በዲሴምበር ሦስት ቀን ፲፱፻፳፭ ዓም አስታወቁ"፤ [503] በማለት ያስነብቡናል።

በዚሁ መሠረት ሁኔታው በዚያም ሳያበቃ የሊቀ ጵጵስናውን መሳ ርግ የፓትርያርክነት ቦታ ሰጡት። ገሪማ ይህ ሁኔታ በግብፁ ቆን ስላ በኩል፣ ለግብፁ ፓትርያርክ እንደ ተነገራቸው፤ እርሳቸው በሁኔታው እንዳልተሰማሙ ይገልጻሉ።[504] አቡነ አብርሃም ግን ሳይፈቀድላቸው ያንኑ ሥልጣን ይዘው የተወሰኑ ጳጳሳትን ሹመው

[502] ዝኒ ከማሁ
[503] ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ በጋሻው ገጽ 89።
[504] ዝኒ ከማሁ

ማገልገል እንደ ጀመሩ ብዙም ሳይቆዩ ሞቱ።[505] በሳቸው የተተኩት አቡነ ዮሐንስ ደግሞ፣ ባስልዮስ፥ ሚካል፥ ቴዎፍሎስ፥ ጢሞቴዎስ፥ ያዕቆብ፥ ይስሐቅ፥ ጴጥሮስ፥ ሳዊሮስ፥ አብርሃም፣ የተባሉ ጳጳሳትን ሹመው ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ የመንፈሳዊ ቅኝ አገዛዝ ነጻ ወጣች በማለት አወጁ።[506]

ሁኖም ነጻ ቤተ ክርስቲያን ናት በማለት አወጁ እንጂ፣ ሆኖም አዋጁ ግን በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መወገዝን ሲያስከትል በኢትዮጵያውያን አርበኞችም ጥሩ ስሜትን አልፈጠረም*[507]። ከዚህ የተነሣ አባ ዘካርያስ የተባሉ ጳጳስ ለኢየሩሳሌም ተሹመው በስደተኛው ተቀባይነት በማጣታቸው ብዙ ሲጉላሉ ቆይተው ወደ አገራቸው አንደ ተመለሱ መምህር ገብረ ዮሐንስ ገልጸዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት ተመለሱ፤ በዚህ ወቅት፣ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ጳጳሳት ተሸረው ወደ ገዳም አስተዳዳሪነት ዝቅ ብለው ሲመደቡ፣ አንዱ ብቻ ለፖለቲካ ሲባል ሹመታቸው አንዳለ ጸድቆላቸው ነበር።[508] ሌሎቹ ግን በኋላ እንደ ገና ጵጵስና ለሁለተኛ ጊዜ እንደ ተሾሙ ይነገራል። ይህ ሁሉ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር ሲታይ ስህተት ነበር። በየትኛውም ትውፊታዊ ቀኖና ተደጋፊነት የለውም፤ የሚደረገው ለፖለቲካ ጥቅም

[505] ዝኒ ከማሁ ገጽ 92።
[506] ዝኒ ከማሁ
[507] *በገሪማ ታፈረ የተጻፈው ጎንደሬ ቢጋሻው የሚለው መጽሐፍ ላይ፣ የሊቀ ጵጵስና ሹመት የተሾሙት ሁለተኛው አቡነ ዮሐንስ ሲሾሙ፣ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብም ተዘጋጅቶ አብሮ የወጣ መሆኑን የሚገልጸው በዚሁ ጊዜ ነው፤ ሕጉ በአዋጅ ከወጣ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ በፌርማ አረጋግጠው ለጳጳሳቱና ለካህናቱ የማጽደቂያ ደብዳቤ ጽፈዋል፣ ገጽ 102. ::
[508] ሉሌ መላኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 138.

ሲባል ስለ ሆነ፣ በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየው ይህ ዓይነቱ ችግር አሁንም ያን ጊዜም ፖለቲከኞች ለሥልጣናቸው ሲሉ የሚያደርጉት ስህተት መሆኑን መረዳት ይቻላል።[509]በኢጣልያ ግፊት የተሾሙትን ጳጳሳት ልዩነት ፈጥሮ አንዱን ሸሮ ሌላውን መተው፤ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ከዜግነት አንጻር ሲታይ ሊወገዝ የሚገባው ተግባር ነበር።[510]

ሌላው ሕገ ወጥነት ደግሞ፣ የተሻሩትን ጳጳሳት በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ የጵጵስና ሥልጣን መሰጠቱ ነው። ይህም ከምሥጢረ ክህነትና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር ሲታይ የከፋ ሕገ ወጥ እርምጃ ነበር።[511]
ይህ ስህተት ከተፈጸመ በኋላ ነጻነት ሲመለስ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ ሁሉ፣ ከክህነት ሹመት ቦታቸው ተሰደው ወደ አገራቸው ሂደው የነበሩት ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ፣ ወደ መንበራቸው ተመልሰው እስኪሞቱ ድረስ ካገለገሉ በኋላ በመንፈሳዊ ጉባኤ ቀስቃሽነትና በንጉሠ ነገሥቱ ጥረት ቀኖና ጥሰቱ ተስተካክሎ ቤተ ክርስቲያኒቱ ራሷን የቻለች ነጻ ቤተ ክርስቲያን ሆነች።*[512] ሁኖም ግን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሲወድቅ ያው የፖለቲካው ተፅዕኖ በሌሎቹ አገሮች

[509] ሉሌ መላኩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 173.
[510] ገብረ ዮሐንስ ገበረ ማርያም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 84.
[511] ዝኒ ከማሁ
[512] ይህን ታሪክ፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የጻፉ ሁሉ ጸሐፊዎች አስፍረውታል። ገብረ ዮሐንስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 80-85። ሉሌ መላኩ የኢትየጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 173-174። አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጲያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 80-882።

እንደ ሆነው ሁሉ፣ በእኛም አገር ያው የተለመደው ችግር ተፈጠረና የቤተ ክርስቲያን ችግር ቀጠለ።[513]

2.3. ሁለተኛው ቀኖናዊ ቀውስ ሲከሰት

እንደ ራሽያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በእኛም ቤተ ክርስቲያን ስም ኮሚኒስቱን የደርግ ወታደራዊ መንግሥት መደገፍ ተጀመረ።[514] ይህ እርምጃ ሁለተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በእሥር ቤት እንዳሉ እንዲገደሉ አደረገ።[515] ድርጊቱ በዚህ ሳያበቃ ፓትርያርኩ በእሥር ላይ እንዳሉ ጉዳያቸው ሳይጣራ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም ተጥሶ፣ ሦስተኛ አዲስ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተሾሙ።[516] እርሳቸው ለአሥራ ሁለት ዓመት ያህል ቤተ ክርስቲያቱን መርተው በክብር ዓረፉ።
ከስድሳ ቀን በኋላ፣ ቀኖናው ተጠብቆ፤ ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ"፣ተብለው አራኛው ፓትሪያርክ ሁነው በሕጋዊ መንገድ ተመርጠው ተሾሙ።[517]

ይህ በዚህ አንዳለ ነው ወያኔ ኢሐዴግ ወደ መንግሥት ሥልጣን የመጣው። ወያኔ መንግሥት ሲይዝ፣ አሁንም በቤተ ክርስቲያን

[513] *Erickson, Orthodox Christians in America, A short , History , pp. 5-9*

[514] *Eastern Christianity and Politics, Edited by Pedro Ramet,Christianity Under stress, pp. 386-398*

[515] *Ibid, p. 388*

[516] የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የበዓለ ሢመት መጽሔት ልዩ እትም ለንደኛ ዓመት የመጅመሪያ ርእሰ አንቀጽ ላይ ይመልከቱ።

[517] ተመሳሳይ መጽሔት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በዓለ ሢመት አንደኛ ዓመት መጽሔት.

ላይ እጁን በመጫን የተለመደውን ሕገ ወጥ ሥራ ሠራ። አቶ ታምራት ላይኔ የቀድሞውን ፓትርያርክ አቡነ መርቆሬዎስን ከሥልጣን እንዲወርዱ ያደረኩት በእኔ ፊርማ ነው፣ ብለው እንደ ገለጡት።[518] በመንግሥት ትእዛዝ የደርግን የፖለቲካ ዶክትሪን ተከትሎ፣ "ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ አይሾም" የሚለውን ዓለም አቀፉን ቀኖና አፍርሶ፣ በሕገ ወጥ መንገድ ሕገ ወጥ ፓትርያርክ ሾመ።[519] የአፈጻጸሙ ሂደት ከላይ እንደ ተባለው በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር በአቶ ታምራት ላይኔ መረጋገጡ የቅርብ ጊዜም ትዝታ ስለ ሆነ ሌላ ማስረጃ መመልከት አስፈላጊ አይደለም።[520]

እነዚህን ሁሉ ሂደቶች ስንመለከታቸው፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ጥሰት መነሻውም መድረሻውም ፖለቲካ መሆኑን እንረዳለን። ከታሪካችን እንደምንገነዘበው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ከአገር ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ አገሪቱን የሚመለከት ጉዳይ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ስለሚመለከት፣ የችግሯ ዋና ምክንያትም በሀገሪቱ የሚከሠተው የፖለቲካ ተጽዕኖ ነው። በአገሪቱ የፖለቲካ ነጻነት ካለ ቤተ ክርስቲያኒቱ አምልኮዋንና ሥርዓቷን፣ ቀኖናው በሚያዘው መሠረት፣ ያለምንም ችግር ታካሂዳ

[518] ከዊከሊክስ ድኅረ ገጽ የተገኘው መረጃ

[519] አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ሕግን ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን? ገጽ 91
የማይገለጥ የተከደነ የለም ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሕገ ወጡ የወያኔ ሲኖዶስ የተሰጠ መልስ ገጽ 71-72.

[520] የአቶ ታምራት ላይኔን መልስ ለነድ በመጽሐፉ መጨረሻ በሚቀመጠው መረጃ ይመልከቱ።

ለች። የፖለቲካ ነጻነት ከሌለ ግን እንደ ልብ መሥራት አስቸጋሪ እንደ ሆነ ባለፈው ታሪክም አሁንም በተግባር እያየነው ነው።[521]

እንግዲህ የችግሩ መነሻ የፖለቲካ ተጽዕኖ ከሆነ፤ የዚህ መጽሐፍ ዓላማም፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር ላይ የሚደረግ ውይይት የፖለቲካውም ተጽዕኖ እንዳለበት በውል ማስገንዘብ ነው። ለቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር መፍትሔ ይሆናል ተብሎ የሚደረገው ውይይትም መጀመር ያለበት በሀገሪቱ የፖለቲካና የሃይማኖት ነጻነት መኖር መርሕ ላይ ነው።[522]

ቤተ ክርስቲያንን ለስደት የዳረጋት፥ ፓትርያርክ እያለ ፓትርያርክ እንዲሾም ያደረገው የወያኔ መንግሥት ፖለቲካ ነው።[523] ፖለቲካ የወያኔ ኢሕአዴግን መንግሥት የተጠጉትንም እንኳ የወለኑትን ውሳኔ በሥራ ላይ እንዳያውሉት እያስቸገረ ነው።[524] ያለ መንግሥት ፈቃድ ውሳኔያቸውን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ነጻነት የላቸውም፤[525] ይህ ሊስተባበል የማይችል ሀቅ ነው። በአሁኑ ወቅት በሚታየው የፖለቲካ መድረክ ፥ በሕግ የታወቁ ተቃዋሚና ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶችን በነጻ ለማሳተፍ የማይሻ መንግሥት መሆኑ በገሀድ ታውቋል።[526]

[521] *የንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴን፥ የደርግን፥ የወያኔን፥ መንግሥታት ብንመለከት በቤተ ክርስቲያን መጠቃም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳይ እንመለከታለን፡፤*

[522] *የሰደቱ ምክንያት ፖለቲካውን የማይደግፍ ሰው በሀገሪቱ መኖር ስለማይችል ነው። የማይገለጥ የተከደነ የለም ገጽ 57*

[523] *ዝኒ ከማሁ*

[524] *የአባ ጳውሎስን አቧሿም የሸጠው ጦቢያ መጽሔት ነሐሴ 1984 ቁጥር አምስት*

[525] *በሥራ ላይ ያልዋለው የአባ ጳውሎስ የሐውልት መፍረስ ውሳኔን ይመለከቷል።*

[526] *ደበበ አሸቱ የአመቴ ፈተና ከምርጫ 97- ቃልቲ አሰራትና... መጻፉ የወያኔን ከፋትና ዓይን ያወጣ የውሸት ፖለቲካ ያጋለጠ መጽሐፍ ነው። በተለይም ከገጽ 360-380 ያለው።*

ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ የመብት ጥሰት የተካሄደው በመንግሥት አስተባበሪነት ነው የሚለውን ከስ የሚያስተባብል ማንም የለም። አፈጻጸሙም ሲታይ፥ መንግሥት ከሚፈቅደው ውጭ፥ ሲኖዶሱ በራሱ ፈቃድ መሥራትም፣ መንቀሳቀስም፣ አይችልም።[527] እንግዳውስ ቀኖናውን የጣሰውም ያስጣሰውም መንግሥት ነውና፥ ይህን ችግር ለመፍታትና የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናዊ መብት ለማስከበር የመንግሥት ፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሌለበት፥ ፍጹም ነጻነት ያስፈልጋል።[528]

ሕግ ተጣሰ፥ ቀኖና ፈረሰ፥ ሰብአዊ መብት ተረገጠ፥ ብሎ መናገር፣ ፖሊቲካ ነው፣ <u>ለወንጌል አገልግሎት እንቅፋት ይሆናል</u> የሚለው አባባል፣ ፖለቲካን ከነጻነት፥ ነጻነትን ከፖለቲካ ለይቶ አለማወቅን የሚያመለክት ነው። ወይም <u>ፖለቲካ ነው</u> በማለት የሚናገር ሰው፣ ራሱ የፖለቲካ አጀንዳ አራማጅ ነው ማለት ይቻላል*[529]በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ *ቀኖናዊ ቀውሱ የፈጠረው ሦስት ዓይነት ቡድኖች የሚያንቀሳቅሱት የውስጥና የውጭ* መከፋፈል ችግር አለባት። ይህም ችግር፣ ቀደም ብለን ከተመለከትናቸው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ችግሮች ጋር ተመሳሰይ ነው።

የእኛን ልዩ የሚያደርገው ከሦስቱም ቡድኖች ውስጥ፥ የግል ባሕርያቸውን እንደ ሕግ የሚጠቀሙ ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያንን እንመ

[527] *የማይገለጥ የተከደነ የለም ከገጽ 45-59 ይመልከቱ።*

[528] *ዝኒ ከማሁ*

[529]*የብዙ ሰዎች ችግር <u>መንግሥት</u> የሚለው ስም ከተነሣ "ፖለቲካ ነው፥ ከእርሱ አትግቡ" በማለት አጠንክረው የሚሰጡት ሐሳብ፣ የወያኔን መርሕ በተዘዋዋሪ መንገድ ለማራመድ የሚጠቀሙበት የፖለቲካ ስልት ነው።

ራለን ብለው ግራ ማጋባታቸው ነው። ባሉበት የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ እንኳ ጎብረት የሌላቸው ሰዎች፣ የማያምኑበትን መንፈሳዊ ተቋም መምራት እንዴት ይችላሉ? የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ችግር ከሌሎቹ ልዩ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱት ይገኙበታል።

<u>አንደኛ</u> ፖለቲከኞች ቤተ ክርስቲያንን ለሕዝብ መሰብሰቢያ ጥቅም ይፈልጓታል።[530] በአንጻሩ ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ቀኖናዊ ሕግ እንዳትመራ፥ በአመክንዮ ላይ የተመሠረተ አጀንዳም እንዳታራምድ፣ ቀፍድዶ በመያዝ በተለያዩ መንገዶች ይቃወሟታል።[531] ለዚህም፣ ቀደም ሲል የነበረውን ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን ዘተዋሕዶና፥ የአሁኑን የሲኖዶስ ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ ብለው ራሳቸውን የሰየሙትን ግለሰቦች መመልከት በቂ ነው። አባቶች እኒህን ዐይነት ግለሰቦች ይዘው የሚያደረጉትን ተግባር በማስተዋል ለተመለከተው፣ አዲስ አበባዎቹ በወታደር ኃይል ይብለጧቸው እንጂ በሌላው ተግባራቸው ግን አይተናነሱም።[532]

ከህነታዊ አገልግሎትን ለቶፈኝነት አሳልፎ በመስጠትም የተወሰኑ ስደተኛ አባቶችንም የሚበልጣቸው አልተገኘም። አንዳንድ የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የበላይ ኃላፊዎች በየሄዱበት ቀኖናዊ ሕግን

[530] ፖለቲከኞች ሲባል ለአገር ጥቅም ሥራ የሚሠሩትንና ሕይወታቸውን ለዚህ አሳልፈው የሰጡትን እውነተኛ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ማለት አይደለም። በዚህ ፖለቲካ በሚለው ስም የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም እያካሄዱ ሲነቃባቸው የነሱን ስህተት ከወያኔ ጋር የሚዛምዱና ለስህተታቸው መጠለያ የሚያደርጉ የግል ጥቅመኛ ግለ ሰቦችን ለማለት ነው።

[531] ለፈለጉት የግል ዓላማና ጥቅም የማያስሄድ ከሆነ ቤተ ክርስቲያንን ማፍረስ፥ የምሥጢረ ከህነትን ሥራ በደብዳቤ ማገድ ምንም ቅር ሊያሰኛቸውም ። መረጃ ሰነዱን በታው ላይ ይመልከቱ።

[532] ለቤተ ክርስቲያኑ ቦርድ የተጻፈ ደብዳቤ በዋቢ ሰነዶች ቦታ ይመልከቱ።

ከሚከተሉ ይልቅ፣ የኃይል ሚዛንን ይመለከታሉ፤ ለምሳሌ በሐዲበት ቦታ፣ የካህናት ወዳጆች ካሏቸው፣ ቤተ ክርስቲያን በቃለ አዋዲው አንድትመራ ሥልጣን የካህናት ነው ይላሉ። ለዚህም በሕግ ፊት የቃለ አዋዲውን ሕጋዊነት ያስረግጣሉ።

በተዎሰኑ ቦታዎች ይህንኑ በማድረጋቸው ምክንያት፣ ለሽምግልና ከሄዱበት ቦታ ካህናቱን ይደግፉ ስለ ነበር፥ ቦርድ ጥፋተኛ ነው ብለው ቤተ ክርስቲያን እንዳይቀደስ አድርገው፤ በሌላኛው አባት ገላጋይነት ቤተ ክርስቲያኑ ከመፍረስ፣ የተረፈበት ጊዜ በታሪክ ሲወሳ ይኖራል።

በሌላኛው ቦታ ደግሞ ምእመናንን ስለሚያውቁ ሊቀ ጳጳሱን እዲያባርሩ ለምእመናን መብት ሲሰጡ ማየት ሕሊናን ያቆስላል። በተይም በአንዳንድ ቦታዎች የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የተቋቋሙ ሽማግሌዎች ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ ለዚህ ሁሉ አባባላችን እውነተኝነት ማረጋገጫ ነው። "ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያን ራስ ስለ ሆኑ ለችግሩ መፍትሔ ሊሰጡት የሚገባው እነርሱ ናቸው" ለሚለው ጥያቄ፣ ጳጳስ እንኳን የቤተ ክርስቲያን ራስ፥ እግርም መሆን አይችል፤ ከማለታ ቸውም አልፈው የቤተ ክርስቲያኒቱ ራስ ቦርድና የቦርድ ሊቀ መንበር ነው።[533] በማለት የሚመልሱት መልስ ለቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቋሚአለሁ ማለታቸውን በገሀድ መሻራቸውን ያሳያል።

[533] የአንዳንድ ችግር ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት የአዲት ኮሚቴ ያወጣው የምርመራ ውጤት ሰነድ በዋቢ ዝርዝር ላይ ይገኛል እሱን ይመልከቱ ።

በአንጻሩ ለቤተ ክርስቲያን እድገትና አንድነት አብረዋቸው ከሚ ሠሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይልቅ፥ የንግድና የግል ፖለቲካ አራማጅ ብልጣ ብልጦች ሐሳብ ይበልጥብኛል ብለው፤ ትናት ሲያወግዙት የነበረውን ዓላማ፤ ሰዎቹ ስለተለዋወጡ ብቻ ለቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ለግለ ሰቦች ስሜት ሥልጣናቸውን አሳልፈው ሲሰጡ ማየት በትዝብት ጉዳዩን ከመመልከት ውጭ ሌላ ሊባል የሚችል ነገር የለም።[534]

እኒህ አባቶች በማንና በየትስ የተቀነነ ቀኖና እንደሚጠቅሱ ብና ውቅ፣ እኛም መማር እንችል ነበር። ንጹሕ ሐሳብ የያዙትን የቤተ ክርስቲያን ልጆች፥ እውነተኛ መስለው ለቀረቡ ግለ ሰቦች አሳል ፈው ከሰጡ፤ ይህን ሁኔታ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር እንዴት ያዩታል? ተብለው ቢጠየቁ ምን ሊመልሱልን ይችሉ ይሆን? [535] ሁኖም ግን ይህን ሐሳብ የሚያነብ ሰው፣ ሕጋዊ የከህነት ውከልና ያላቸውን አባቶች የከህነት ሥልጣንና ትውፊታዊና ቀኖናዊ ሲኖዶስን መቃወም አለመሆኑን ማሳወቅ የግድ ነው።በግልጽ አነጋገር "ግብራቸውን እንጂ ሥልጣነ ከህነታቸውን አልተቃ ወምንም" ማለት ነው።

በዚያ ስም የሚቀልዱ ግለ ሰቦች ግን የዮሐንስ አፈወርቅ ጠላት የነ በረውን ማቴዎስን ይመስል እየተገለባበጡ ለጠላት መሣሪያ በመ ሆን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የተነሡ ያስመስላቸዋል።[536]

[534] የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴና የማኅበረ ተዋሕዶ አማካሪዎች ያወጡትን ደንብ ናሙና በዚሁ በዋቢ ዝርዝር ውስጥ ይመልከቱ።

[535] *ፍትሕ መንፈሳዊ ለንቀጽ ለምስት ቍጥር 178.*

[536] *ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ትርጉም በያረጋል አቢጋዝ ገጽ 55*

እንዲህ ሲያደርጉ የምናያቸው አባቶች፥ በሚያደርጉት ስህተት፥ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት አደራ የተጣለባቸውን ከህነት ይወከ ላሉና ብለን፥ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ከጥያቄ ውስጥ ማስገባት የለብ ንም፤[537] ሁኖም ግን ፖለቲከኞቹ ለእነሱ ስሜት የሚስማማ ሐሳብ ያላቸውን ጳጳሳት በከንቱ ውዳሴ በመደለል፣ ቤተ ክርስቲያ ንን እየከፋፈሏት ይገኛሉ። አሳዛኙ ነገር የአባቶች አለመጠርጠር ነው።

ይህም ምናልባት ከዕወቀት ማነስ ወይም ከጥቅም አንጻር ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ ሳይታረም በዚሁ ከቀጠለ አሁን ባለንበት ወቅት የብዙዎቹ በራስ ስሜት ላይ ብቻ የተመሠረተው አካሄድ፥ በጠቅላላው ሕዝባችን ላይ ያንዣበበ መከራ ሆኖ እየታየ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ የተሳካ ውጤት አይታይም። ይህን ሐሳብ እንዲህ ብለን ልናስቀምጠው እንችላለን፤ የትውልደ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ወዳድነት መንፈስ፥ በትውልደ ደርግና ወያኔ አልፎ፥ ከድኅረ ዘመናዊነት ጋር ተጋጭቷል።[538]

ይህ መንፈስ ከእርሱ በቀር ሌላ ዐዋቂ ሰው አለ ብሎ አያስብም፤ ስለ ሆነም ሐሳብን የመስጠትና የመቀበል ፍላጎት የለውም። በመ ሆኑም ከሱ ሐሳብ የወጣውን ሁሉ ስሕተተኛ ነህ ስለሚል፥ የከፍ ፍል ምንጭ ሁኖ ይታያል። መንፈሱ በፖለቲካው ያደረገውን ክፍፍል በቤተ ክርስቲያንም አስገብቶ፣ ቤተ ክርስቲያንን ሰላም

[537] *ፍትሕ መንፈሳዊ ለንቀጽ ለንድ ቍጥር ለንድ*

[538] አንዳርጋቸው ጽጌ ነጻነት ያማያውቅ ነጻ አውጭ

ነሥቷታል፣ ከርስቲያኑንም ሕዝብ በቡድን ከፋፍሎታል።[539]በዚህ የጨለምተኝነት መንፈስ የተሸበበው ትውልድ በሦስት ቡድን ተከፍሎ፤ በውስጥ ደግሞ ለቀኑጥር በሚያታክት ሁኔታ ተበታትኖ እሱ እየተተራመሰ ቤተ ክርስቲያንንም እያወካት ይገኛል፤[540] ትውልዱ ለእሱ የማይስማማ ሐሳብ መስሎ ከታየው፥ በእውነተኛ አምክንዮ ላይ የተመሠረተ ራእይ የያዘ እንኳ ቢሆን ከጠላት ወገን ለመፈረጅ ወደ ኋላ የማይ ልበት ሁኔታ እየታየ ነው።

ትውልዱ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ *"ጨለምተኛና ግራ አክራሪ"*[541] በአቶ ዮሐንስ መሸሻ *"ዘረኛና የዘረኝነት ምንጭ"* [542] በአቶ ተስፋዬ መኮንን *"እገርና ራሂይ አንድ ሳያደርገው በእሥር ቤት አንድ የሆነ"* ፤ ተብሎ ተገልጿል።[543] ትውልዱ ቤተ ክርስቲያንን ለችግር የጣ ላት አንደኛው አካል ስለ ሆነ፣ በዚህ መጽሐፍም መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ባጭሩ እናየዋለን። ትውልዱ የተለያየ ቡድን ስላለው፣ በቡድን በቡድን ስሙ ልንጠራው እንችላለን።

በዚህም ምክንያት *"እነዚህ"* የሚል ቅጥል ሰጥተነዋል። እነዚህ ቡድኖች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው አለን ይበሉ እንጂ፤ አንዳቸውም ለቤተ ክርስቲያን ሲጠቅሙ አይታዩም። ቡድኑ በዓይነትና በመጠን የተለያየ ስም ይኑረው እንጂ ባሕርዩ አንድ

[539] ገለልተኛ፥ የአዲስ አበባ ሲኖዶስ፥ ሕጋዊ ሲኖዶስ፥ የሚለውን ቡድን ሲሆን የአዲስ አበባው ብቻውን ሦስት ቡድን አለው ይኸውም የአቶ መለስ ቡድን፥ የአቶ ስየ ቡድን፥ ከሁለቱም ያልሆነ ገለልተኛ ቡድን ፥ በመባል የተከፋፈለውን ቡድን ይመለከቷል።

[540] *ዝኒ ከማሁ*

[541] አንዳርጋቸው ጽጌ ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጭ።

[542] ዮሐንስ መሸሻ የኢትዮጵያ አሰተዳደር የፖለቲካዊ ሂደት።

[543] ተስፋየ መኮንን ይድረስ ለባለታሪኩ።

ነው። እያንዳንዱ ቡድን ሌላውን ቡድን ወንጅሎ የሚጠራበት ስምና ግብር አለው። አንዱ ሌላውን ምን ዓይነት ባሕርይና ስም፤ እንደሚሰጠው በመጠኑ ማብራሪያ ያስፈልጋልና እንደሚከተለው እንመልከተው።

<u>የመጀመሪያው፤</u> ቡድን አሁን በሁሉም ዘንድ በከፋቱ በሚታወ ቀው፥ መንግሥት ተመድቦ የሚሠራው ቡድን ነው ይኸው ቡድን በባለሥልጣኑ ወያኔ መራሽ መንግሥት እየተደገፈ ያለው ሲሆን፥ በስደተኛው ሲኖዶስ ሕገ ወጥ ተብሎ የሚጠራው፥ በአዲስ አበባ የሚገኘው በብዙዎች እምነትና አጠራር የወያኔ ሲኖዶስ የተባለው ቡድን ነው።[544]

ይህን ቡድን በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን ዓላማውን ያሳካለት ዘንድ የቀረጸው የወያኔ መንግሥት ሲሆን፤ ይህን ያደረገበት ምክ ንያት፣ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የአገርን ሉዓላዊነት የሚጻረሩ ሥራዎችን ስለሚሠራ ለዚህ ዓላማው ቤተ ክርስቲያን ለመሣሪያነት እንደምትጠቅመው ስለሚያውቅ ነው።: [545] ቤተ ክርስቲያን አንድም በሱ ቁጥጥር ሥር መሆን አለባት፤ አለበለ ዚያም መበታተን አለባት፤ ብሎ ስለሚያምን ነው።[546]

ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ መጻሕፍትና መረጃዎች፣ በራሱ ክልል ውስጥ የነበሩ የፖለቲካው ተባባሪዎች እያወጡ ስለ ሆነ የዚህን አውነተኝነት ለማወቅ የመረጃ እጥረት ይኖራል ብሎ የሚያስብ

[544] *የተከደነ ያማይገለጥ የለም*

[545] *ዝኒ ከማሁ*

[546] *ዝኒ ከማሁ*

የለም።[547] በመሆኑም የአዲስ አበባው ቡድን የወያኔ ሥራ አስፈጻሚ ቡድን ነው፤ የሚለውን እውነት የሚያስተባብል ማንም የለም። ስለዚህ የአዲስ አበባው የወያኔ መንግሥት ሠራሹ ቡድንና የወያኔ መንግሥት ዓለማ ቀኖና ማፍረስ ብቻ አይደለም። በስደት ያለችው ቤተ ክርስቲያንም እንድትኖር አይፈልግም።[548]

ስለ ሆነም በአንድም ሆነ በሌላ፣ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ መሰና ክል ገጥሞት ከሕዝብ እንዲለይ ይፈልጋል።[549] ለዚህም ዓላማው ተፈጻሚነት በስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም እንዳይኖር ይጥራል። ይህ ደግሞ፣ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ከተሰደደበት ዓላማ ጋር የሚፃረር ነው። ስደተኛው ክፍልና ለአንድነት የሚሠሩ ወገኖች ሁሉ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በሚያዘው መሠረት አንድ ለመሆን ምን መሟላት እንደሚገባው፣ በቁልፍ ጉዳዮች ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ጥያቄውም ሲቀርብ፥ በቀ ኖና ቤተ ክርስቲያን ላይ የተመሠረተ መሆን ስላለበት ሁኔታዎች መመቻቸት ይኖርባቸዋል።[550]

ስደተኛው ክፍል ለዚህ ጥያቄ ፍርሃትና ይሉኝታ ሊኖር እንደማ ይገባ ማመን ይኖርበታል። የቆመበትን ዓላማ ሕግ የማስጠበቅ ሥራ ነው ብሎ ካመነ ደግሞ፥ ይህን ዓላማውን ተግባራዊ እያደ ረገ በግልጥ ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ያስፈልገዋል። ስደተ

[547] የአቶ ታምራት ላይኔ ምስክርነት

[548] የድርድሩን ሁኔታ የሚከታተሉት ወኪሎች በራሳቸው የሚያቀርቡት የመደራደሪያ ሐሳብ ይህን የሚያረጋግጥ ነው።

[549] Kenenan B. Osborne, Order and Ministry. pp. 67-77

[550] Ibid

ኛው ከፍልም ድርድር አይጀመር ማለት የለበትም፤ ዓላማው ይህ መሆን እንደሌለበት ማሳወቅ አለበት። በስደተኛው በኩል መነሣት ያለበት ጥያቄ፣ ከአደራዳሪዎቹ ማንነት ላይ ሊሆን ይችላል።[551]

አደራዳሪዎች ወይም የሰላም ጉባኤ ከተባሉት ሰዎች ራሳቸው ለተነሡበት የአንድነት ዓላማ በተመለከተ መች ሠሩ? ለቤተ ክርስቲያን የሚያስቡ ከሆነ ለምን አንድነቱን እነሱ አይጀምሩትም? በማለት በብዙ ሰዎች ዘንድ ከፍተኛ ጥያቄና ጥርጣሬ አለ፤ ይህን የሚሉበት ምክንያት ዝም ብለው አይደለም። ከሰላም ኮሚቴው አባላት አንዳንዶቹ ገለልተኛ ከሚለው ካምፕ ውስጥ ስለ ሆኑ፣ አንድነት ለሚለው መርሕ ሕሊናቸው ምን ያህል ይገዛላቸዋል? ለማያምኑበት ጉዳይስ እንዴት ሊሠሩ ይችላሉ? በሚል ምክንያት ነው። ከዚህም ጋር ከሰላም ኮሚቴው ውስጥ፣ በውስጣቸው ለአንዱ ምሥጢር የሆነው ጉዳይ ለሌላው ይወራል። ይህ የድር ድር ጉዳይ ለማይመለከታቸው ሰዎች ደርሶ ለሌሎቹ የፖለቲካ አጀንዳ ሁኖ ይቀርባል የሚል ጥያቄም ስጋትም አለ።

ይህም ከተመከሮ የተነሣ የሚቀርብ ጥያቄ ነው። ለአንድነት ይጠ ቅማሉ የተባሉ ጉዳዮች በአግባቡ ካልተያዙ፣ ልዩነቱን አስፍተው ወደማይጠገን ደረጃ እንዳያደርሱት ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይ ቃል።[552] በሲኖዶሱ የተመደቡትን የሰላም ኮሚቴ አባላት በመለ ያየት ለየብቻ ማነጋገርስ ለምን አስፈለገ? የሚሉት ጉዳዮች ሁሉ መጠናት አለባቸው። ምክንያቱም በጥንቃቄ ካልሆነ በአገር ውስጥ

[551] በብዙዎቹ ሐሳብ፣ አደራዳሪዎቹ ነጻነት የላቸውም ይላሉ፤ በዚህም ምክንያት እውነተኛ የሆነ የአደራዳሪነት ሥራ ይሠራሉ ብሎ ለማመን ይቸገራሉ።

[552] The Counsil of Cconsitntine

ያለው ሕገ ወጥ ቡድን እነዚህን ሁሉ እየተጠቀመ የመበተን ዓላማውን እንደሚያሳካበት ስለሚታመን ነው፤ በተቻለ መጠን የውይይቱ ሂደት ጥንቃቄ የተሞላበት እንዲሆን ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።[553]

በአገር ውስጥ ያለው ቡድን የሀገርን ገንዘብ ለልማት ሳይሆን "ለሐሳቤ አይስማማኝም" የሚለውን ሁሉ፣ ለማጥፊያነት ስለ ሚጠቀምበትና አጥፊ ድርጅትም በመሆኑ ለስደተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ተቃዋሚ ጠላት እርሱ ነው። በአንጻሩም ስደተኛዋ ቤተ ክርስቲያን፣ ለአገር ቤቱ ቡድን፣ የስህተት አጋ ላጭ ተቅዋም ሁና ቀጥላለች፤[554] ለዚህም በጣም ይጠላታል፤ በመሆኑም ስደተኛው ክፍል የቤተ ክርስቲያንን ችግር ማየት ያለበት እውነትን ከማስጨበጥ አንጻር መሆን ይኖርበታል።

በስደተኛውና በአገር ቤቱ መካከል ያለው የኃይል ሚዛን ምንአል ባትም የእኛን ቤተ ክርስቲያን ችግር ከሌሎቹ ልዩ ሊያደርገው ይችላል። የዚህም ምክንያት በበቂ በጀት ተመሥርቶ ለጥፋት ከተ ሰማራ ኃይል ጋር መወዳደሩ ከባድ ስለ ሆነ ነው። ከላይ የጠቀስነ ውን የስደተኛውን አደናጋሪ ፖለቲከኞችን ተጽዕኖም መዘንጋት የለብንም።

የዚህ ዓይነት ችግር ገጥሟቸው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ችግራ ቸውን የተወጡት፣ ዕውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ሐሳባቸውን፣ በእውነተኛ ጥናት ላይ አድርገው በጋራ በመሥራታቸው ነው

[553] የመጀመሪያውን ውይይት መግለጫ መመልከት የስጋቱ መነሻ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ያስችላል።
[554] ለምሳሌ የሚሆኑ መግለጫዎችን በዋቢው ለነዶች ክፍል ይመልከቱ።

ችግራቸውን ያስወገዱት እንጂ፤ ከሰማይ በወረደ ተአምር አይደ ለም። ጥናታቸውም ዳግም በቤተ ክርስቲያን ችግር እንዳይነሣ ያደረገ፣ ቢነሣም እንኳ ችግሩ የሚወገድበትን መፍትሔ ያስቀመጠ ጥናት ነበር።[555]

ለምሳሌ የሩሲያንና የአርማንያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስንመ ለከት፣ ከፍተኛ ጥናት በማድረጋቸው ነው ኮሚኒስቱ መንግሥት ሲወድቅ መልሶ አንድ ለመሆን ጊዜ ያልወሰደባቸው።[556] በእኛ ቤተ ክርስቲያንም ሊደረግ የሚገባው፣ ለስደትና ለከፍፍል ዋና ምክንያት የሆነው ዓለም አቀፉ ቀኖና መጣሱ ስለ ሆነ፣ ሁሉም በጋራ ዕውቀቱን፣ ገንዘቡን፣ ሐሳቡን፣ ማፍሰስ ያለበት <u>የተጣሰው ሕገ ቀኖና እንዴት ይከበር?</u> በሚል መርሕ ላይ መሆን አለበት።[557]

ሲኖዶስ መኖር ካለበት በሕጋዊነቱ ሕጉን አስጠብቆ ነው። የግለ ሰቦች ኩርፊያ ማባበያ ሁኖ መኖር የለበትም። አሁን የተቸገርነው ቀኖናን ከመቻቻል ጋር የምናዳብለው ሰዋዊ አባባል እያደረግነው ነው። ይህ አመለካከት ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠናክር ሐሳብ አይ ደለም።

አሁን ያለንበትን አቅዋም ስናስተውለው፤ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ላይ የተመሠረተውን ክብር ዝቅ፣ የግለሰቦችን ሐሳብ ግን ከፍ ከፍ በማድረግ ላይ ነው ያለነው። ይህ ዓይነቱ አቅዋም ስደተኛውን

[555] *Meyendorff, Vision of Unity, p. 98.*
[556] *Amirmenian Church Historical Studies, Matter Doctrine and Adminstration, pp. 231-300; በዚህ መጽሐፍ የአርመን ኦርቶዶክስ አስተዳደራዊ ችግር የተገለጠ ሲሆን እንዴት ያን ሁሉ ችግር ለንዳለፉትም ጠቅሚ ሐሳብን ይሰጣል። ለዚህ ነው በመጽሐፉ ሰፊ ክፍል የተሰጠው።*
[557] *Ibid*

ከፍል ትዝብት ላይ እየጣለው ይታያል። ስለዚህ ስደተኛው ከፍል መጀመሪያ የቆምኩበት መሠረት ምንድን ነው? ማለት ይኖርበ ታል፤ ከዚህ ተነሥቶ ነው የአንድነትን ጉዳይ ማስቀደም ያለበት። ይዞት በተነሣው አቋም መሠረት፣ የቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ሕግ ከማስጠበቅ ላይ ያትኩር ነው እምንለው።

ጉዳዩን በውል ስንመለከተው፣ ለአንድነቱ እስከምን መሄድ አለ ብን? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ይዞ የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖናዊ እውነት መሠረት ማድረግ አለበት እንጂ፣ ከውጭ ግለ ሰቦችና ከስም ፖለቲከኞች እርዳታ መፈለግ የለበትም። ቀኖናው የተጣሰው ከምን ላይና እንዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ በመጠ የቅ፣ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ የሠራውን ስሕተት ማጥናትና መመርመር ነው ያለበት። ከዚህ ላይም መጠነኛ ግንዛቤ እንዲ ኖረን ቀኖናዊ ማብራሪያ ያስፈልጋል፤ ስለ ሆነም እንደሚከተለው እንመልከት።

የአዲስ አበባው ሲኖዶስ፣ በሐዋርያት ቀኖና መሠረት፣ ከሁለት በላይ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባኤ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የሚወክል ሲኖዶሳዊ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል ስለሚል ቀኖናዊነቱን በመርሕ ደረጃ እንቀበለው እንበል[558] [559]። ሁኖም ግን በፓትርያርኩ ላይ የወሰደው ሲኖዶሳዊ ውሳኔ ስለሌለ፣ ሲኖ ዶስ የሚያሰኘውን ኃይል ሊያገኝ አልቻለም፣ አይችልምም። ምን ስህተት ሠራ? ምንስ ውሳኔ ማስተላለፍ ነበረበት? ለሚሉት ጥያቄ

[558] *The Apostolic Canon, Canon II.*
[559] *Ibid*

ዎች መልስ፣ ሲኖዶሱ ቢያንስ ሦስት እጅግ በጣም ትልልቅ ስሕተ ቶችን ሠርቷል እንላለን። እነዚህም፤

<u>የመጀመሪያው ውሸት፣ እውነትን ከዷል፤</u>

በወያኔ መንግሥት የታገደውን የሠራተኛውን ደመወዝና የቤተ ክህነቱን የሥራ ማስኬጃ በጀት ለማስለቀቅ ሲባል፣ ሳይታመሙ ታመዋል፤ ብለው የመንግሥትን ጉዳይ ለማስፈጸም አባታቸውን ክደው፥ ምንም ዓይነት የቀኖና ድጋፍ ሳይኖር ወርደዋል፣ ማለታ ቸው፣ በሁለት መንገድ ክህደት ነው፤[560] የቤተ ክርስቲያኒቱን አባት መካድ ታላቅ በደል ሁኖ እያለ። ይህም አልበቃ ብሎ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪ አባት እንደ አባት ካለማስከበሩም በላይ፣ እንደ አንድ ዜጋ እንኳ ሰብአዊ መብታቸውን ማስከበር አለመቻሉ ትልቅ ውርደት ነው።

ይህን የሰብአዊ መብት ጥበቃ የቤተ ክርስ ቲያን ራስ በሆኑት አባት ቢለማመደው ኑሮ ለማንኛውም ዜጋ ያደርገው ነበር። ይህ በአንድ በኩል የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ከአደጋ መጠበቅ አለመቻል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ሲኖዶሱ የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብት ሊያስጠብቅበት ይገባው የነበረውን ኃላ ፊነት የተወጣ ባለመሆኑ ስህተትም ሠርቷል፤ በደልም ፈጽሟል።[561]

[560] *ምማይገለጥ የተከደነ የለም ።*

[561] *ዝኒ ከማሁ*